የዜግነት ትምህርት የተማሪ መማሪያ መጽሃፍ

7ኛ ክፍል

በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባነት ተዘጋጅቶ የተተረጎመ

ተርጓሚዎች

1. እየሩሳለም ገርባባ
2. ፈጠነ ቡልቻ
3. አሸብር ሀብታሙ
4. ሰለሞን ንጉሴ
5. ስሪቃ ገመቹ

አርታዒዎች

1. አስመራ ቤጊ
2. ሞቲ ድንቁ
3. ፍራንኦል ዋቅጅራ
4. ኃይሉ ብሩ
5. ተስፋዬ አበባየሁ

ግራፍክስ

ታደሰ ድንቁ

ገላጭ መስል

ቡዛዮ ግርማ

ገምጋሚ

ደረጀ መኮንን ዬሬሳ

© ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014/2022

ይህ የተማሪዎች መጽሃፍ በኢፌዴሪ የትምህርት ምንስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አስተባባርነት ተስማምቶ ወደ አፋን ኦሮሞ የተተረጎመ ነዉ።

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው።ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል።

ማውጫ

ገፅ

ምዕራፍ አንድ፡ የዜግነት 3
1.1. ዜግነት 4
1.2. የመልካም ዜጋ ባህሪያት 6
1.3. የመልካም ዜጋ አስፈላጊነት 10
1.4. ዜግነት የሚገኝባቸውና የሚታጣባቸዉ መንገዶች 13
1.5 በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ መስፈርቶች 17
ምዕራፍ ሁለት፡ መንግስት እና የመንግስትአስተዳደር 22
2.1 የመንግስት ፅንሰ ሀሳብ 22
2.2 መሰረታዊ የመንግስት ምሶሶዎች/ አካላት 23
2.3. የመንግስትአስተደደር ተግባራት 27
2.4. የመንግስትአስተዳደር አይነቶች31
2.5 መንግስት እና በመንግስት አስተዳዳር መካከል ያሉ ልዩነቶች 33
ምዕራፊ 3፡ ዴሞክራሲ 38
3.1. የዴሞክራሲ ትርጉም 38
3.2. የዴሞክራሲ መነሻ 39
3.3 የዴሞክራሲ አይነቶች 40
3.4 ዴሞክራሲን የማስፈጸም መንገዶች 41
3.5. ዲሞክራሲ ላይ ያሉ እሳቤዎች/አተያዮች/አመለካከቶች 44
3.6 አገር በቀል ዴሞክራሲያዊ ተግባራት/ልምዶች 44
ምዕራፊ 4፡ የሕግ የበላይነት 49
4.1. የሕግ የበላይነት ጽንሰ-ሐሳብ 49
4.2. የሕግ ምንጮች 52
4.3. የህግ የበላይነት አስፈላጊነት 55
4.4. የህግ የበላይነት መገለጫዎች 58
4.5. የሕግ የበላይነት እና የግለሰብ የበላይነት 60
4.6 የህግ የበላይነት እንቅፋቶች 60

ምዕራፍ 5: ሰብዓዊ መብቶች 64
5.1. የሰብአዊ መብት ጽንሰ-ሀሳብ 64
5.2. የሰብዓዊ መብቶች መገለጫ ባህሪያት 66
5.3. ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር አስፈላጊነት 67
5.4. የሰብዓዊ መብቶችን የማስጠበቅ ሀላፊነቶች 68
5.5. የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች69
5.6. የሰብዓዊ መብቶችን በማረጋገጥ ረገድ የመንግስት ሚና 71
ምዕራፍ 6፡ የማህበረሰብ ተሳትፎ 74
6.1 የማህበረሰብ ተሳትፎ ፅንሰ- ሀሳብ 74
6.2 የማህበረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊነት 75
6.3 የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጥቅሞች 77
6.4 የማህበረሰብ ተሳትፎ አይነቶች 81
ምዕራፍ 7፡ በጥልቀት ማሰብ 86
7.1 በጥልቀት ማሰብ ፅንሰ- ሀሳብ 86
7.2 በጥልቀት የማሰብ አስፈላጊነት 88
7.3 በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶች 90

ምዕራፍ 1 የዜግነት

መግቢያ

በስድስተኛ ክፍል ስለ ዜግነትና ሥነ ምግባር እሴቶች ተምረሃል/ሻል። በሥነ ምግባርና በዜግነት ትምህርት መካከል ያለውን ግንኙነትም ተረድተሃል/ሻል ። በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ደግሞ የዜግነት ምንነት ፣ የመልካም ዜግነት መገለጫ ባህሪያት እና አስፈላጊነት እንዲሁም አንድ ሰው ዜግነቱን እንዴት እንደሚያገኝና እንደሚያጣ ትማራለህ/ሽ። በመጨረሻም የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ በተመለከተ ትምህርት ይቀርብላችኋል።

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

- የዜግነትን ፍሬ ነገር መረዳት፤
- የዜግነት ባህሪያትን ለይቶ መግለጽ፤
- የመልካም ዜግነትን አስፈላጊነት ማበራራት፤
- ዜግነት የሚገኝበትና የሚታጣበት መንገዶችን መዘርዘር፣
- የኢትዮጵያ የዜግነት ሕግ መሰፈርቶችን ማብራራት::

1.1. ዜግነት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፤-

- የዜግነት ምንነት ትገልፃለህ/ሽ፤

- የዜጎችን መብቶችና ግዴታዎችን ትዘረዝራለህ/ሽ፤
- የዜጋና የዜግነትን ልዩነት ትለያለህ/ሽ፡፡



1- ዜግነት ከሚለው ቃል ምን ተረድተሃል/ሻል?

2- በዜጋና በዜግነት መካክል ያለው ልዩነት ምንድነው?

የዜግነትን ፅንስ ሐሳብ ከማብራራት በፊት የዜግነትን ምንነት መግለፅ አስፈላጊ ነው፡፡ ዜጋ ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ ዜጋ ሆኖ በሕግ የተወሰኑ መብቶችና ኃላፊነቶች ያሉበት ሰው ማለት ነው፡፡እንዲሁም ዜጎች በመንግሥት ጥበቃ የሚደረግላቸው ሆኖ የተወሰኑ መብቶችና ኃላፊነቶች ተሰጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው ዜጋ ለመባል በህግ የተወሰነ መብት እና ግደታ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ ሰው እንደኢትዮጵያዊ ራሱን መግለፅ፣ የሕግ ከለላ ማግኘት፣ ለሀገሪቱ ሕግ መታዘዝ፣ ግብር የመክፈልና ሌሎች ሀላፊነቶችን መወጣት አለበት፡፡ በተጨማሪም አንድ ዜጋ የሀገሩን ሕግ ማክበርና ከውጭ ጠላት የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡



ስእል 1.1 የዜግነት ማንነት መገለጫ

ዜግነት የአንድ ሀገር ማህብረሰብ ሙሉ አባል መሆን ነው። በዚህ መሠረት ዜግነት የሚያሳየው በአንድ ፖለቲካዊ ማህብረስብ ውስጥ አባላቶቹ ከመንግሥት ኃላፊነቶችን የመቀበል ግዴታ ሲኖርባቸው መንግሥትም ማህበረሰቡን የመጠበቅ ግዴታ አለበት። ስለዚህ ዜግነት የህግ ዕውቅናና የአንድን ሰው ማንነት ማረጋገጫን ያሳያል ማለት ነዉ።

የጉዳይ ጥናት

ዜጎች ከመንግሥት ማግኘት ከሚገባቸው መብቶች አንዱ የትምህርት ዕድል ነው፡ ፡ በአንዲት ትንሽ መንደር ውስጥ ሁለት ልጆች ነበሩ ። እነዚህ ልጆች በተለያዩ ሥራዎች ወላጆቻቸውን ይረዱ ነበር ። አንድ ቀን መምህራን በዚያች ትንሽ መንደር ሲደርሱ ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት መላክና መማር እንዳለባቸው ተገነዘቡ ። በዚህ ምክንያት፣ መምህራኑ ወደ ልጆቹ ወላጆች ቀርበው ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኳቸው ጠየቁ ። የልጆቹ ወላጆችም የመምህራኑን ሃሳብ በጥሞና ካዳመጡ በኋላ በሐሳቡ እንደማይስማሙና ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መላክ እንደማይፈልጉ ይገልፃሉ።በመጨረሻም የልጆቹ ቤተሰቦች ልጆቹን ወደ ት/ቤት ከመላክ ይልቅ በቀጣይነት በሥራ እንዲያግዟቸው ይወስናሉ።

ከዚህ በላይ በቀረበው ጉዳይ ጥናት ላይ ተንተርሰህ/ሽ ለቀረቡትን ጥያቄዎች መልስ ስጥ/ጪ።



የቡድን ሥራ፡ ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን ተወያዩበት፡-

1. የዚህ ትረካ መጨረሻ ምን ሊሆን ይችላል?
2. ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ላለመላክ ሰበብ ማቅረባቸው ምን ያህል አሳማኝ ነው?
3. አንድ ልጅ ትምህርት ቤት የመሄድ መብቱ የወላጆች በጎ ፈቃድ ብቻ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ?

1.2. የመልካም ዜጋ ባህሪያት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፤-

- ☞ የመልካም ዜጋ ባህሪያትን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤
- ☞ የመልካም ዜጋ ባህሪያትን ታሳያለህ/ሽ፤
- ☞ የመልካም ዜጋ ባህሪይን ትለማመዳለህ/ጃለሽ።



1. መልካም ዜጋ ማለት ምን ማለት ነው?
2. መልካም ዜጋ ከሚያሳያቸው ባህሪያት ውስጥ ሶስቱን ጥቀስ/ሽ

ጥሩም ሆነ መጥፎ ዜጋ ሆኖ የሚወለድ ሰው የለም ። መልካም ዜግነት በቤተሰቦቻችን፣ በማህበረሰቦች፣ በወዳጆቻችን እና በመምህራን እንማራለን። መልካም ዜጋ ከሚታወቅበት ባህሪዎች ጥቅቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ☞ ሌሎችን ያከብራል፤
- ☞ ሌሎችን ይረዳል፤
- ☞ የሌሎችን ሰዎች አስተያየት ይሰማል፤
- ☞ ራሳቸውን መርዳት የማይችሉ ሰዎችን ይረዳል፤
- ☞ ከሌሎች የህብረተሰብ አባላት ጋር ተስማምቶ ይኖራል፤
- ☞ ሁልጊዜ ለመማር ፈቃደኛ ነው፤
- ☞ የማህበረሰባዊ ሃላፊነቶቹንና መብቶቹን ጠንቅቆ ያውቃል።

የጉዳይ ጥናት

የዕውቀት ምንጭ ት/ቤት በዓመታዊ የትምህርት ቤት መዝግያ ላይ ለየት ያለ ተግባር ያከናውናል። በዚህ በዓመታዊው የትምህርት ቤት መዝጊያ ቀን በዓል ላይ የተማሪ ወላጆች እንዲገኙ ይጋበዛሉ። በመቀጠል ትምህርት ቤቱ በውጤቱ አንደኛ የሆነ እና በተጉዳኝ ትምህርት ውስጥ በትጋት የተሳተፈ ተማሪ በተለየ ሁኔታ በወላጆች ፊት በታላቅ ክብር እንዲሸለም ያደርጋል። ለዚህም በዓመታዊው ትምህርት ቤት መዝጊያ ቀን በዓል ላይ የሚገኝ ሁሉ የዕለቱ አሸናፊ ተማሪ ማን እንደሆነ ለማወቅ ይጓጓል። በመጨረሻም የዓመቱ ልዩ ተሸላሚ ተማሪ በሰም ተጠርቶ ልዩ ሽልማቱን በተማሪዎችና በቤተሰቦቻቸው ፊት በክብር ይቀበላል፡ ፡ ከዚህ በመነሳት ብዙ ተማሪዎች በዚህ ት/ቤት በየዓመቱ ይህን ሽልማት ለማግኘትና ቤተሰቦቻቸውን ለማስደሰት በተስፋ ይጠባበቃሉ። ከነሱም ውስጥ በጣም የሚተጉ በየዓመቱ ተሸላም ይሆናሉ።

ከላይ በቀረበው ጉዳይ ጥናት ላይ በቡድን ተወያዩበት

1. ከቀረበው ታሪክ ምን ትረዳላችሁ? በታሪኩ ውስጥ የቀረበ ተማሪ ፣ ጥሩ ዜጋ ነው? መልሳችሁ አዎ ከሆነ ጥሩ ዜጋ ነው ያላችሁበትን ምክንያት ለመዘርዘር ሞክሩ።

መልካም ዜጎች ሊኖራቸው ከሚገቡት ባህሪዎች ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሀ) ለህግ መታዘዝ - የአንድ ጥሩ ዜጋ የመጀመሪያና ዋናው ህዝባዊ ግዴታ ለሕግ መታዘዝ ነው። ህግ ሰዎች ማድረግ ያለባቸውንና የሌለባቸውን የሚወስን እንዲሁም ማህበረሰቡ ለመተዳደሪያ ብሎ የደነገገው ደንብ ነው ። አንድ ጥሩ ዜጋ ደንቡን ይከተላል፣ ለወላጆች፣ ለመምህራንና በስልጣን ላይ ላሉት አካላት ይታዘዛል። ጥሩ ዜጋ የት/ቤቱን መተዳደሪያ ደንብ የመጠበቅ እና የማክበር ኃላፊነት አለበት።



ስዕል፡ 1.2 የትምህርትን ቤት ደንብና ስርዓት ማክበር

የግንዛቤ ጥያቄ፡

የትምህርት ቤታችሁ ተማሪዎች መመሪያዎችን የማይከተሉና እርስ በርስ

የማይስማሙ ከሆነ ምን ሊፈጠር ይችላል? ከጎናችሁ ካለው ተማሪ ጋር ተወያዩበት፡፡

ለ) ኃላፊነት ፡ ኃላፊነት ሁለተኛውና ዋነኛው የመልካም ዜግነት ባህሪ ነው፡፡ ጥሩ ዜጋ በተሰማራበት ሥራ ወይም የተሰጠውን ግዳጅ በብቃት የሚወጣ ሰው ነው፡፡ኃላፊነት እርምጃ መውሰድን የሚጠይቅ ከመሆኑም በላይ የምናስባቸውን በርካታ ገጽታዎችን ያጠቃልላል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች በዋናነት ከሚጠበቅባቸው ኃላፊነቶች ውስጥ መማር፣ የቤትና የክፍል ሥራን መሰራት፣የክፍል ጓደኞቻቸውን እና አስተማሪዎቻቸውን ማክበር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እንደዚሁም እንደ አንድ ጥሩ ዜጋ የተሳሳተ ድርጊት ካጋጠመ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አካባቢን ንጹህ ማድረግ፣ በማህበረሰብ አገልግሎት ውስጥ መሳተፍ የጥሩ ዜጋ ኃላፊነት ነው፡፡ ከላይ በቀረበው አጭር የጉዳይ ጥናት እንደተረዳኸው/ሽው ለሽልማት የሚቀርብ ተማሪ በክፍል ውስጥ ካለው ትልቅ ኃላፊነት በተጨማሪ በተጓዳኝ ትምህርት ውስጥ በትጋትና በቁርጠኝነት በሚያደርገው ተሳትፎ ነው፡፡



ስእል 1.3 ተማሪ ኃላፊነትን በመውሰድ የቤት ስራ ሲስራ/ስትሰራ



የግንዛቤ ጥያቄ

1. ኃላፊነት የሚሰማው ተማሪ ነህ/ሽ?
2. ተጠያቂ መሆን አለመሆንህን/ሽን እንዴት ማወቅ ትችላለህ/ያለሽ?

ሐ) መቻቻል - ልዩነቶችን ተቀብሎ በሰላም አብሮ መኖር ነው። መቻቻል ሌሎች የራሳቸው አመለካከት እንዲኖራቸው፣ እምነታቸውን እንዲገልጹ እና ከራሳችን የተለየ አመለካከት እንዲኖራቸው መብት እንዲከበር ያስተምረናል። በተጨማሪም መቻቻል ከሀሳብ፣ ከአመለካከት እና አለምን የመረዳት መንገዶች ጋር አብሮ የመኖር ችሎታ ነው። ስለዚህ መቻቻል የመልካም ዜጎች አንዱ ባህሪ በመሆኑ ዜጎች በሰላም አብረው እንዲኖሩ ያደርጋል።



ስእል 1.4 በልዩነት ውስጥ መቻቻል



የፕሮጀክት ሥራ

የተለያየ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ባህልና ብሔር ካላቸው ሰዎች ጋር መኖር ምን ዓይነት ጥቅም ሊኖረው እንደሚችል ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ አቅርቡ

መ) የሀገር ፍቅር ስሜት፡ ይህ ሌላው የጥሩ ዜጋ ባህሪ ነው። የሀገር ፍቅር ስሜት ያለው ዜጋ ለአገሩ ጥቅም መስዋእትነት ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ እውነተኛ ሰው ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ የበርካታ ጀግኖች እና አርበኞች ሀገር ነች። የሀገራችንን ነፃነት ለማረጋገጥ ውድ ህይወታቸውን የከፈሉ ብዙ ጀግኖች አሉ። የአገር ፍቅር ስሜት ከወታደራዊ አገልግሎት ውጪ በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል። ለምሳሌ፡ በዲፕሎማሲ፣ በትምህርት በመሳተፍ

ለሀገራችን ያለንን ፍቅር ማሳየት እንችላለን። እንዲሁም በሕክምና፣ በግብርና፣ በንግድና ሌሎች የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ ማሳየት እንችላለን። በዓለም አቀፍ መድረክ የሀገራችንን ስምና ሰንደቅ ዓላማ የሚያስተዋውቁ አርቲስቶች፣ አትሌቶችና ሌሎች ባለሙያዎችም ጀግኖቻችን ስለሆኑ ኩራቶቻችን ናቸው ።

በአጠቃላይ ከላይ የተመለከትናቸው የጥሩ ዜጋ ባህሪያት የእያንዳንዱን ዜጋ መብቶች እና ግዴታዎች በአግባቡ መጠቀምና እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁል ጊዜ እነዚያን የመልካም ዜግነት ባህሪያት መያዝ እና መጠቀም አለብን።



ምስል 1.5 ኮ/ል አብድሳ አጋ (የኢትዮጵያ አርበኛ)




ምስል 1.6 ደራርቱ ቱሉና አበበ ቢቂላ



የቡድን ሥራ

1. የአገር ፍቅር ስሜት መገለጫ ባህርያትን መጥቀስ ትችላላችሁ?
2. የአገር ፍቅር ስሜትን የሚያዳክሙ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
3. በእናንተ አስተያየት የኢትዮጵያውያንን የአገር ፍቅር ስሜት ለማሳደግ ምን መደረግ አለበት?

1.3. የመልካም ዜጋ አስፈላጊነት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡-

- ☞ የመልካም ዜጋ መነሻ ትለያለህ/ሽ፤
- ☞ መልካም ዜጋ ያለውን አስፈላጊነት ታብራራለህ/ሪያለሽ፤
- ☞ የመልካም ባህሪይ መጎናፀፍ እና ማጣት በማወዳደር ትገልጻለህ/ጫለሽ።



የቡድን ሥራ

በምትማርበት ትምህርት ቤት ውስጥ በተማሪዎችና በአስተማሪዎች ፣ በተማሪዎችና በትምህርት ቤቱ አስተዳደር እንዲሁም በአስተማሪዎች መካከል የመልካም ዜጋ ባህርያት ካልተንፀባረቁ ምን ዓይነት ችግር ሊፈጠር ይችላል?

አምስት አምስት በመሆን በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ሐሳባችሁን አንጸባርቁ

የመልካም ዜጋ ባህርይዎች በግለሰቦች ላይ ጠንካራ የሞራል እሴቶችን ለመትከል ብቻ ሳይሆን በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ አስተማማኝ እና ደጋፊ የሆነ ህብረተሰብ እንዲኖር ያደርጋል። የመልካም ዜጋ ባህሪዎች ጤናማና ዘላቂ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ኅብረተሰብ እንዲፈጠርና ዜጎች በሰላም አብሮ እንዲኖሩ ያግዛል። ሰለዚህ መልካም ባህርይ ያላቸው ዜጎች ሀገራቸውን ወደ ተሻለ ቦታ የማድረስ፤ የመገንባትና ጥንካሬዋን የመጠበቅና የማስጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው ። ከዚህም በተጨማሪ መልካም ዜጎች ተቃራኒ አመለካከት ባላቸው ሰዎች መካከል ገንቢ የሆነ ክርክር እንዲኖር በማድረግ አስፈላጊውን የማቀራረብ ሥራ ይከውናሉ። ለምሳሌ ፡ የመልካም ዜጋ ባህሪያት ያላቸው ተማሪዎች ከእነርሱ ተቃራኒ ከሆኑ ሰዎች ጋር የጋራ መግባባት መፈጠር ይችላሉ። የመልካም ዜጋ ባህርይ ስዎች እርስ በርስ መከባበር እና መረዳዳትን በማዳበር ወደ አንድ የጋራ ግብ እንዲደርሱ ያግዛቸዋል።




የቡድን ሥራ

እንደ አንድ ግለሰብ ኃላፊነትን በመወጣት ለማኅበረሰቡ ምሳሌ መሆን ችያለሁ ብላችሁ ታምናላችሁ? በዝርዝር አስረዱ?



ስእል 1.7 የተማሪዎች ቡድን ክርክር

የፍትህ መጓደልን መቃወምና ፍትሐዊነትን ማራመድ ጥሩ ዜጋ ለመሆን ወሳኝ ነገር ነው። ለምሳሌ ያህል አደገኛ ዕፅ አዘዋዋሪ የሆነን ሰው ወይም በአካባቢያቸው ስርቆት ላይ የተሰማራን ሰው ለሚመለከተዉ አካል ማሳወቅ የጥሩ ዜጋ ባህሪ ነው። እንዲህ ማድረግ ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች አንዱ ለማኅበረሰቡና ለፍትህ ሥርዓቶች ደህንነት አስተዋጽኦ ማበርከት ነው ። እያንዳንዱ ዜጋ ፍትህ እንዲሰፍንና የፍትህ መጓደልን ለመጋፈጥ ቢሠራ አመፅ ይቀንሳል። አመፅ ሲቀንስ ዜጎች ፍትሃዊነትን ለማስፈንና ኢፍትሃዊነትን ለመጋፈጥ ይሰራሉ።



ስእል 1.8 አንድ ተማሪ ወረቀት እየቀደደ በክፍል ውስጥ ሲወረውር

የቡድን ሥራ

አንድ ተማሪ ወረቀቶችን እየቀደደ በመማርያ ክፍል ውስጥ ሲወረውር ብታዩ ምን ታደርጋላችሁ?

መልካም ዜጋ ማንኛውንም የማህብረሰብ አካል የሚንከባከብ ፣ የሚያከብር፣ ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነትን የሚወሰድ ነው። ስለዚህ እንደ መልካም ዜጋ ይህን ማድረግ ከቻላችሁ ሌሎች ያደንቋችኋል። እንዲሁም በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በብሔር ወይም በሌሎች ልዩነቶች ላይ የተመሠረተ ዓመፅ እንዲቀንስ

የራሳችሁን ኣስተዋጽኦ ታበረክታላችሁ። በዚህ መሰረት የሚከተሉት የመልካም ዜጋ ኣስፈላጊነት ይጠቀሳሉ፡-

- ☞ በግለሰቦች ላይ ጠንካራ የሥነ ምግባር ደንብ ማስረጽ፤
- ☞ ኣስተማማኝና ደጋፊ የሆነ ህብረተሰብ ማሳደግ፤
- ☞ ኣገራችንን የተሻለ ቦታ ማድረስ፤
- ☞ ተቃራኒ ኣመለካከት ባላቸው ሰዎች መካከል ገንቢ ክርክር እንዲኖር ማድረግ፤
- ☞ እርስ በርስ መከባበርና መግባባት እንዲኖር ማሳደግ፤
- ☞ የጋራ ግብ ላይ ተባብሮ መስራት፤
- ☞ ተማሪዎች ያላቸውን ገንቢ ኣመለካከት እንዲያሰፉ ማበረታታት፤
- ☞ ስለ ማህበረሰብ ግፍና ጭቆና በጥልቀት ማሰብ፤
- ☞ የፍትህ መጓደልን መገዳደርና ፍትህን ማስፈን፤ እና
- ☞ ለሌሎች ተማሪዎች ኣክብሮትና እንክብካቤ የማሳየት ስሜት ማዳበር።

1.4. ዜግነት የሚገኝባቸውና የሚታጣባቸዉ መንገዶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡-

- ☞ ዜግነት የሚገኝባቸው መንገዶችን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ ፤
- ☞ ዜግነት በመወለድና በዘር ሐረግ ማግኘት የሚቻልባቸው መንገዶች ታወዳድራለህ/ሪያለሽ፤
- ☞ ዜግነት በሕግ ማግኘት የሚቻልባቸውን መንገዶች ትገልጻለህ/ ጪያለ/ሽ።



የግንዛቤ ጥያቄ፡-

ዜግነት እንደት ማግኘትእና ማጣት ይቻላል ?


ዜግነት የኣንድ ኣገር ኣባል ሆኖ በመመዝገብ የሚገኝ ሕጋዊ መብት ነው።ማንኛውም ሰው የሀገሪቱን ህጋዊ ሁኔታዎች ካሟላ የኣንድ ሀገር ኣባል መሆን ይችላል። በኣጠቃላይ ሲታይ ዓለም ኣቀፍ የዜግነትን ህግ ለመወሰን ለእያንዳንዱ መንግሥት ይተዋል። ሰለዚህ ዜግነት በእያንዳንዱ ኣገር የመንግስት ስርዓት መሰረት ሊያገኝ ይችላል። ይህም ማለት ዜግነት የማግኘት ኣሰራር እንደየ ኣገሩ ይለያያል ማለት ነው። ይሁን እንጂ ዜግነት ለማግኘት የሚረዱ የተለያዩ ዘዴዎችን መጥቀስ እንችላለን።

1.0.1 ዜግነት ማግኘት የሚቻልባቸው መንገዶች

በዚህ ትምህርት ክፍል መክፈቻ ላይ እንደተገለፀው አንድ ሰው የአንድን ሀገር ዜግነት ማግኘት የሚችለው በሀገሪቱ ደንብ መሰረት ነው። በዚህ ምክንያት ዜግነት የማግኘት አሰራር በእያንዳንዱ ሀገር የተለያየ ነው። ይሁን እንጂ ዜግነት ለማግኘት የሚረዱ ዋና ዋና መንገዶች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ በመወለድ የሚገኝ ዜግነት፡ በመወለድ የሚገኝ ዜግነት በተፈጥሮ የሚሰጥ ነው። የዚህ አይነት ዜግነት በማህበራዊና ፖለቲካዊ መሰፈርቶች ላይ የሚመሰረት አይደለም። በመወለድ የሚገኙ የዜግነት አይነቶች በሁለት ይከፈላሉ። እነሱም፡- በትዉልድ ቦታ የሚገኝ ዜግነት እና በዘር ሐረግ የሚገኝ ዜግነት ናቸው።

1. **በትውልድ ቦታ የሚገኝ ዜግነት**፡- በዚህ ሃሳብ መሰረት በአንድ ሀገር ክልላዊ ወሰን ውስጥ የተወለደ ሁሉ በራሱ የዛ ሀገር ዜጋ ይሆናል። ይህ የሚያሳየው ደግሞ በዚያ የተወለደ ልጅ የሀገሩ ዜጋ የመሆን ብቃት አለው ማለት ነው ። በዚህ የዜግነት ማገኛ ዜዴ ውስጥ የልጁ ቤተሰብ ዜግነት ታሳቢ አይደረግም። ይህ አይነት ዜግነት የሚያመልከተው የሀገር ባለቤትነት ወይም የአፈር መብት የሚለውን ቃል ነው ። ዜግነትን በትውልድ ቦታ ማግኘት እጅግ በጣም የታወቀ ዘዴ ሰለሆነ ብዙ ሀገሮች ይህን ዘዴ ይጠቀማሉ።



ስእል 1.9 አዲስ የተወለደ/ች ሕፃን

2. **በዘር ሐረግ የሚገኝ ዜግነት፤-** አንድ ሰው በአንድ ወይም በሁለቱም ወላጆቹ ዜግነት ላይ ተመሥርቶ የአንድ አገር ዜጋ ሊሆን ይችላል ። ይህ መሠረታዊ ሥርዓት ልጆች የትም ቦታ ይውለዱ፣ ዜግነታቸው ግን የሚወሰነው በወላጆቻቸው ዜግነት ነው የሚል አቋም አለው። ይህም የደም ትክክለኛነት ጽንሰ ሐሳብ ተብሎ ይጠራል ።



ስእል 1.10 አባት እና እናት ከአራስ ልጃቸው ጋር

ለ/ በሕጋዊ መንገድ የሚገኝ ዜግነት፡ በሕጋዊ መንገድ የሚገኝ ዜግነት አንድ የውጭ አገር ዜጋ ለመሆን ብቁ የሚያደርግ ሕጋዊ ሂደት ነው ። በሕጋዊነት ዜጋ ለመሆን የሚፈልግ ሰው በራሱ ፍቃድ ማመልከቻውን ሞልቶ በሕጋዊነት የዜግነት ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። ስለዚህ የአንድ አገር ዜግነት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሀገሪቱን ህጋዊ መስፈርት ማሟላት አለበት። ዜግነት በሕጋዊ መንገድ ለማግኘት የተለያዩ ዘዴዎች ቢኖሩም ዋና ዋናዎቹ ጋብቻ እና ጉዲፈቻ ናቸው።

1.ዜግነት በጋብቻ - ዜግነት በጋብቻ የአንድ አገር ዜጋ ለሚያገባ የውጭ አገር ዜጋ የሚሰጥ የዜግነት አይነት ነው። የአንድ ሀገር ዜጋ የሆነ ሰው ከሌላ ሀገር ዜጋ ጋር ከተጋቡ በኋላ የዚያ ሀገር ዜግነት ለማግኘት በማመልከቻ ሲያቀርብ ሕጋዊ ዜግነት ሊሰጣቸው ይችላል ማለት ነው።



ስእል 1.11 ሕጋዊ ዜግነት በጋብቻ

2. **ዜግነት በጉዲፈቻ፡-** ሕጋዊ ወላጆች ለመሆን የተዘጋጁ ባልና ሚስት ወይም ግለሰብ በሌላ አገር የተወለደውን ልጅ በጉዲፈቻ ሊያሳድጉትና ዜጋ ሊያደርጉት ይችላሉ። ይሁን እንጂ ይህ ከመደረጉ በፊት አንዳንድ መሟላት ያለባቸዉ ጉዳዮች አሉ። እነዚህም መመዘኛዎች፤-

- ወላጆቹ (ባልና ሚስት ወይም ግለሰብ) የአንድ ሀገር ቋሚ ዜጎች መሆን አለባቸው።
- ለጉዲፈቻ የሚወሰደው ልጅ ከ18 ዓመት በታች መሆን አለበት፤ እና
- ህጻኑ ጉዲፈቻነት የተቀበለበት ሀገር ቋሚ ዜጋ መሆን አለበት።



ስእል 1.12 በጉዲፈቻ የተወሰደ ልጅ

የቡድን ሥራ

1. ዜግነት ማግኘት የሚቻልባቸውን የተለያዩ መንገዶች መዘርዘር ትችላላችሁ?
2. በውልደት እና በሕጋዊ ዜግነት መካከል ያለው ዋና ልዩነት ምንድን ነው?

1.4.2 ዜግነት ማጣት የሚቻልባቸው መንገዶች

የግንዛቤ ጥያቄ፡-

አንድ ሰው ዜግነቱን እንዴት ሊያጣ ይችላል?

ዜግነት በተለያዩ መንገዶች ሊገኝ እንደሚችል ሁሉ፣ በተለያዩ መንገዶችም ሊነጠቅ ወይም ሊታጣ ይችላል። አንድ ሰው ዜግነቱን አጣ ማለት የሀገሪቱ ህጋዊ ዜጋ ሆኖ መቀጠል እንደማይችል ያመለክታል። ይህ የሚያሳየው የምትኖርበት ሀገር ዜግነት ከከለከለህ ዜግነት አጥተሃል ማለት ነዉ። ዜግነት የማጣት ሂደት እንደ ዜግነት የማግኘት ሂደት ሁሉ በየሀገሮቹ ሕግ ላይ የተመሠረተ ይሆናል። ዜግነት በሁለት መንገድ ሊወሰደ ወይም ሊመለስ ይችላል። እነሱም፤-

1. ዜግነትን በፈቃደኝነት መመለስ

ይህ አንድ ሰው አሰቦበት በራሱ ጊዜ በፈቃደኝነት ዜግነቱን የሚመልሰበት ሂደት ነው። አንድ ሰው በራሱ ውሳኔ በፈቃደኝነት ዜግነቱን ማንሳት ይችላል ማለት

ነው። ዜግነቱን በፈቃደኝነት ማንሳት ወይም መመለስ የሚፈልግ ሰው የሀገቱን ሕጋዊ አሰራር ተከትሎ በሕጋዊ መንገድ ዜግነቱን መመለስ ይችላል።



የቡድን ውይይት

የሚከተለውን ሀሳብ ሁለት ሁለት በመሆን ተወያይታችሁ ለክፍል አቅርቡ

አንድ ሰው በምን ምክንያት ዜግነቱን በፈቃደኝነት ሊመልስ እንደሚችል የደረሳችሁበትን ሀሳብ በቡድን ተወካያችሁ አማካኝነት ለክፍል አቅርቡ

ዜግነትን ያለፈቃደኝነት መነጠቅ

እያንዳንዱ ሀገር ዜግነትን የሚቆጣጠርበት የራሱ ደንቦች አሉት። አንድ ዜጋ የተወሰኑ መስፈርቶችን የማይከተል/የማያሟላ ከሆነ የዜግነት መብቱ ሊሰረዝ ይችላል። ይህ በተለያዩ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል ። ይሁን እንጂ የአንድን ሰው ዜግነት ለመንጠቅ በፍጥነት ወይም ወዲያውኑ የሚከናወን ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም የተለያዩ ተከታታይ እርምጃዎችን ማለፍ አለበት። ዜግነትን ሊያሰነጥቁ የሚያስችሉ መስፈርቶች ከሀገር ሀገር ልዩነት ቢኖራቸውም ከዚህ በታች ያሉትን ምሳሌ መውሰድ ይቻላል።

- ☞ የሀገርን ምስጢር ለውጭ ጠላት አሳልፎ መስጠት
- ☞ ከውጭ ጠላት ጋር ተባብሮ ሀገር መውጋት
- ☞ በፍርድ ቤት በሕጋዊ መንገድ ዜግነቱን በመሰረዝ ሊሆን ይችላል።

1.5 በኢትዮጵያ የዜግነት ህግ መስፈርቶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡-

- ☞ በኢትዮጵያ ዜግነት የማግኘትና የማጣት መንገዶችን ትገልጻለህ/ጫለሽ፤
- ☞ የሌላ ሀገር ዜግነት ያለው ሰው የኢትዮጵያን ዜግነት በሕጋዊ መንገድ ሊያስገኙለት የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ታሰረዳለህ/ጃለሽ፤
- ☞ በኢትዮጵያ ዜግነትን ሊያሰነጥቁ ወይም ሊያሳጡ የሚያስችሉ መንገዶችን ትለያለህ/ሽ።



የግንዛቤ ጥያቄ፡-

ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነህ/ሽ ? አዎን ብለህ ከመለስክ/ሽ እንዴት አገኘህ/ሽ?

ኢትዮጵያ የራሷ የዜግነት ሕግ ካላቸው ሀገሮች አንዷ ናት። ኢትዮጵያ በ1930 ዓ.ም የመጀመሪያውን የጽሁፍ የዜግነት ሕግ በሥራ ላይ አዋለች። ይህ ከመሆኑ በፊት ዜግነት በኢትዮጵያ ውስጥ በአብዛኛው የሚታወቀው በባሕላዊ መንገድ ነበር። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በ1995 በሥራ ላይ የዋለው ስለ ዜግነት አንዳንድ መሠረታዊ መርሆዎችን በማጸደቅ ነው። በዚሁ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 6 መሰረት ከባልና ሚስት አንዱ ወይም ሁለቱም ኢትዮጵያዊ ከሆኑ የሚወለዱ ልጆች ሁሉ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ናቸው።

በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት የኢትዮጵያ ዜግነት መብትን በመወለድ ወይም በደም ላይ በመመስረት አጽድቋል። በሕጋዊነት የኢትዮጵያ ዜግነትን ለማግኘት አጠቃላይ አዋጅም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት ውስጥ ተካቷል። ከዚህም በላይ በኢትዮጵያ ዜግነት አዋጅ ቁጥር 378/2003 መሰረት በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ዜግነት የሚወረሰው በዘር በኩል ነው። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ዜግነት አዋጅ ቁጥር 378/2003 መሰረት በትውልድ ቦታ ለሚገኝ የዜግነት መብት ቦታ የለውም። ስለዘህ ይህ አዋጅ ኢትዮጵያ በሕጋዊ መንገድ ለምትሰጠው ዜግነት ከዘህ በታች የተጠቀሱትን መስፈርቶች ኣሟልቶ መገኘት አለበት። የውጭ አገር ዜጋ ሆኖ የኢትዮጵያ ዜግነት ማግኘት የሚፈልግ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች የማሟላት ግዴታ አለበት

ሀ. የኢትዮጵያ ዜግነት ሕግ በሚጠይቀው ፅድሜ ላይ መድረስ፤

ለ. የዜግነት ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት ቢያንስ ለአራት ዓመታት በኢትዮጵያ የኖረ፤

ሐ. በየትኛውም የሀገሪቱ ብሔሮች/ብሔረሰቦች ቋንቋዎች በአንዱ መግባባት መቻል፤

መ. እራሱንና ቤተሰቡን ለማስተዳደር በቂና ህጋዊ የገቢ ምንጭ ያለው፤

ሰ. መልካም ባህሪ ያለው ሰው መሆን፤

ረ. ምንም የወንጀል መዝገብ የለላቸው፤

ሠ. የመጀመርያ ዜግነቱን መመለሱንና የሌላ ሀገር ዜግነት አለመኖሩን ማሰረጃ ማቅረብ ወይም ሀገር አልባ ሰው መሆኑን ማሳየት መቻል፤ እና

ሸ. በአዋጁ አንቀፅ 12 ላይ የተገለጸውን የታማኝነት ቃለ መሐላ መፈጸም ይጠበቅበታል።

በተጨማሪም ለሀገሪቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረጉ የውጭ ዜጎች እውቅና ለመስጠት የሚያስችል በልዩ ሁኔታ የኢትዮጵያ የክብር ዜግነት እንዲያገኙ ይፈቀዳል። በዚህ ምክንያት፣ ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ምንም ይሁኑ ምን ለኢትዮጵያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉ የውጭ ሀገር ዜጎች የኢትዮጵያ የክብር ዜግነት በህጋዊ መንገድ ሊሰጥ ይችላል ማለት ነው።



የፕሮጀክት ሥራ

በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ ሀገር ዜጋ ሆኖ ለሀገሪቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ የኢትዮጵያ የክብር ዜግነት የተሰጠውን ሰው ታውቃላችሁ? ቤተሰብና መምህራንን በመጠየቅ ያገኘኸውን/ሽውን መረጃ ለክፍልህ/ሽ ተማሪዎች አቅርብ/ቢ።

በሌላ መንገድ ደግሞ የኢትዮጵያ ዜግነት ማጣት የሚቻልባቸው መንገዶች በአዋጅ ቁጥር 378/2003 ስር ተገልጸል። በዜግነት አዋጁ መሰረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ዜግነቱን በፍቃደኝነት ካለወጠ ሌላ ዜግነት ካላገኘ በስተቀር በመንግስት ውሳኔ የኢትዮጵያ ዜግነቱን ሊገፈፍ አይችልም።

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 33(1) መሠረት ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ ከራሱ ፍላጎት እና ምርጫ ውጪ የኢትዮጵያ ዜግነቱን ሊገፈፍ አይችልም። ይህም ማለት በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት

ሳያስፈቅዱ የአንድን ሰው ዜግነት መንሳት ወይም መንጠቅ አይፈቀድም ማለት ነው።

 **መልመጃ-1 ቀጥሎ ያለዉን ጥያቄ በቡድን በቡድን ተወያዩበት፡-**

አንድ ከኢትዮጵያዊ እናትና በአባቱ አሜሪካዊ ዜግነት ካላቸዉ ወላጆች የተገኘ ህጻን በፈረንሳይ ሀገር ቢወለድ ዜግነቱ የየት አገር ሊሆን ይችላል? የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ብቁ ነዉ? እንዴት?

የምዕራፍ ማጠቃለያ

ዜጋ ማለት በአንድ ሀገር ህግ መሰረት የተወሰነ መብትና ግዴታ ያለው ሰው ነው። ዜጎች የተወሰኑ መብቶችና ነላፍነቶች ይሰጣቸዋል። ዜጎች ሃሳብን የመግለፅ፣ በህግ የመጠበቅ እና ሕጉን በመታዘዝና ግብር መክፈል የመሳሰሉት ሃላፊነቶች አለባቸዉ።ዜግነት የአንድ ሀገር ማህብረሰብ ሙሉ አባል መሆን ነው።ስለዚህ ዜግነት የህግ ዕውቅናና የአንድን ሰው ማንነት ማረጋገጫን ያሳያል ማለት ነዉ።

መልካም ዜጋ ሌሎችን የሚያከብር፣ የሚረዳና ስለ ሌሎች ማሰብ፣ የሌሎችን አስተያየት ማዳመጥ፣ ራሳቸውን መርዳት የማይችሉትን ማገዘ፣ ከሌሎች የኅብረተሰብ አባላት ጋር ተስማምተው የሚኖርና ለመማር ምንጊዜም ዝግጁ የሆኑ ሰዎችን ያመላክታል። ተማሪዎች ጥሩ ዜጋ የሚተገብረዉንና ከለሎች ሰዎች ጋር የጋራ መግባባት እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይማራሉ። በዚህም ምክንያት ትምህርት ቤትና ማህበረሰቦችን በአንድነት እንድሠሩ ማድረግ የጥሩ ዜጋ ባህርይን ማሳደግ አለባችሁ።

ዜግነት የአንድ አገር አባል ሆኖ በመመዝገብ የሚገኝ ህጋዊ መብት ነው።ማንኛውም ሰው የሀገሪቱን ህጋዊ ሁኔታዎች ካሟላ የሀገር አባል መሆን ይችላል። እንደ አጠቃላይ ደንብ፣ ዓለም አቀፍ ሕግ ዜጎቹ እነማን እንደሆኑ ለመወሰን ለእያንዳንዱ ሀገር ይተዋል፤ በዚህ መሠለት ዜግነት በተለያዩ ሀገራት ያሉ ህጎች የዜግነት መብት ማግኘትን እና ማጣትን በተለያዩ መንገዶች ይይዙታል። ኢትዮጵያ በ1930 ዓ.ም.የመጀመሪያውን የጽሁፍ የዜግነት ህግ ሥራ ላይ አዋለች።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በ1995 በሥራ ላይ የዋለዉ ስለ ዜግነት አንዳንድ መሠረታዊ መርሆዎችን በማጸደቅ ነዉ።በዚሁ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 6 መሰረት ሁለቱም ወይም የኢትዮጵያ ወላጆች ያሉት ማንኛውም ግለሰብ የኢትዮጵያ ዜጋ ነው። የኢትዮጵያን ዜግነት የማግኘት መብት በዘር ሐረግ ወይም በደም የመውረሰ ጽንሰ-ሀሳብ ነዉ።

የቁልፍ ቃላቶች ፈች

ዜጋ፡-የአንድ ሀገር ሙሉ አባል ሆኖ በህግ መሰረት የተወሰነ መብትና ግዴታ ያለው ሰው ነው።

ዜግነት፡- የአንድ ሀገር ሙሉ አባል መሆን

ዜግነት በህግ፡- ሀገራት ዜግነት የምሰጡበት እና የምወሰዱበት የህግ መስፈርት

ህገ መንግስት፡- የአንድ ሀገር የበላይ ህግ

የሀገር ፍቅር ስሜት፡- ለአገሩ ጥቅም መስዋእትነት ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ ዜጋ

ነላፍነት ፡- አንድ ሰዉ ለምሠራ ሥራ ሁሉ ተጠያቅነትን መዉሰድ

የምዕራፍ የክለሳ ጥያቄዎች

ክፍል 1፤- የሚከተሉትን ጥያቀዎች ትክክል ከሆነ እዉነት ትክክል ካልሆነ ውሸት በማለት መልሰ።

1) ዜጋ የተወሰኑ መብቶች ቢኖሩትም ምንም ግዴታ የሌለበት ሰው ነው።

2) ጥሩ ዜጋ ለመሆን ሃላፊነት የጎደለው መሆን አለበት።

3) ሁሉም ሀገራት ዜግነት በመስጠትና በዉሰድ ረገድ ተመሳሳይ አሠራሮችን ይከተላሉ።

ክፍል 2፦ ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ለእያንዳንዱ አራት ምርጫ ቀርቦዋል ። በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ትክክለኛዉን መልሰ ምረጥ ።

1) ስለ ዜግነት ከሚከተሉት መካከል የትኛው ትክክል ነው?

ሀ) በሕግ ላይ የተመሠረተ ነው

ለ) መብት እና ኃላፊነት የሚሰማው የአንድ ሀገር ሙሉ አባል መሆንን ያመለክታል

ሐ) ዜጋ የዜግነት ማዕረግ የያዘ ሰው ነው

መ) ከላይ የተጠቀሱት ሁሉ

2) የመልካም ዜጋ ገጽታ ያልሆነ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መካከል የትኛው ነው?

ሀ) ማንኛውንም ጥፋት ማጋለጥ

ለ) ለአገሩ ጥቅም ሲል መስዋዕትነት ለመክፈል ፈቃደኛ የሆነ

ሐ) ለሌሎች አክብሮት የማያሳይ

መ) ዴሞክራሲያዊ መርሆች የምያከበር

3) በተለያዩ ማህበረሰብ ውስጥ ---------- ለሰላማዊ አብሮ መኖር አስፈላጊ ነው?

ሀ) አለመግባባት

ለ) መቻቻል

ሐ) መበዳደል

መ) ችላ ማለት

ክፍል 3 - በአምድ 'ሀ' ሥር የተዘረዘሩትን ዜግነት ማግኛ መንገዶች በ 'ለ' አምድ ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዳቸዉ

	ሀ		ለ
1	የአፈር መብት	ሀ	ዜግነት በጋብቻ
2	የደም መብት	ለ	ዜግነት በጉዲፈቻ
3	የአንድን አገር ዜጋ የሚያገባና ዜግነት የሚያገኝ የውጭ አገር ዜጋ	ሐ	ዜግነት በውልደት
		መ	የዜግነት ማጣት
4	ሕጋዊ ወላጆች እንደሆኑ ተደርጎ የተሰጠውን ግለሰብ ዜግነት ማግኛ	ሰ	ዜግነት በዘር ሐረግ

ክፍል 4፤- አጭር መልስ:: ለሚከተለው ጥያቄ ተገብውን መልስ ጻፍ ::

1) ጥሩ ዜጋ አስፈላጊ የሆነበትን ቢያንስ አራት ምክንያቶች ዘርዝር?

ምዕራፍ 2

መንግስት እና መንግስት አስተዳደር

መግቢያ

በምዕራፍ አንድ ስለ ዜግነት ፅንሰ ሃሳብ እና የዜግንነት መርሆዎች እንዲሁም ዜግነትን እንዴት ማግኘት እና ማጣት እንደሚቻል አውቀሃል/ሻል። በተጨማሪም የኢትዮጵያን የዜግነት ህጎች ተምረሃል/ሻል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ስለ ሀገረ መንግስት ፅንሰ ሀሳብ እና የመንግስት መሰረታዊ ምሶሶዎች ትማራለህ/ሽ፡ ፡ በተጨማሪም የመንግስትን ትርጉም፣ተግባር እና ቅርፅ/ይዘት ትማራለህ/ሪያለሽ። በመጨረሻም በመንግስት እና መንግስት አስተዳደር መካከል ያለቀውን ተመሳሳይነት እና ልዩነት ትማራለህ/ሪያለሽ።

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

- የመንግስትን ጽንሰ ሃሳብ መግለፅ፣
- የመንግስትን አካላት መለየት፣
- የመንግስት ተግባራትን መዘርዘር፣
- የመንግስት ቅርጾች መለየት፣
- በመንግስት እና በመንግስት አስተደደር መካከል ያለውን ልዩነት ማብራራት ይሆናል።

2.1 የመንግስት ፅንሰ ሀሳብ

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፤

- ☞ የመንግስት ምንነትን ትገልፃለህ/ጫለሽ፣
- ☞ የመንግስትን ምሳሌ ትሰጣለህ/ጫለሽ፣
- ☞ ኢትዮጵያ ሀገር መሆኗን እና አለመሆኗን ትላያለህ/ሽ።



መንግስት ማለት ምን ማለት ነው?

መንግስት ማለት በፖለቲካ የተደራጀ ማህበረሰብ ሆኖ በአንድ የመንግስት አስተዳደር ስርዓት ስር የሚኖር ማለት ነው። በዚህም ምክንያት መንግስት ማለት ይብዛም ይነስ በአንድ የተወሰነ ግዛት ውስጥ በቋሚነት የሚኖሩ፣ የራሳቸው አስተዳደር ያላቸው እና ከውጭ ጣልቃ ገብነት ነፃ የሆኑ የሰዎች ስብስብ ነው። የመንግስት ህልውና የሚፈለገው ከመሰረታዊ የህይወት ፍላጎቶች በመነሳቱ ነው። መንግስት የመመስረት አላማ ህጎችን በመጠቀም በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት ነው።



የቡድን ሥራ

የሚከተለውን ጥያቄ በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

ዓለም አቀፋዊ እና የአፍሪካን ሀገራት ዘርዝሩ።



ምስል 2.1 አለም አቀፋዊ የሀገራት ካርታ


2.2 መሰረታዊ የመንግስት ምሶሶዎች/ አካላት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፤

- የመንግስት ምሶሶዎች ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤
- የመንግስት መኖር ለሀገር መሠረት መሆኑን ትገልፃለህ/ጫለሽ፣
- ከመንግስት ምሶሶዎች ዉስጥ አንድ ብቀር ምን እንደምሆን ትገምታለህ/ቻለሽ፡፡

መሰረታዊ የመንግስት ምሶሶዎች ምን ምን ናቸው?

ከላይ በተገለፀው የመንግስት ፍቺ መሰረት የመንግስት መሰረታዊ ምሶሶዎች ማለትም ህዝብ፣ ግዛት፣ መንግስት እና ሉዓላዊነትን በማቀፍ ይታወቃል፡፡



ምስል 2.2 የመንግስት ምሶሶዎች

2.2.1 ህዝብ

የቡድን ውይይት

የሚቀጥለውን ጥያቄ በቡድን በመወያየት ግለፁ፡፡

ኢትዮጵያን የብዙህን ሀገር ያሰኛት ምንድን ነዉ?

ህዝብ የመንግስት ወሳኝ አካል ነው፡፡ መንግስት ለመመስረት የሚያስፈልገው የህዝብ ብዛት ቋሚ አይደለም፡፡ የአንድ መንግስት ህዝብ የአንድ ዘር፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋ እና ባህል መሆን አስገዳጅ አይደለም፡፡



ምስል 2.3 የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዘሃነት

2.2.2 ግዛት

የክፍል ሥራ

ኢትዮጵያን በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅና በምዕራብ የሚያዋስኗት አገሮች የትኞቹ ናቸው? በግል በመሥራት ለክፍል አቅርብ/ቢ።

የትኛውም መንግስት ያለ ቋሚ ግዛት ሊኖር አይችልም። ሰዎች በማህበራዊ እና በፖለቲካ ለመደራጀት ግዛት ያስፈልጋል። የመንግስት ግዛት መጠን ልክ እንደ ህዝቡ ቁጥር ሊወሰን አይችልም። ለዚህም እንደ ቫቲካን ሲቲ ያለች ትንሽ እና እንደ ሩሲያ ያለ ትልቅ ግዛት ማየት እንችላለን። ሀገር በግዛቱ ውስጥ የሰዎችን፣

የገንዘብ እና የሸቀጦችን ፍሰት መቆጣጠር ይችላል። ስለዚህ አንድ የተወሰነ ግዛት በአለም አቀፍ ህግ የሀገር አስፈላጊ ምሶሶ ተደርጎ ይወሰዳል።

ሀገራችን ኢትዮጵያም የታወቀ የግዛት ድንበር ካላቸው ሀገራት መካከል አንዷ ናት። ኢትዮጵያ በሰሜን ከኤርትራ፣ በሰሜን ምስራቅ ከጅቡቲ፣ በምስራቅ ከሶማሊያ፣ በደቡብ ከኬንያ፣ በምዕራብ ከደቡብ ሱዳን እና ከሱዳን ትዋሰናለች።



ምስል: 2. 4 ኢትዮጵያን የሚያዋስኗት ሀገራት

2.2.3 የመንግሥት አስተደደር

የግንዛቤ ጥያቄ

የመንግሥት አስተደደር ማለት ምን ማለት ነው?

የመንግሥት አስተዳደር ሦስተኛው እና በጣም አስፈላጊው የመንግስት አካል ነው። ያለ መንግሥት አስተዳደር የተረጋጋ መንግስት ሊኖር አይችልም።

የመንግሥት አስተዳደር የሀገር የስራ ክንድ እንዲሁም ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ነው። የመንግሥት አስተዳደር የሀገርን ስልጣን እና ተግባራትን የማከናወን ሃላፊነት አለበት። እንዲሁም መንግሥት የመንግስትን ሕጎች ያወጣል፤ ይፈጽማል፤ይተረጉማል።

2.2.4 ሉዓላዊነት

የቡድን ውይይት

የመንግስት ሉዓላዊነትን በተመለከተ በቡድን በመዋያያት ለክፍል አቅርቡ።

ሉዓላዊነት በተለምዶ ውስጣዊ እና ውጫዊ በመባል በሁለት ይከፈላል። የውስጥ ሉዓላዊነት በግዛት ሥልጣን ውስጥ ያለውን ሉዓላዊነት ያመለክታል። የውስጥ ሉዓላዊነት ያለው መንግስት በህብረተሰቡ ላይ ትእዛዝን የመስጠት ስልጣን እና አቅም አለው። በአንድ መንግስት እና በሌሎች ሉዓላዊ ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት የውጭ ሉዓላዊነት ተብሎ ይጠራል። የአንድ መንግስት የውጭ ሉዓላዊነት ከሌሎች ሀገራት ጋር ገለልተኛ ግንኙነት እንድትፈጥር ያስችላታል። ይህ በግለሰቦችም ሆነ በክልሎች የውጭ ፍላጎቶች ሁሉ ላይ የመንግስት የበላይነት ነው። ስለዚህ ሉዓላዊነት በጣም አስፈላጊ የመንግስት ምሶሶ ተደርጎ ይወሰዳል። ኢትዮጵያ የራሷ ባንዲራ እና ብሔራዊ መዝሙር ያላት ሉዓላዊት ሀገር ነች።

የጉዳይ ጥናት

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው በአለም አቀፍ ህግ ብቻ ሳይሆን ብሔር ብሔረሰቦች በከፈሉት መስዋእትነት ነው። የኢትዮጵያ ጀግኖች የሀገራችንን ሉዓላዊነት ለማደፍረስ የሞከሩትን የውጭ ወራሪዎች በታሪክ በርካታ ጦርነቶች አሸንፈዋል። በዚህም የተነሳ ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት የነጻነት በዓልን ስያከብሩ ኢትዮጵያ ግን ነፃነቷን አስጠብቃ የድል በዓልን ታከብራለች።

የቡድን ውይይት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመወያያት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

1. **የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ የተሰውትን ቢያንስ ሶስት ጀግኖችን ጥቀሱ?**

2. የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በማስከበር ረገድ የወጣቱ ትውልድ ዋና ኃላፊነቶች ምን ምን ናቸው?

2.3. የመንግስትአስተደደር ተግባራት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፤

- የመንግስት አስተደደር ተግባራትን ትገልፃለህ/ጫለሽ፣
- የዴሞክራሲያዊ መንግስት አስፈላጊነት ትናገራለህ/ሪያለሽ፣
- ዴሞክራሲያዊ መንግስት የዜጎችን ፍላጎት ለማሟላት የሚያዳርገዉን ተግባራት ትዘረዝራለህ/ሽ።



የግንዛቤ ጥያቄ

የመንግስትአስተደደር ተግባራት ምን ምን ናቸው?

የመንግስት አስተደደር መንግስትን እንደሚመራ አካል የሚጠበቅበት የተለያዩ ተግባራት አሉት። እነዚህን ተግባራት ለመወጣት አብዛኛውን የሀገሪቱ ዜጎች የሚገዛ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅበታል። ምንም እንኳን የመንግሥት ተግባራት አንደ የሀገሩ ቢለያይም፣ የተለመዱት የሚከተሉት ናቸው።

- ህግ እና ስርዓትን ማስጠበቅ
- የህዝብ አገልግሎቶችን መስጠት
- ብሔራዊ ደህንነትን መጠበቅ
- ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎችን ማድረግ ናቸው።

እነዚህን ኃላፊነቶች ለመወጣት መንግሥት በሁሉም ዜጎቹ ላይ አስገዳጅነት ያለው ውሳኔ መስጠት አለበት:: ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዱን ከላይ የተጠቀሱትን የመንግስት አስተደደር ተግባራት እንደሚከተለው ይቀርባል።

2.3.1 ህግ እና ስርዓትን ማስጠበቅ

የቡድን ውይይት፤

ዴሞክራሲያዊ መንግስት ህግ እና ስርዓትን በማስጠበቅ ረገድ ያለውን ሚና በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

የዴሞክራሲያዊ መንግስት አስተደደር አንዱ እና ዋነኛው ተግባር ህግ እና ስርዓትን ማስከበር ነው፡፡ መንግስታት ይህንን የሚፈፀሙት የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች እንቅስቃሴ የሚቆጣጠሩ ህጎች በማውጣት ነው:: የመንግስት አስተደደር ህጎች የህዝብን ሰላም፣ መብት፣ንብረት እና ህይወት ለመጠበቅ ይረዳሉ፡፡ በተጨማሪም የዜጎች አለመግባባቶችን በጊዜና በስርዓት ለመፍታት የሚረዱ እንደ ፍርድ ቤቶች ያሉ የአሰራር ዘዴዎችን በማዘጋጀት የግለሰቦችን ግጭቶች ለመቆጣጠር ገደቦችን ይጥላሉ፡፡ እንዲሁም የእርስ በርስ ግጭትን ለመቆጣጠር መንግስት ግለሰቦች ማድረግ ያለባቸው እና ማድረግ የሌለባቸው ጉዳዮች ላይ ገደቦችን ይጥላል፡፡



ምስል:2.5ፖሊስ ህግ እና ስርዓትን ሲያስከብር

2.3.2 የህዝብ አገልግሎቶችን መስጠት

የግንዛቤ ጥያቄ

የመንግስት አስተዳደር ለህዝብ ከሚያቀርባቸዉ አገልግሎቶች ጥቅቶቹን ጥቀሱ፡፡

የመንግስት አስተዳደር ሌላኛው ተግባር የማህበረሰብን ህይወት የሚያጎለብቱ አስፈላጊ የህዝብ አገልግሎቶችን መስጠት ነው፡፡ የመንግስት አስተዳደር በድንበሩ ውስጥ ለሚኖሩት ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ለማገልገል ኃላፊነት አለው፡፡ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትም ለህዝቡ ድጋፍ እንድያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ የህዝብ አገልግሎቶች ከመሠረታዊ ሰብአዊ መብቶች ጋር የተሳሰሩ ሆነው እንደ እሳት አደጋ መከላከያ፣ ህግን ማስከበር፣ የአካባቢ ጥበቃ፣የህዝብ መኖሪያ ቤት ፣ትምህርት፣ ጤና፣ መብራት እና የህዝብ ማመላለሻን ያካትታል፡፡



ምስል2.6 የህዝብ አገልግሎት መስጠት

2.3.3 ብሔራዊ ደህንነትን መጠበቅ

የቡድን ሥራ

በቡድን በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል አቅርቡ፡፡

ኢትዮጵያ በውጪ ወራሪ እንዳትወረር ማን ይጠብቃታል?

ከመንግስት አስተዳደር ዋና ተግባራት አንዱ የዜጎችን ደህንነት ማስጠበቅ ነው፡፡ መንግስታት ከውጭም ሆነ ከውስጥ ስጋቶች ሊጠበቁ ይገባል፡፡ በመሆኑም የብሔራዊ ደኅንነት ጉዳይ ለእያንዳንዱ ሉዓላዊ መንግስት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ተግባር ለመፈፀም የመንግስት አስተዳደር ወታደራዊ፣ ትጥቅ እና ኦፕሬሽን እንዲሁም የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎችን ያካተቱ የመንግስት መከላከያ ሃይሎችን ያቋቁማል፡፡ መንግስታት ብሄራዊ ደህንነትን ከማረጋገጥ በተጨማሪ ከውጭ ሀገራት ጋር ጥሩ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡




ምስል2.7 ብሔራዊ ደህንነትን መጠበቅ

2.3.4 . ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎችን ማድረግ

የግንዛቤ ጥያቄ

ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎችን ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው?

የትኛውም አገር ብቻውን የዜጎቹን ፍላጎት ሊያሟላ አይችልም። የመንግስት አስተዳደር የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር፣ ንግድን በማበረታታት እና የተፈጥሮ ሃብት ልማትን በመቆጣጠር የኢኮኖሚ እድገት እና መረጋጋትን ለማስፈን ይሰራል። በተጨማሪም መንግሥት የአገሪቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚቆጣጠሩ ደንቦችን ያወጣል። በዚህም ምክንያት ኢኮኖሚያዊ ውሳኔዎችን ማድረግ ሌላው የመንግስት አስተዳደር አስፈላጊ ተግባር ነው።



ምስል: 2.8 የሕዳሴ ግድብ

2.4. የመንግስትአስተዳደር አይነቶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛዉ የመማር ብቃቶች፤

- መሠራታዊ የመንግስት አስተዳዳር ቅርጾች/አይነቶችን ትለያለህ/ሽ፣
- በንጉሳዊ አገዛዝ እና አሪስቶክራሲ መካካል ያለውን ልዩነት ትዘራዝራለህ/ሽ፣
- የዴሞክራሲያዊ መንግስት መሠረታዊ መርሆችን ትገልፃለህ/ጫለሽ።



የግንዛቤ ጥያቄ

የመንግስት አስተዳዳር አይነቶችን ጥቀስ/ሽ፡፡

መንግስታት በተለያዩ መልኮች ሊዋቀሩ ይችላሉ፡፡ የመንግስት ቅርጾች/አይነቶች ሉዓላዊ ስልጣንን በሚጨብጡ ሰዎች ቁጥር ላይ በመመስረት እንደሚከተለው ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

2.4.1 ንጉሳዊ አገዛዝ



የክፍል ሥራ

የንጉሳዊ አገዛዝ ስርዓት ላይ በቡድን ከተዋያያቸሁ በኋላ ለክፍሉ ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

በንጉሳዊ አገዛዝ ስርዓት ከሚተዳዳሩ ሀገራት መካከል ጥቂት ምሳሌዎችን በማንሳት አብራሩ ፡፡

በንጉሳዊ አገዛዝ ሉዓላዊ ሥልጣን በአንድ ግለሰብ ማለትም በንጉሠ ነገሥቱ የተያዘ ሆኖ – ሥልጣን በዘር ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍበት የመንግሥት ዓይነት ነው፡፡ ንጉሳዊ አገዛዝ የሚመራው በንጉስ ወይም በንግስት ሊሆን ይችላል፡፡ ዙፋኑ ብዙውን ጊዜ ለታላቅ ወንድ ልጅ ወይም ለቅርብ የወንድ ዘር ይተላለፋል፡፡

2.4.2. አሪስቶክራሲ



የቤት ሥራ

የሚከተለውን ጥያቄ በግል በመስራት ለክፍል ተማሪዎች ግለፅ/ጭ፡፡

አሪስቶክራሲ ምን አይነት ስርዓት ነው፡፡

የአሪስቶክራሲ ስርአት ሌላኛው የመንግስትአስተዳዳር መዋቅር ሆኖ ጥቂት እና ለመግዛት ብቁ ናቸው ተብሎ በሚታሰቡ ቡድኖች የሚመራ ስርአት ነው፡፡ ይህ ስርአት በተማሩ እና በጥቂት ቡድኖች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

2.4.3. አምባገነንነት

የግንዛቤ ጥያቄ

አምባገነንነት ምን ዐይነት ሥርዓት ነው?

በአምባገነናዊ ስርዓት ሥልጣን ገደብ የሌለው ሆኖ/እና በአንድ ግለሰብ ወይም በጥቂት ቡድኖች እጅ መኖሩን ያሳያል። በዚህ ስርዓት ውስጥ ሥልጣን በሀይል ይጠበቃል። አብዛኞቹ አምባገነኖች በአውቶርታርያን ወይም በቶታሊታሪያን አገዛዝ ውስጥ ይታያሉ።



ሒትለር(1889-1945) ጀርመን ሞሶሎኒ (1883-1945) ጣሊያን

ምስል 2.9 የአምባገነኖች ምስል

2.4.4. ዲሞክራሲ

የግንዛቤ ጥያቄ

ዴሞክራሲያዊ ስርዓተ መንግስት አስተዳደር ማለት ምን ማለት ነው?

ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት ዜጎች በፖለቲካዊ ውሳኔዎች ውስጥ የሚሳተፉበት የመንግሥት ዓይነት ነው። ከሌሎች የመንግስት አካላት የሚለየው የዲሞክራሲ ባህሪያትን ተግባራዊ ማድረጉ ነው። በዴሞክራሲ ውስጥ ሁሉም ሰው ለማደግ እኩል እድል አለው ምክንያቱም መንግስት በዜጎች መካከል

እኩልነትን ለማምጣት ይጥራል. ዲሞክራሲ ባለበት ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ይካሄዳል። ሁሉም በድምጽ መስጫ እድሜ ላይ ያሉ ዜጎች ሀገሪቱ እንዴት እንደምትመራ የራሳቸውን አስተያየት ሊሰጡ እና በተወካዮቻቸው አማካኝነት ድምፃቸውን ማሰማት ይችላሉ። ይህ የደሞክራሲ መግቢያ ሀሳብ ብቻ ቢሆንም; ዝርዝሮች በሚቀጥለው ምዕራፍ ቀርበዋል.



ምስል 2.10 ማንዴላ (1918-2013) ደቡብ አፍሪካ)

2.5 መንግስት እና በመንግስት አስተዳዳር መካከል ያሉ ልዩነቶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፤

- በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካካል ያለውን ልዩነት ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፣
- የመንግስት አስተዳደር ከመንግስት አካል አንዱ መሆኑን ትገልፃለህ/ጫለሽ::



የግንዛቤ ጥያቄ

በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ያሉ ልዩነቶች ምን ይመስልሀል/ሻል ?

መንግስት እና የመንግስት አስተዳደር የሚሉት ቃላቶችን በተደጋጋሚ በተለዋዋጭነት ሰዎች ሲጠቀሙ ይስተዋላሉ፡፡ ይሁን እንጂ በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ልዩነቶች እንዳለ ሁሉ ተመሳሳይነትም ይኖራል፡፡አገሪቱን የሚያስተዳድር አካል የመንግሥት አስተዳደር በመባል ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ መንግስት ስንል መላውን የኢትዮጵያን ግዛት የሚያጠቃልል ማለታችን ነው፡፡ በአንፃሩ የኢትዮጵያን የመንግስት አስተዳደር ስንጠቅስ ሦስቱን የመንግስት አካላት ማለትም ህግ አውጪ፣ አስፈፃሚ እና የዳኝነት አካል ማለታችን ነው፡፡ የመንግሥት አስተዳደር ሁሉንም ባለሥልጣኖች እና ተግባራትን በመንግስት ስም ይመራል፡፡

በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ያሉት መሰረታዊ ልዩነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

I. የመንግስትአስተዳደር የመንግስት አካል ብቻ ነው፡፡

ቀደም ሲል መንግስት አራት አስፈላጊ ምሶሶዎችን እንዳቀፈ መገለፁ ይታዋሳል፡ ፡ እነሱም ህዝብ ፣ግዛት፣ የመንግስት አስተዳደር እና ሉዓላዊነት ናቸው፡፡ በመሆኑም የመንግስት አስተዳደር መንግስትን ወክሎ የሚሰራ የሀገር አካል ነው፡፡

II. መንግስት ረቂቅ ሲሆን የመንግሥት አስተዳደር ግን ተጨባጭ ነው፡

መንግስት የማይታይ ረቂቅ ፅንሰ-ሀሳብ ነው። በሌላ በኩል የመንግሥት አስተዳደር ተጨባጭ ነው። የመንግስት ስልጣንን ለመጠቀም የሚተባበሩ የሰዎች ስብስብ ተደርጎ ሊወሰድም ይችላል። መንግሥት በሕዝብ የተመረጡ ሰዎችን ያቀፈ ነው። ግልጽ የሆነ መዋቅር እና ቅርጽ አለው::

III. የመንግሥት አስተዳደር በተወሰነ ሕዝብ ብቻ የተደራጀ ነው

መንግስት መላውን ህዝብ ያጠቃልላል። በሌላ በኩል የመንግስት አስተዳደር የሚመሰረተው በህዝብ ተወካዮች ነው። የመንግስትአስተዳደር የህዝብ ተወካዮች ሆነው እንዲያገለግሉ ከተመረጡት ጥቂት ሰዎች ብቻ የተዋቀረ ነው።

IV. የመንግስት አባልነት ግዴታ ሲሆን የመንግስት አስተዳደር ግን አይደለም

የአንድ ሀገር ዜጎች ሁሉ የሀገሪቱ አባል ናቸው። ሁሉም ዜጎች ግን የመንግስት አስተዳደር አባል ላይሆኑ ይችላሉ። የመንግስት አባል መሆን ማለት የመንግስት አስተዳደር አባል መሆን ማለት አይደለም። ስለዚህ የመንግስት አባልነት ለሁሉም ዜጎች ግዴታ ሲሆን የመንግስት አስተዳደር አባልነት ግን ግዴታ አይደለም። ይህ ማለት ዜጎች በግልም ሆነ በፖለቲካ ፓርቲ ስም በመደራጀት በመንግስት አስተዳደር ውስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ። ይህ ደግሞ በዜጎች መልካም ፈቃድ ላይ የሚመሰረት እንጂ እንደ የመንግስት አባልነት አስገዳጅ አይደለም።

V. እያንዳንዱ መንግስት አንድ አይነት አስፈላጊ ምሶሶዎች አሉት ነገር ግን የመንግስትአስተዳደር አይነቶች እና ባህሪያት ከመንግስትመንግስትይለያያሉ።

እያንዳንዱ መንግስት እንደ ህዝብ፣ ግዛት፣ መንግስት እና ሉዓላዊነት ያሉ የጋራ

ባህሪያት አሉት። በሌላ በኩል መንግስታት እንደ ፓርላሜንታዊ፣ ፕሬዚዳንታዊ ወይም የሁለቱን ጥምረት የመሳሰሉ የተለያዩ ስርዓቶችን ሊሆኑ ይችላሉ። የመንግስት አስተዳደር በባህሪው ዴሞክራሲያዊ ፣ ንጉሳዊ፣ መካንንት ወይም አምባገነን ሊሆን ይችላል።

VI. መንግስት ቋሚ ነው የመንግሥት አስተዳደር ግን ጊዜያዊ ነው።

መንግስታዊ አስተዳደር ሁል ጊዜ ይመጣል ይሄዳል ። በፕሬዘዳንታዊ ምርጫ ወይም አብዮት እንኳን ሙሉ ለሙሉ የመንግስት አስተዳደር ለውጥ ሊያስከትል ይችላል። መንግስት ግን ሉዓላዊነቱን እስከ ተጠበቀ ድረስ በአንፃራዊነት ላልተወሰነ ጊዜ ይኖራል።

 **የፕሮጀክት ሥራ**

በመንግስት እና በመንግስት አስተዳደር መካከል ያሉ ልዩነቶችን በማስመልከት ሌሎች መምህራንን በመጠየቅ ለክፍል ተማሪዎች አቅርብ።

የመንግስት አስተዳደር የመንግስት አንድ አካል ነዉ ብለህ/ሽ ታስባለህ/ቢያሽ? እንደኤት?

የምዕራፉ ማጠቃለያ

መንግስት ማለት በፖለቲካ የተደራጀ ማህበረሰብ ሆኖ በአንድ የመንግስት አስተዳደር ስርዓት ስር የሚኖር ነው። ዘመናዊ መንግስት አራት መሰረታዊ ምሶሶዎችን ያቀፈ ነው። እነዚህም ህዝብ፣ ግዛት፣ መንግስት እና ሉዓላዊነት ናቸው። ዴሞክራሲያዊ መንግስት ህግ እና ስርዓትን የማስከበር ፣የሰዎች እና የንብረት ደህንነትን የማረጋገጥ ፣ኢኮኖሚውን የመምራት እና መንግስትን ከውጭ ስጋቶች የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት። በመሆኑም ለሰላም ህልውና የአንድ መንግስት ውጤታማ ተግባር ያስፈልጋል።

መንግስታት በተለያየ መልኩ ይዋቀራሉ። የተለያዩ የመንግስት አካላትን በግልፅ ለመረዳት ሉዓላዊ ስልጣን የሚይዙ ሰዎችን ቁጥር እንደ መስፈርት እንጠቀማለን። በውጤቱም፣ የመንግስት አይነቶች ሉዓላዊ ስልጣንን በሚጠቀሙ ሰዎች ቁጥር ላይ በመመስረት እንደ ንጉሳዊ አገዛዝ፣ መኳንንት፣ አምባገነንነት እና ዲሞክራሲ ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ።

መንግስት እና የመንግስትአስተዳደር የሚሉት ቃላት በተደጋጋሚ ቢለዋወጡም ተመሳሳይነት ያላቸው አይደሉም። በመንግስት እና በመንግሥትአስተዳደር መካከል ልዩነት ይኖራሉ። ዘመናዊ መንግስት አራት መሰረታዊ ምሶሶዎችን ያቀፈ ሲሆን ከነዚህም አንዱ የመንግስት አስተዳደር ነው። መንግስት መሰረታዊ ረቂቅ ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን የመንግስት አስተዳደር ግን ተጨባጭ እና የመንግስት ስልጣንን ለመጠቀም በጋራ የሚሰሩ የሰዎች ስብስብ ተብሎ ሊታሰብ ይችላል። በተጨማሪም ግዛቱ ከጠቅላላው ሕዝብ ጋር የተዋቀረ ሲሆን የመንግሥትአስተዳደር ግን የሕዝብ ተወካዮችን ያቀፈ ነው። በመንግስት ሁሉም ሰው እንደ ዜጋ ይቆጠራል። የግዛቱ አጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር ዜጎች ናቸው። የመንግስት አስተዳደር አባልነት ወዲያውኑ አይሰጥም። ማንም ሰው በግድ ወደ መንግስት አስተዳደር ሊገባ አይችልም። ከዚህም በላይ መንግስት ላልተወሰነ ጊዜ ይኖራል። ሉዓላዊነቱን እስካስጠበቀ ድረስ ላልተወሰነ ጊዜ ይቀጥላል።

የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

አሪስቶክራሲ በተማሩ እና በጥቂት ቡድኖች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ስርዓት ነዉ።

ዴሞክራሲ መሪዎች በዜጎች የሚመረጡበት የመንግስትአስተዳዳር አይነት ነው

አምባገነናዊ ስርዓት ገደብ የሌለው ሥልጣን ሆኖ በአንድ ግለሰብ ወይም በጥቂት ቡድኖች እጅ መኖሩን የሚያሳይ ነው።

ንጉሳዊ አገዛዝ ሥልጣን በዘር ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍበት የመንግሥት ዓይነት ነው።

መንግስት በፖለቲካ የተደራጀ ማህበረሰብ ሆኖ በአንድ የመንግስት አስተዳደር ስርዓት ስር የሚኖር ነው።

ህዝብ ህዝብ የመንግስት ወሳኝ አካል ነው።

ግዛት ሰዎች በማህበራዊ እና በፖለቲካ ለመደራጀት ግዛት ያስፈልጋል።

የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄ

ክፍል አንድ፡ የሚከተሉት ጥያቀዎች ትክክል ከሆኑ"እዉነት" ስህተት ከሆኑ ደግሞ "ሀሰት" በማለትመልስ/ሽ።

1. መንግስት ማለት በመንግስት አስተዳደር ሥልጣን ስር የሚንቀሳቀሰው በይፋ የተመሰረተ የፖ`ለቲካ ማህበረሰብ ነው።
2. የአንድ መንግስት ህዝብ ብዛት አንድ ዘር፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋ እና ባህል መሆን አለበት።
3. ያለ መንግስት አስተዳደር መንግስት ሊኖር አይችልም።
4. የመንግሥትአስተዳደር ከመንግስት በተለየ ላልተወሰነ ጊዜ ይኖራል።

ክፍል ሁለት፣ ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ/ጭ

1. ከሚከተሉት ውስጥ የመንግስት አስፈላጊ ምሶሶዎች ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ህዝብ
   ለ. መንግስት አስተዳደር
   ሐ. የፖ`ለቲካ ፓርቲ
   መ. ሉዓላዊነት

2. ሉዓላዊ ሥልጣን የበላይ ሆኖ ለመምራት ብቁ ናቸው ተብሎ በሚታሰበው የሕዝብ ስብስብ ውስጥ የሚገኝ የመንግሥት ዓይነት ነው።

   ሀ. ንጉሳዊ ስርዓት

   ለ. አሪስቶክራሲ

   ሐ. አምባገነን

   መ. ዴሞክራሲ

3. ከሚከተሉት ምርጫዎች ውስጥ መንግስትን በደንብ የሚገልጸው የትኛው ነው?

   ሀ) ከሰፊው ህዝብ የተገነባ

   ለ) አባልነት ወዲያውኑ አይሰጥም

   ሐ) ተጨባጭ ነው

   መ) በህዝብ ተወካዮች የተዋቀረ ነው.

ምዕራፍ 3

ዴሞክራሲ

መግቢያ

በምዕራፍ ሁለት ስለመንግስትና የመንግስት አስተዳደር ተምረሀል/ሻል። ይህ ምዕራፍ ደግሞ በዴሞክራሲ ላይ ያተኮረ ነው። የዴሞክራሲ ፅንሰ-ሀሳብ ከሰው ልጆች ዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር የተያያዘ ነው። ስለሆነም የዚህ ምዕራፍ አላማ የዴሞክራሲ ፅንሰ-ሀሳብ፤የዴሞክራሲ ዓይነቶችና ዴሞክራሲ የሚተገበርባቸውን ስልቶች መተንተን ይሆናል። በተጨማሪም ስለ ዴሞክራሲያዊ አመለካከቶችና ሀገር በቀል ዴሞክራሲያዊ እሴቶች ይዳሰሳሉ።

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

- የዴሞክራሲን ፅንሰ-ሀሳብ ማብራራት፤
- የዴሞክራሲ ዓይነቶችን መዘርዘር፤
- ዴሞክራሲን የመተግበሪያ መንገዶችን መለየት፤
- ሀገር በቀል ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን ማድነቅ፤
- የተለያዩ የዴሞክራሲ አመለካከቶችን መለየት ይሆናል።

3.1. የዴሞክራሲ ትርጉም


ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች:-

- የዴሞክራሲን ምንጭ ትገልጻለህ/ሚለሽ፤
- የዴሞክራሲን ትርጉም ትናገራለህ/ሪያለሽ፤
- የግለሰብ የበላይነትን ትገልጻለህ/ሚለሽ።

የግንዛቤ ጥያቄ

ዴሞክራሲ ማለት ምን ማለት ነው? ሃሳብህን/ሽን ለክፍሉተማሪዎች አካፍል/ይ፡

:



ምስል 3.2 የዴሞክራሲን ፅንሰ-ሀሳብ

ዴሞክራሲ የሚለው ቃል ከሁለት የግሪክ ቃላት ዴሞስ እና ክራቶስ የተገኘ ነው፡፡ ትርጉሙም ዴሞስ “ህዝብ” ሲሆን ክራቶስ ደግሞ “ማስተዳደር”ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ቃላት ተጣምረው ዴሞክራሲን ይፈጥራሉ፡፡ ትርጉሙም “የሕዝብ አስተዳደር” ማለት ነው፡፡

ዴሞክራሲ የአስተዳደር ስርአት ሆኖ ሕዝብ የስልጣን ባለቤት የሆነበትና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሀገር ጉዳይ ላይ ተሳታፊ የሚሆንበት የመንግሥት ሥርዓት ነው፡፡ በአጠቃላይ ዴሞክራሲ የሕዝብ፣ በሕዝብ እና ለሕዝብ የሆነ አስተዳደር ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡

የጉዳይ ጥናት

በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ሁሉም የመማሪያ ክፍሎች የየራሳቸው ተወካዮች መኖር ወሳኝ ነው፡፡ ስለዚህ ልክ እንደሌላው ክፍል እናንተም ተወካዮች ሊኖሩዋችሁ ይገባል፡፡ በክፍልህ ውስጥ 35 ተማሪዎች እንዳሉ አስብ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የሚመረጡት ተወካዮች ሁለት ናቸው፡፡ በምርጫው ወንድ እና ሴት ተማሪዎች መወከላቸውን አረጋግጡ፡፡ ሁለት ተወካዮች መኖራቸው የሚያስፍልገው አንድ ተወካይ በተለያዩ ምክንያቶች በክፍሉ ውስጥ የማይገኝ ከሆነ ሁለተኛው (ምክትል) ተወካይ የራሱን ሚና ይተካዋል:: እነዚህ ሁለት ተወካዮች የተመረጡት በእነዚያ 35 ተማሪዎች ሁሉ ተሳትፎ ነው፡፡ ምርጫው

ፍትሃዊ እና ነፃ መሆን አለበት፡፡ በምርጫው ማንም የውጪ አካል ጣልቃ መግባት የለበትም፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በምርጫው ነፃ ሆነው መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል፡ ፡ ምርጫው በዚህ አይነት መልኩ ከተካሄደ ትክክለኛ እና ፍትሃዊ ነው ማለት ይቻላል፡፡

የቡድን ስራ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል አቅርቡ፡፡

1. ከላይ በጥናቱ ላይ የተገለፀው ምርጫ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ነው ማለት ይቻላል? ለምን?ዘርዝሩ፡፡

2. የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ የረጅም ጊዜ ሂደት የሚጠይቅ ነው ። ምክንያቱ ላይ በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ::

3.2. የዴሞክራሲ መነሻ

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡-

- የዴሞክራሲ መነሻ ቦታን ትለያለህ/ሽ፤
- የአቴንስ ዴሞክራሲ ባህሪያትን ትገልጻለህ/ጫለሽ፤
- የአቴንስ ዴሞክራሲን ውስንነት ትዘረዝራለህ/ሪያሽ፤
- የአቴንስ ዴሞክራሲ አስተዋጾን ትዘረዝራለህ/ሪያሽ፡፡

3.2.1 የአቴንስ ዴሞክራሲ

የክፍል ስራ

የዴሞክራሲ መነሻ ቦታ የት ነው ብለህ ትገምታለህ/ቻለሽ ?

ዴሞክራሲ ክክርስቶስ ልደት በፊት በ5ኛው ክፍለ ዘመን ከግሪክ ከተሞች ውስጥ አንዷ በሆነችው “አቴንስ” ውስጥ ተጀመረ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይሁን እንጂ የዴሞክራሲ ሥርዓት አቴንስ ውስጥ ብቻ የነበረ ሳይሆን በይበልጥ አቴንስ በጣም ታዋቂ እና ኃያል ስለነበረች ነው፡፡

በአቴንስ ውስጥ እያንዳንዱ (ወንድ አዋቂ) ዜጋ በከተማው በጣም አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ቀጥታ በመሳተፍ የውሳኔ ድምጽ ይሰጡ ነበር፡፡ ስለዚህ በግሪክ የተጀመረው ዴሞክራሲ ቀጥተኛ ዴሞክራሲ ነበር፡፡ የአቴንስ ዴሞክራሲ ብዙ ከዘመናዊው ዴሞኪራሲ ጋር የሚጣጣም መርሆች አሉት፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

- ቀጥተኛ የህዝብ ተሳትፎ መኖሩ፤
- የፖለቲካ እኩልነት (ቢያንስ ለአዋቂ ወንድ ዜጎች) መስጠቱ፤
- መንግስት ለህዝብ ተጠያቂ መሆን አለበት የሚለው አስተሳሰብ መኖሩ፤
- ተገገርዎች በሚል ፋንታ ዜጎች የሚል ሀሳብ መፈልሰፉ።

በአጠቃላይ የአቴንስ ዴሞክራሲ እንደ ዴሞክራሲ መነሻ ቢወሰድም ውስንነቶችም ነበሩት። ከውስንነቶቹ መካከል ለምሳሌ ከዴሞክራሲ መሰረታዊ መርሆች ውስጥ ሁሉም ዜጎች በሀገራቸው ፖለቲካ ውስጥ እኩል ተሳትፎ ይኖራቸዋል የሚል እና ሁሉም ዜጎች ነጻና በባርነት መገዛት የለባቸውም የሚለውን አያሟላም። ይሁን እንጂ በመንግስታዊ አስተዳደር ውስጥ ለዜጎች እድል ስለሚሰጥ ለዘመናዊ የውክልና ዴሞክራሲ እንደ መሠረታዊ ምንጭ ይወሰዳል።

3.3 የዴሞክራሲ አይነቶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃት፤

- የሊበራል ዴሞክራሲ ምንነት ትገልጻለህ/ሚለሽ፤
- የማህበራዊ ዴሞክራሲ ዋና ባህርያት ትገልጻለህ/ሚለሽ፤
- በሊበራል እና ማህበራዊ ዴሞክራሲ መካከል ያለውን ልዩነት ትገልጻለህ/ሚለሽ።



የግንዛቤ ጥያቄ

የሊበራል እና ማህበራዊ ዲሞክራሲ ልዩነት ምንድን ነው?

መንግስት በምጣኔ ሀብታዊ እና በፖለትካዊ ጉዳየዎች ዉስጥ የሚያደርገውን ተሳትፎ መሠረት በማድረግ ዲሞክራሲን ሊበራል እና ማህበራዊ በማለት ሁለት ቦታ መክፈል ይቻላል።

3.3.1 ሊበራል ዲሞክራሲ

ሊበራል ዲሞክራሲ በህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ የመንግስት ጣልቃ ገብነትን የሚከለክል የዲሞክራሲ አይነት ነው። በኢኮኖሚያዊ ዘርፎች ውስጥ የመንግስት ሚና በጣም አናሳ ነው። እንደ ገበያ ላሉ የኢኮኖሚ ኃይሎች ግን ከፍተኛው ቦታ ተሰጥቷል። ይህ ዓይነቱ ዴሞክራሲ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚን መሠረት ያደረገ ነው። ይህ የሚያመለክተው የመንግስት ሚና ሥርዓትን ማስጠበቅ እና

ደንቦችን ማዘጋጀት ተወዳዳሪ የኢኮኖሚ ኃይሎች ሚዛን በመጠበቅ ሚናቸውን የሚጫወቱበትን ማዕቀፍ ያዘጋጃል። ከዚህ በመነሳት የሊበራል ዲሞክራሲ ማዕከላዊ ሃሳብ የግለሰብ የፖለቲካ እና የህግ እኩልነት እንጂ የኢኮኖሚ እኩልነት አለመሆኑን ማወቅ ይቻላል። ከዚህ እይታ አንጻር ሊበራል ዲሞክራሲ አንዳንዴ ካፒታሊስት ዲሞክራሲ ይባላል። ይህም በአብዛኛዎቹ በምዕራባውያን አገሮች ይተገበራል።

3.3.2 ማህበራዊ ዴሞክራሲ

ማህበራዊ ዴሞክራሲን የሚያራምዱ መንግስታት ለኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች የበለጠ ቅድሚያ ይሰጣሉ። የማህበራዊ ዴሞክራሲ ግብ ካፒታሊዝምን በማሻሻል እኩልነት እና መደብ አልባ ማህበረሰብን መፈጠር ነው። ማህበራዊ ዴሞክራሲ ለማህበራዊ ፍትህ እና ድሆችን በኢኮኖሚ ማብቃትን ያበረታታል። ለዚህም የማህበራዊ ዋስትና፣ የመኖሪያ ቤት፣ የነፃ ትምህርት፣ የጤና እና የህክምና አገልግሎት አቅርቦት እና ሌሎች መሰል አገልግሎቶችን መስጠትን ይመለከታል።

3.4 ዴሞክራሲን የማስፈጸም መንገዶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃት፤

- ዴሞክራሲ ሥራ ላይ የሚውልበትን መንገድ ታብራራለህ/ሪያለሽ፣
- የቀጥተኛ ዲሞክራሲ ምንነትን ትገልጻለህ/ጫለሽ።



የግንዛቤ ጥያቄ

ዴሞክራሲ በምን መንገድ ሥራ ላይ ይውላል ብለህ ታስባለህ/ቢያለሽ?

በዴሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ የዜጎችን ተሳትፎ መሰረት በማድረግ ዴሞክራሲን በሁለት መክፈል ይቻላል። እነሱም ቀጥተኛ (ንፁህ) እና ቀጥተኛ ያልሆነ (ተወካይ) ዴሞክራሲ ይባላሉ።

3.4.1 ቀጥተኛ ዴሞክራሲ

የክፍል ስራ

ቀጥተኛ ዴሞክራሲ የምንለው ምን አይነት ዴሞክራሲ እንደሆነ ግምትህን ፃፍ/ፊ።

ቀጥተኛ ዴሞክራሲ (ንፁህ ዴሞክራሲ) "ሁሉም አዋቂ ዜጎች" ያለምንም ተወካይ ጣልቃ ገብነት በቀጥታ በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ የሚሳተፉበት የዴሞክራሲ አይነት ነው። ይህ እምነት የተመሰረተው ከተወሰነ ዕድሜ በላይ የሆነ ማንኛውም ዜጋ በፖለቲካ ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ፣ የተወያዩበት ጉዳይ ላይ ድምጽ መስጠት እና የብዙሃኑን ውሳኔ መቀበልን የሚያካትት ነው። ለምሳሌ፡ በክፍል ውስጥ፤ የክፍላችሁን ተወካይ በቀጥታ መምረጥ ትችላላችሁ። ይህ ደግሞ የቀጥተኛ ዲሞክራሲ አንዱ ምሳሌ ነው።



ምስል 3.2 ተማሪዎች የክፍል ተወካዮቻቸውን በቀጥታ ሲመርጡ

ከቀጥተኛ ዴሞክራሲ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮች የሚታወቁ ናቸው። የአንድ ሀገር ህዝብ ውሳኔ ለማድረግ መሰብሰብ በማይችልበት ጊዜ ውስብስብ እና አጠቃላይ ጉዳዮችን በተመለከተ ቀጥተኛ የዴሞክራሲ ሥራ ላይ ማዋል አዳጋች ይሆናል። ሆኖም ቀጥተኛ ዴሞክራሲን ለመተግበር የሚያስችሉ ሁኔታዎች

አለ። ቀጥተኛ ዴሞክራሲ ሪፈረንደም ለማካሄድ፤ በአከባቢ ኮሚቴዎች፣ ትምህርት ቤቶች እና የዜጎች ማኅበራት አማካይነት ሊተገበር የሚችል ሲሆን ይህም ውይይት ተደርጎበት በጋራ ድምፅ ሊሰጥበት ይችላል።

የሚና ጨዋታ

በኢትዮጵያ ማንኛውም ሰው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ያስቀመጠውን መስፈርት እስካሟላ ድረስ በህዝበ ውሳኔ የመምረጥ መብት አለው። በዚህ መልኩ አንተ የምትኖርበት አከባቢ ያለ ህዝብ ከዞን መዋቅር ወደ ክልልነት ለማደግ ድምጽ እየሰጡ ነው ብለህ አስብ፤ እንደ ዜጋም አንተም/ችም በሪፈረንደም ላይ ድምጽህን እየሰጠህ ነህ/ሽ እንበል፣ ከላይ የተሰጠውን ምሳሌ በማድረግ ከክፍል ተማሪዎች ጋር ከወረዳ ወደ ዞን መዋቅር ለማደግ በሚሰጠው ህዝበ ውሳኔ ላይ ሚና ተጫወቱ። ድምጽ መስጠት ሲጨርሱ አስተማሪያችሁ ድምጽጻችሁን ይቆጥራሉ። በመጨረሻም አስተማሪያችሁ የሪፈረንደም ውጤቱን ያሳውቃሉ። በዚህ ህዝበ ውሳኔ ሂደት ውስጥ ያለህ ተሳትፎ የቀጥተኛ ዴሞክራሲ አንዱ ማሳያ ነው።

የቡድን ሥራ

ቀጥተኛ ዴሞክራሲን በዚህ ዘመን መተግበር ይቻላል? ለምን? በቡድን በመወያየት ለክፍላችሁ አቅርቡ።

3.4.2 ቀጥተኛ ያልሆነ (የውክልና) ዴሞክራሲ

የውክልና ዴሞክራሲ ምን አይነት ዴሞክራሲ ነው?

ቀጥተኛ ያልሆነ ዴሞክራሲ ዛሬ ያለንበት የዘመናዊ ዴሞክራሲ አይነት ነው። የውክልና ዴሞክራሲ ማለት የአንድ ሀገር ዜጎችን ወክለው ውሳኔ የሚሰጡ ተወካዮችን የሚመርጡበት ሂደት ነው። ከዚህ አንፃር የውክልና ዴሞክራሲ ትርጉሙ መላው ሕዝብ በራሱ ጉዳይ ላይ በቀጥታ መሳተፍ ባይችልም በየጊዜው ራሱ በሚመርጣቸው ተወካዮቹ አማካይነት መሳተፍ ማለት ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ በየአምስት አመቱ ህዝቡ በፓርላማ እንዲወክላቸው የሚፈልገውን እንዲመርጥ እድሉን ያገኛል። የፓርላማ አባላት በህዝብ ተወካዮች

ምክር ቤት ተገናኝተው ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተወያይተው ውሳኔ ያስተላልፋሉ፡፡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ እያንዳንዱ የተመረጠ ፓርላማ ሁሉንም ዜጎች ይወክላል፡፡ በሕግ ማውጣት ላይ የመሳተፍ ኃላፊነት በመራጮች ለፓርላማ አባላት ተሰጥቷል፡፡ በዚህ ሁኔታ መሪዎች በስልጣን ላይ ለመቆየት ከመራጮች ጋር በተወሰነ ደረጃ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ነገር ግን ፓርቲው በስልጣን ዘመናቸው ደካማ አፈጻጸም ካሳዩ ውክልናችውን የማንሳት ሙሉ ስልጣን አለው፡፡ ህዝቡ በዚህ መልኩ በተወካዮቹ ላይ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡



ምስል 3.3 በኢትዮጵያ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዝብን ወክሎ በፓርላማ ውሳኔ ሲያስተላልፍ



የቡድን ሥራ

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

1. **ቀጥተኛ ያልሆነው ዴሞክራሲ በዘመናችን ከቀጥታ የበለጠ ተመራጭ የሆነው ለምንድን ነው?**
2. **ቀጥተኛ እና የውክልና ዴሞክራሲ ምን አይነት ተመሳሳይት እና ልዩነት አሉት?**

3.5. ዲሞክራሲ ላይ ያሉ እሳቤዎች/አተያዮች/አመለካከቶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃት፤

- ሒደታዊ ዴሞክራሲ አተያይን ታብራራለህ/ሪያለሽ፤፣
- ተጨባጭ ዴሞክራሲ አተያይን ትገልጻለህ/ጫለሽ፤፣
- የሒደታዊ ዴሞክራሲ እና ተጨባጭ ዴሞክራሲ አተያይ ሊዩነት ታብራራለህ/ሽ።።



ዴሞክራሲ ሒደት ነው ወይስ ግብ ነው ብለህ ታስባለህ/ቢያለሽ?

ዴሞክራሲን ለመረዳት ሁለት አቀራረቦች አሉ፡ እነሱም፤ ሂደት እና ተጨባጭ ናቸው።።

3.5.1 ሥርዓታዊ/ሒደታዊ የዴሞክራሲ አተያይ

የሥርዓታዊ/ሂደታዊ የዴሞክራሲ አተያይ የመንግስትን ቅርፅ እና ሂደት ወይም ህዝብ እራሱን እንዴት ማስተዳደር እንዳለበት ያጎላል። የሂደታዊ ዴሞክራሲ አተያይ መርሆዎች ሁለንተናዊ ተሳትፎ፣ የፖለቲካ እኩልነት እና የአብላጫ አገዛዝ ናቸው። እንደ ሂደታዊ አተያይ፤ ዴሞክራሲ የሚለየው መራጮች ተወካዮቻቸውን ለመምረጥ በሚያደርጉት ነጻ ምርጫ ነው። ለሥርዓታዊ ዴሞክራሲ የምርጫ ሂደት ለዴሞክራሲ ማዕከላዊ እንደሆነ እና ሁሉም የምርጫ ሂደቶች መከበር እንዳለባቸው አጽኖት ይሰጣል።

3.5.2 ተጨባጭ የዴሞክራሲ አተያይ

ተጨባጭ የዴሞክራሲ አተያይ የሚያተኩረው መንግሥት በተጨባጭ በሚሠራው ሥራ ላይ ነው። ማለትም፦ የሚተገብራቸው ፖሊሲዎች ከዴሞክራሲያዊ እሳቤዎች ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው። ተጨባጭ ዴሞክራሲ የምርጫ ውጤቶች ህዝብን ይወክላል ተብሎ የሚታሰብበት የዴሞክራሲ አተያይ አይነት ነው። በተጨባጭ ዴሞክራሲ ውስጥ መንግስት የፖለቲካ ጉዳዮቹን እንዴት እንደሚመራ ህዝቡ የራሱን ድምጽ መስጠት መቻል አለበት። ይህ ዓይነቱ የዴሞክራሲ አተያይ ተግባራዊ ዴሞክራሲ በመባልም ይታወቃል።

ምንም እንኳን አንድ ሀገር ሁሉም በድምጽ መስጫ እድሜ ላይ ያሉ ዜጎች እንዲመርጡ መፍቀድ ብትችልም ይህ ግን ብቻውን እንደ ተጨባጭ ዴሞክራሲ

እንድትታይ አያደርጋትም። ተጨባጭ ዴሞክራሲ አለ ለማለት ምርጫው ለህዝቦች (የፖለቲካ እኩልነት፣ የኢኮኖሚ ብልፅግና እና ሌሎች) ተግባራዊ ለውጦችን ማምጣት አለበት።

በአሰራር ዴሞክራሲ እና በተጨባጭ ዴሞክራሲ መካከል ያለው ዋና ልዩነት ምን እንደ ሆነ በቡድን በመወያት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

3.6 አገር በቀል ዴሞክራሲያዊ ተግባራት/ልምዶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃት፤

- የአገር በቀል ዴሞክራሲያዊ ተግባራት ምንነት ትገልጻለህ/ሚለሽ፤፣
- የኢትዮጵያን አገር በቀል ዴሞክራሲያዊ ተግባራት ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ።

ሀገር በቀል ዴሞክራሲ ማለት ምን ማለት ነው?

ዘመናዊ የአፍሪካ መንግስታት ከመፈጠሩ እና የመድበለ ፓርቲ ፖለቲካ ስርዓት ከመጀመሩ በፊት ኢትዮጵያን ጨምሮ ሀገር በቀል ልማዳዊ ተቋማት እና የአስተዳደር ስርዓቶች በአፍሪካ እንደነበሩ እና አሁንም እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ ባህላዊ የአፍሪካ የአስተዳደር ሥርዓቶች ለዘመናዊ አስተዳደር ጠቃሚ ናቸው ተብሎ ይታመናል። ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓቶች ከዘመናዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች በተጨማሪ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።

በኢትዮጵያ በተከታታይ መንግስታት ዘመናዊ የአስተዳደር ስርዓቶችን ተግባራዊ ቢያደርጉም የሀገር በቀል ተቋማት የህብረተሰቡን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ህይወት በመምራት በተለይም በገጠር ያሉ የመንግስት ተቋማት የሚፈጠሩትን ክፍተት በመሙላት የማይተካ ሚና ተጫውተዋል እየተጫወቱም ነው። ኢትዮጵያ በሥልጣኔ፣ በታሪክና በባህል የምትታወቅ አገር ነች። ይህ ሀብት በተለያዩ የኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች ውስጥ ከጥንት ጀምሮ የቆዩ ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን ያጠቃልላል። ለምሳሌ፤ ግልጽ ክርክር፣ መግባባት እና በአጀንዳ ቀረጻ እና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የመሳተፍ መሰረታዊ የዴሞክራሲ መርሆዎች በተለያዩ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች በአከባቢ ደረጃ እንደ ልማዳዊ ባህሎች ሲተገበሩ ቆይተዋል።

ገዳ የኦሮሞ ህዝብ ከሚጠቀምባቸው ሀገር በቀል የአስተዳደር ስርዓቶች አንዱ

ሲሆን ይህም በማህበረሰብ ልምድ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ቆይቷል። ስርዓቱ የማህበረሰቡን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን ይቆጣጠራል፣ እንደ ግጭት አፈታት እና ሌሎች ጉዳዮችን ይመለከታል። ገዳ ለማህበራዊ ትስስር እና የማህበረሰቡ የባህል መገለጫዎች ሆኖ ያገለግላል። –



ምሲል 3.4 ሀገር በቀል ዴሞክራሲያዊ ተግባራት

የኢትዮጵያ ህዝብ በማህብረተሰቡ ዘንድ ቅቡልነት ያለውን ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ተቋማት አሉት። ከነዚህም የተወሰኑት፤ ጃርሱማ በኦሮሞ፤ ሽምግልና በአማራ፣ ያጆካ በጉራጌ፣ ዲራሲማ በወላይታ፣ እናሽማ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ባይቶ በትግራይ፣ ማዳአ በአፋር፣ ጠር በሱማሌ ፣ እና ሌሎች አገር በቀል የግጭት መፍቻ ልማዶችን መግለጽ ይቻላል።

በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች እየተተገበሩ ያሉ የተለያዩ ሀገር በቀል የግጭት አፈታት ተግባራት በልዩ ልዩ ጥቅም ምክንያት የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ፍርድ ቤቶች ያሉ መደበኛ ተቋማት ቢኖሩም ከላይ የተጠቀሱት አገር በቀል አሠራሮች የተለያዩ ጉዳዮችን በማንሳት ብዙ አስተዋፅዖ አላቸው።

የምዕራፍ ማጠቃለያ

ዴሞክራሲ ከግሪክ ቃላት (ዴሞስ እና ክራቶስ) የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም "የሕዝብ አገዛዝ/አስተዳደር" ማለት ነው። ዴሞክራሲ በአቴንስ ከተሞች እንደተጀመረ ይታሰባል። ዴሞክራሲ የፖለቲካ ስልጣን በህዝብ እጅ መኖሩን የሚያሳይ የመንግስት አይነት ነው። የአንድ ሀገር ዜጎች በቀጥታ እና በተወካዮቻቸው በኩል በዴሞክራሲ መሳተፍ ይችላሉ። ሁሉንም አዋቂ ዜጎች በማሳተፍ ዴሞክራሲን በቀጥታ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል። በቀጥተኛ ዴሞክራሲ ውስጥ ዜጎች በሁሉም የፖለቲካ ጉዳዮች እና ውሳኔዎች ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ።

በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች እንደ የህዝብ ብዛት፣ የመሬት አቀማመጥ፣ ሀብት፣ ጊዜ እና ሌሎች በርካታ ጉዳዮች፣ ቀጥተኛ ዴሞክራሲ አይመረጥም። ይልቁንም የውክልና ዴሞክራሲ ለብዙ አገሮችና ዜጎቻቸው ዴሞክራሲን በተግባር ከሚያሳዩባቸው መንገዶች አንዱ ሆኗል። በተወካይ ዴሞክራሲ ውስጥ ህዝቦች ተወካዮቻቸውን ይመርጣሉ፤ ከዚያም ተመራጮቹ ህዝቡን ወክለው ይሠራሉ ተብሎ ይጠበቃል።

በሌላ መንገድ፤ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ዴሞክራሲን መገንባት ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ የተለያዩ ተዋናዮችም ዴሞክራሲን እና የዴሞክራሲ ባህልን ለመገንባት በጋራ መሥራት አለባቸው። በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሚዲያዎች፣ የሕዝብ አስተያየትና የሲቪክ ማኅበራት ሚናቸው ትልቅ ነው። –

ዴሞክራሲን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፤እነዚህም ሊበራል እና ማህበራዊ ዴሞክራሲ ናቸው። ሊበራል ዴሞክራሲ በህብረተሰቡ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ የመንግስት ጣልቃ ገብነትን የሚከለክል የዴሞክራሲ አይነት ነው። ማህበራዊ ዴሞክራሲ ደግሞ የካፒታሊዝም የለውጥ መንገድ በመከተል እኩልነት እና መደብ አልባ ማህበረሰብን መፍጠር ነው።

ዴሞክራሲን ለመረዳት ሁለት አተያዮች አሉ፤ የሥርዓት/ህደት እና ተጨባጭ አተያይ። የሂደት የዴሞክራሲ እይታ የመንመንገድግስት ቅርፅ እና ሂደት ላይ የሚያተኩር ሲሆን ተጨባጭ የዴሞክራሲ እይታ ደግሞ መንግስት በሚያደርገው ተጨባጭ ውጤት ላይ ያተኩራል።

ሀገር በቀል ዴሞክራሲ የህብረተሰቡ ነባር እውቀት ሆኖ ህብረተሰቡ ውሳኔ ለመስጠት፤ ግጭቶችን ለመፍታት እና አመራር ለመስጠት ሲጠቀምበት የነበረ እና እየተጠቀመበት ያለ ተግባር ነው። ከዘመናዊው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጎን ለጎን ባህላዊ/ሀገር በቀል የአስተዳደር ሥርዓቶች ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል እያበረከቱም ነው።

የምዕራፍ ቁልፍ ቃላት

- ዴሞክራሲ- የህዝብ አስተዳደር ሆኖ ስልጣን በሰፊው ህዝብ እጅ ያለ ሥርዓት ነው።
- ቀጥተኛ ዴሞክራሲ- ሁሉም አዋቂ ዜጎች ያለ ተወካይ ጣልቃ ገብነት በቀጥታ በውሳኔ አሰጣጥ ህደት ላይ የሚሳተፉበት የዴሞክራሲ አይነት ነው።
- የውክልና ዴሞክራሲ- የአንድ ሀገር ዜጎች ህዝቡን የሚወክሉ ግለሰቦችን በመምረጥ በተወካዮች በኩል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የመሳተፍ ሂደት ነው።
- ሊበራል ዴሞክራሲ- የግለሰቦችን መብት እና ነጻነት የሚያበረታታ ሆኖ በህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ውስጥ የመንግስት ጣልቃ ገብነትን የሚከለክል የዴሞክራሲ አይነት ነው።
- የማህበራዊ ዴሞክራሲ- ማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ሆኖ የዜጎችን እኩልነት እና ፍታዊነትን በማረጋገጥ መደብ አልባ ማህበረሰብን ማስፈንን የሚደግፍ ነው።
- የሥርዓት/ሂደታዊ የዴሞክራሲ- የዴሞክራሲ አተያይ ሆኖ የመንግስትን ቅርፅ እና ሂደት ላይ የሚያተኩር ነው።
- ተጨባጭ ዴሞክራሲ- የዴሞክራሲ አተያይ ሆኖ መንግሥት በተጨባጭ በሚሠራው ሥራ ላይ የሚያተኩር ነው።

የምዕራፍ የክለሳ ጥያቄዎች

ክፍል አንድ፡ የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት " ስህተት ከሆኑ " ሐሰት " በማለት መልሱ። –

1. ዴሞክራሲ በጥንቷ ሮም እንደተጀመረ ይታሰባል።
2. የዴሞክራሲ ተጨባጭ እይታ መንግስት በተጨባጭ በሚሰራው ላይ ያተኩራል።
3. ጥንታዊው የአቴና ዴሞክራሲ ለዘመናዊ ዴሞክራሲ ምንም አይነት አስተዋፅኦ የለውም።
4. በውክልና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ሕዝብ በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በቀጥታ ይሳተፋል።
5. የማህበራዊ ዴሞክራሲ አላማ ካፒታሊዝም በማሻሻል እኩልነትን እና መደብ አልባ ማህበረሰብን ማስፈን ነው።

ክፍል II፡ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ

1. ከሚከተሉት ተዋናዮች መካከል በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ውስጥ ጠቃሚ የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. የፖለቲካ ፓርቲዎች ሐ. የሕዝብ አስተያየት

   ለ. የብዙሃን መገናኛ መ. ሁሉም

2. ስለ ጥንታዊው የአቴንስ ዴሞክራሲ ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የትኛው እውነት ነው?

   ሀ. ዜግነት ለጥቂት ልሂቃን የተገደበ ነበር።

   ለ. ሴቶች እና ባሪያዎች እንዲሳተፉ አይፈቀድላቸውም ነበር።

   ሐ. ቀጥተኛ የዲሞክራሲ ዓይነት ነበር

   መ. ሁሉም

3. የነፃ ገበያ ሥርዓትን በመደገፍ የሚታወቀው ዴሞክራሲ ዓይነት የቱ ነው?

ሀ. ማህበራዊ ዴሞክራሲ

ለ. ሊበራል ዴሞክራሲ

ሐ. ተጨባጭ ዴሞክራሲ

መ. ሂደታዊ ዴሞክራሲ

4. ሀገር በቀል የዴሞክራሲ ተቋም ሆኖ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ግጭቶችን ለመፍታት የሚያገለግለው የቱ ነው?

ሀ. ሽምግልና ሐ. ማዳኣ

ለ. ዬጆካ መ. ጃርሱማ

5. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ዴሞክራሲ እውነት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ዴሞክራሲ እና የዴሞክራሲ ሥርአት ግንባታ ሂደት ነው።

ለ. ዴሞክራሲ ሊገነባ የሚችለው በመንግስት ተሳትፎ ብቻ ነው።

ሐ. ቀጥተኛ ዴሞክራሲ በዘመናችን ከበፊቱ የበለጠ ተመራጭ ነው።

መ. መልስ አልተሰጠም

ምዕራፍ 4 የሕግ የበላይነት

መግቢያ

በምዕራፍ ሦስት ስለ ዴሞክራሲ ዕንሰ ሀሳብ እና ተዛማጅ ጉዳዮችን ተምረሃል/ሻል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ከመሰረታዊ የዴሞክራሲ ስርዓት መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ስለሆነው ስለ የህግ የበላይነት ትማራለህ/ሽ። በጥቅሉ ይህ ምዕራፍ ስለ የሕግ የበላይነት ጽንሰ-ሐሳብ፤ የህግ የበላይነት አስፈላጊነት፣ የህግ የበላይነት መገለጫዎች፤ በሕግ የበላይነት እና በግለሰብ የበላይነት መካከል ያለውን ልዩነት እንደዚሁም የህግ የበላይነት ተግዳሮቶችን የሚያካትት ይሆናል።

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

- የሕግ የበላይነት ጽንሰ-ሐሳብን መግለጽ፤
- የሕግ ምንጮችን መለየት፤
- የህግ የበላይነት አስፈላጊነትን መግለጽ፤
- የህግ የበላይነት መገለጫዎችን መለየት፤
- የህግ የበላይነት እና የግለሰብ የበላይነትን መግለጽ፤
- የህግ የበላይነት ተግዳሮቶችን መተንተን ይሆናል።

4.1. የሕግ የበላይነት ጽንሰ-ሐሳብ

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡-

- የሕግ የበላይነት ጽንሰ-ሀሳብን ትገልጻለህ/ጫለሽ፤
- ፍትህን በዕለት ተዕለት ኑሮህ/ሽ ውስጥ ትተገብራለህ/ሪያለሽ፤
- የአንድ ሰው ድርጊት ፍትሃዊ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ትተነትናለህ/ኛለሽ።



የህግ የበላይነት ማለት ምን ማለት ነው?

የህግ የበላይነትን ለመገንዘብ የህግ ምንነትን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ሕግ ማለት መመሪያዎችንና ደንቦችን ያቀፈ ሆኖ በህግ አውጭው አካል ተደንግጎ ዜጎች ሁሉ ማክበር ያለባቸው ነው። ህግ የዜጎች መብቶች በተለያዩ አካላት ማለትም በግለሰቦች፣ በተለያዩ ተቋማት እና በመንግስት እንዳይጣስ ጥበቃ ያደርጋል። ህግ ዜጎች በዕለት ተዕለት ኑሯቸው ውስጥ ማድረግ የሚገባቸውንና ማድረግ የማይገባቸውን የሚያሳይ ነው። በተጨማሪም ዜጎች የሚጠበቅባቸውን ማድርግ ካልቻሉ የሚያስከትለውን ቅጣት ያሳያል።

የህግ የበላይነት ማለት ደግሞ ህግ በተደነገገው መሰረት ስራ ላይ መዋሉን የሚያሳይ ጽንሰ-ሀሳብ ነው። በተጨማሪም መንግስት ከገደብ ውጪ ስልጣን እንዳይጠቀም መገደብና ሰዎች ሁሉ በህግ ፊት እኩል መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። በህግ የበላይነት መርህ መሰረት ማንኛውም ዜጋ ለፈጸመው ጥፋት በህግ ይጠየቃል ማለት ነው። ይህም ማለት ማንኛውም ሰው በህግ ከመጠየቅ የሚያግደው ልዩ መብት የለውም ማለት ነው። በመሆኑም ሁሉም ዜጎች በሕግ ጥላ ሥር እኩል ይስተናገዳሉ ማለት ነው።



ምስል 4.1 ባለስልጣናት እና ህዝብ በሕግ ፊት እኩል ናቸው።

የጉዳይ ጥናት

በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎች በእረፍት ሰዓታቸው የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወቱ ነበር። በጨዋታው ሂደት ከተማሪዎቹ መካከል ሁለቱ ተጣሉ። አብረዋቸው ሲጫወቱ የነበሩት ተማሪዎች ችግሩን ለመፍታት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። በዚህ ጊዜ በአቅራቢያው ያለ አንድ መምህር ወደ ተማሪዎቹ ጠጋ ብሎ ሊያረጋጋቸው ሞከረ። መምህሩም በጥሉ ከተሳተፉት ተማሪዎች ውስጥ አንዱ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ልጅ መሆኑን አረጋገጠ። መምህሩም እነዚህ ተማሪዎች ለምን ወደ ግጭት እንደገቡ ጠየቀ። ከእነሱ ጋር ሲጫወቱ የነበሩት ተማሪዎችም ጥፋተኛው የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ልጅ እንደሆነና ልጁ ሁልጊዜ ከእነርሱ ጋር ሲጫወት ሃይል እንደሚጠቀም ነገሩት። መምህሩ ግን ጥፋተኛው የርዕሰ መምህሩ ልጅ መሆኑን እያወቀ ጥፋተኛ ያልሆነውን ተማሪ አስጠንቅቆ ተመለሰ።



ምስል 4.2 ጨዋታ ላይ ያሉና እየተጣሉ ያሉ ተማሪዎች

የቡድን ስራ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል አቅርቡ፡፡

1. ጥፋተኛ ያልሆነ ተማሪ ቦታ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?
2. በእናንተ አስተያየት የመምህሩ ድርጊት ተቀባይነት አለው? ለምን?
3. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ አድሎ ደርሶባችሁ ያውቃል? መልሳችሁ አዎ ከሆነ አድሎው ምን ነበር?

የህግ የበላይነት ጽንሰ ሃሳብ ከፍትሃዊነት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡ የህግ የበላይነት ሁሉም ሰው ያለአድሎ እኩል መስተናገድ መቻልን የሚያመላክት ነው፡፡ ፍትሃዊነት በሞራልም ሆነ በህግ ትክክል ወይም እውነት መሆንን የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ሰዎችን ማክበርና ማግኘት የሚገባቸውን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ህግ የሰዎችን ማንነት ማዕከል ሳያደርግ ስራ ላይ መዋል አለበት፡፡ ስለዚህ ህግ በፆታ፣ በቀለም፣ በዘር ወይም በሁኔታዎች አድሎ የሚያደርግ ከሆነ ፍትሃዊ እንዳልሆነ ይቆጠራል፡፡

የጉዳይ ጥናት

መምህሩ ሁል ጊዜ የትምህርቱ ዓላማዎች መሳካታቸውን ለማረጋገጥ ጥያቄ ይጠይቃል። ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት ብዙ ተማሪዎች እጃቸውን ያወጣሉ። መምህሩ ግን ሁል ጊዜ ለጥያቄው ምላሽ እንዲሰጡ ለሁለት ተማሪዎች ብቻ እድል ይሰጣል። ተማሪዎቹም በመምህሩ ድርጊት እየተናደዱ መጡ። በመምህሩ ድርጊት ከተናደዱት ተማሪዎች መካከል አንዱ አንድ ቀን ድንገት ተነስቶ "መምህር ሆይ ጥያቄ አለኝ" አለው። በተማሪው ድርጊት የተበሳጨው መምህር ለተማሪው ጥያቄ መጠየቅ የሚችለው ፍቃድ ከተሰጠው ብቻ እንደሆነ ይነግረዋል። ተማሪውም መምህሩን እኔ ሳላስፈቅድ ተነስቼ ጥያቄ አለኝ ማለቴ ስህተት ሊሆን ይችላል ነገር ግን፣ እኔ ያለ እርሶ ፍቃድ ድንገት ተነስቼ ጥያቄ አለኝ ለማለት የተገደድኩት እርሶ በእኛ መካከል በሚያደርጉት አድሎአዊ አሰራር ነው። እኛ ሁላችንም የእርሶ ተማሪዎች ነን እና ለእያንዳንዳችን እኩል እድል የመስጠት ሃላፊነት አለቦት። እርሶ ግን በአድሎ ለሁለቱ ተማሪዎች ብቻ እድል ይሰጣሉ። በመሆኑም አሁን በአክብሮት የምጠይቆት ሁላችንም መሳተፍ እንፈልጋለን ። ስለዚህ ለሁላችንም እኩል የመሳተፍ እድል ሊሰጡን ይገባል አለው።



የቡድን ስራ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኃላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ

1. ከላይ በውስን ጥናቱ በቀረበው መስተካከል አለበት በምትሉት ሀሳብ ላይ ተወያዩበት።
2. የተማሪው ድርጊት ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? በክፍል ውስጥ ሀሳባችሁን የሚትገልጹበት ሌላ መንገድ አለ?ተወያዩበት።
3. በዕለት ተዕለት ኑሯችሁ ውስጥ ፍትህን እንዴት ትተገብራላችሁ?



ምስል 4.3 በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን እኩል አለማሳተፍ

4.2. የሕግ ምንጮች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡-

- የሕግ ምንጮችን ትለያለህ/ሽ፤
- እንደ ሕግ ምንጭነታቸው ሕገ መንግሥት እና ሞራልን ታነፃፅራለህ/ሪያለሽ፤
- የሕግ አውጭው አካል እንዴት የሕዝቡን እሴት ህግ ውስጥ እንደሚያካትት ትገመግማለህ/ሚያለሽ።

ህግ ከየት ይመነጫል ብለህ/ሽ ታስባለህ/ቢያለሽ?

ዋና ዋናዎቹ የሕግ ምንጮች በአራት ይከፈላሉ። እነሱም፡-

1. **ሕገ መንግሥት-** ሕገ መንግሥት የአስተዳደር ሥርዓትንና መርሆችን የሚዘረዝር፣የመንግሥት ተቋማትን፣ የተቋማቱን አሰራርና ግንኙነታቸውን የሚገልጽ ሰነድ ነው። እንዲሁም የመንግሥት የሥልጣን ገደብና የዜጎችን መብት ይገልጻል። የአንድ ሀገር ህግ የሚተገበረው ህገ መንግስቱን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው። ስለዚህ ሕገ መንግሥት መሠረታዊ የሕግ ምንጭ ነው።
2. **እሴት-** እሴት ጠቃሚ ልምዶች ህብረተሰቡ በረጅም ጊዜ የኑሮ ሂደት ውስጥ ያዳበረው እና ያልተጻፈ ሆኖ ህዝቡን የማጣመር እና የመምራት

ሀይል ያለው ነው። ከህግ ምንጮች ውስጥ አንዱ የህዝቡ እሴት ነው። ዘመናዊ ህግ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ በሰዎች መካከል አለመግባባቶችን ለመፍታት እና ውሳኔ ለመስጠት ህብረተሰቡ እሴቱን ሲጠቀምበት ኖሯል፡ ፡ ማንም እሴቱን ሲተላለፍ ማህበራዊ መድልዎ ይደረስበታል። ማህበራዊ ተቋማትም የሚገነቡት የህብረተሰቡን እሴት መሰረት በማድረግ ነው።



ምስል 4.4 አዛውንቶችን ማገዝ

የቡድን ስራ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኃላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

1. ከላይ ባለው ምስል ልጅቷ ምን እያደረገች እንደሆነ አብራሩ። እናንተ ብትሆኑ እንዲህ ታደርጋላችሁ?
2. በአካባቢያችሁ አንድ ሰው የህዝቡን እሴት ከተላለፈ ምን አይነት ማህበራዊ መድልዎ ይደረስበታል?

3. ሃይማኖት እና ሞራል- የሃይማኖት ትእዛዛት የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ሀይሎችን አይቶ መፍራት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የህግ ምንጭ ሆኖ ማገልገል

እንደጀመረ ይታመናል። የሃይማኖት ተቋማትም ህዝቡ አውቆ መጠበቅ ያለባቸውን ትእዛዛት ሲያስተምሩ ቆይተዋል። ብዙ ሀገራትም የህገመንገስታቸውን ይዘት ከሃይማኖት መጽሃፍት ወስደው ሲጠቀሙበት ቆይተዋል።

የሥነ ምግባር ደንቦችም በኅብረተሰቡ ውስጥ ሲታዩ ቆይተዋል። ሥነ ምግባር ጥሩ እና መጥፎ፣ትክክል እና ስህተት የሆነን ድርጊት የሚለይ ነው። የሥነ ምግባር ደንቦች መሰረታቸው የሕዝቡ ሞራል ነው። ሞራል የአንድ ሰው የድርጊት መለኪያ ነው። ሃገራትም የህዝባቸውን ሞራል በህገመንግስታቸው ውስጥ በማካተት ይጠቀሙበታል። ስለዚህ የህብረተሰቡ ሃይማኖት እና ሥነ ምግባራዊ ሕጎች የህዝቡን ባህሪ በመቆጣጠር ረገድ ለመንግስት ትልቅ ግብዓት ሆነዋል። መንግስትም የሃይማኖትና የሞራል ትእዛዛትን ህግ በማድረግ ይጠቀምባቸዋል።



ምስል 4.5 በፈተና ላይ የሚኮርጅ ተማሪና ሃላፍነቱን የማይወጣ መምህር።

የቡድን ስራ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኃላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

1. ከላይ ያለውን ምስል በማየት የተረዳችሁትን ለጓደኛችሁ አብራሩ። የተማሪዎቹ እና የመምህሩ ተግባር ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ተወያዩበት።

2. በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የአስተማሪው ሃላፊነት ምንድነው? መምህሩ ጣልቃ ለመግባት ፈቃደኛ ካልሆነ ምን ታደርጋላችሁ?

4. ህግ አውጭው አካል - በተለምዶ ለብዙ ዘመናት ህግ በመሪዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ቆይቷል። በኋላ ላይ የሕግ አውጭው አካል እንደ አንድ የመንግሥት አካል ሆኖ ተቋቋመ። ህግ አውጭዎቹ የህዝቡን ልማዳዊ የባህሪ ህግጋት ወደ ተወሰነ እና ወደተደነገገው የባህሪ ህጎች መቀየር ጀመሩ። ይህ አዳዲስ ህጎችን የማውጣት ተግባርም የህግ ድንጋጌ ይባላል። ስለዚህ የሕግ አውጭው አካል ከዋና ዋና የሕግ ምንጮች ውስጥ አንዱ ነው ማለት ነው።

ትምህርት ቤቶች የራሳቸው መተዳደርያ ደንብ አላቸው። የትምህርት ቤቶች መተዳደርያ ደንብ የተማሪውንና የመምህሩን መብቶችና ግዴታዎች፣ አስተዳደራዊ ህጎችንና መመሪያዎችን ሊያካትት ይችላል። እናንተም የክፍላችሁን መተዳደሪያ ደንብ ማውጣት ትችላላችሁ። የክፍላችሁ መተዳደሪያ ደንብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሊያካትት ይችላል።

የመማሪያ ክፍል መተዳደርያ ደንብ

1. በሰዓት ክፍል መገኘት
2. ለትምህርት አስፈላጊ መሳሪያዎችን ማሟላት
3. የትምህርት ቤት ደንብ ልብስ መልበስ
4. መልእክቶችን በትኩረት መከታተል
5. ሌሎች ሰዎችን ማክበር
6. ተገቢ ያልሆነ ቃላትን ከመጠቀም መቆጠብ
7. ቆሻሻን ቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል
8. ሁል ጊዜ ትምህርት ላይ ተሳትፎ ማድረግ እናለጥያቄዎች መልስመስጠት
9. ለመስጠት መሞክር።



የቡድን ስራ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኃላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡ ፡

1. **በክፍል ውስጥ የመተዳደርያ ደንብ አስፍላጊነት ምንድን ነው?**
2. **ይህ ደንብ መብቶቻችሁን ሊያስከብርላችሁ ይችላል?እንዴት?**
3. **ተማሪዎች ይህንን መተዳደርያ ደንብ ባያከብሩ ምን አይነት ችግር ሊያጋጥም ይችላል?**

4.3. የህግ የበላይነት አስፈላጊነት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡-

- **የህግ የበላይነት አስፈላጊነትን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤**
- **የህግ የበላይነት እንዴት ለዴሞክራሲ ስርዓት መሰረት እንደሆነ ታሳያለህ/ሽ፤**
- **የህግ የበላይነት እና የግለሰብ ነፃነት መካከል ያለውን ትስስር ታደንቃለህ/ቂያለሽ፡፡**



የህግ የበላይነት ለምን አስፈለገ?

ወ/ሮ አያንቱና አቶ ዋቅጅራ

ወ/ሮ አያንቱና አቶ ዋቅጅራ ለብዙ ዓመታት አብረው የቆዩ ጥንዶች ናቸው፡፡ እነሱም ሞሲሳ የሚባል የ7ኛ ክፍል ተማሪ ልጅ አላቸው፡፡ አንድ ቀን ልጃቸው ስላረፈደ የትምህርት ቤታቸው ሰርቪስ ጥሎት ሄደ፡፡ ስለዚህ እናቱ እና አባቱ በራሳቸው መኪና ልጃቸውን ትምህርት ቤት ለማድረስ ተነሱ፡፡ እየነዱ እያሉ የትራፊክ መብራትጋ ሲደርሱ እንደአጋጣሚ ቀይ መብራት እየበራ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አቶ ዋቅጅራ በአካባቢው የትራፊክ ፖሊሶች እንደሌሉ ስላስተዋሉ ቀይ መብራቱ በርቶ እያለ መንገዱን ለመሻገር ወሰኑ፡፡ ባለቤታቸው ወ/ሮ አያንቱ ባለቤታቸው ህግ ጥሰው መንገዱን ለማቋረጥ እንዳቀዱ በደንብ አስተዋሉ፡፡ በመሆኑም አረንጓዴው መብራት እስኪበራ በትዕግስት ጠብቆ ተረጋግቶ እንዲያልፍ ነገሩት፡፡



ምስል 4.6 የትራፊክ መብራት

የቡድን ስራ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኃላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

1. ለህግ የምንታዘዘው ህግ አስከባሪ ሲኖር ብቻ ነው?
2. ቀይ መብራት እያለ አቶ ዋቅጅራ መንገዱን ቢያቋርጡ ምን ሊፈጠር ይችላል?
3. ከአቶ ዋቅጅራ ችኮላ እና ከባላቤታቸው ጥንቃቄ ምን ትረዳላችሁ?
4. ሰዎች ህግን ባያከብሩ ማህበረሰቡ ምን ሊገጥመው ይችላል?

የህግ የበላይነት በሰዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ ውሰጥ በጣም አስፈላጊ ነው። አስፈላጊ ከሆነባቸው ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

1. ዴሞክራሲን ያጎለብታል

የህግ የበላይነት እንዴት ዴሞክራሲን ያጎለብታል ?

የህግ የበላይነት ከዴሞክራስያዊ ስርአት መርሆዎች ውስጥ አንዱ ነው። ስለዚህ የህግ የበላይነት ዴሞክራሲያዊ ስርአትን በማጎልበት ሂደት ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው። በህግ የበላይነት መርህ መሰረት ማንኛውም ዜጋ በሀይማኖቱ፣ በብሄሩ፣ በቋንቋው፣ በቀለሙ እና በጾታው ሳይለይ በህግ ፊት እኩል ነው።

ስለዚህ የህግ የበላይነት ለዴሞክራሲያዊ መንግስት ህልውና አስፈላጊ መስፈርት ተደርጎ ይወሰዳል።



ምስል 4.7 ዴሞክራሳዊ ስርአትን የገነባ ማህበረሰብ

2 የፍትህ ስርዓቱን ነፃነትእንዲኖርው ያበረታታል

የፍትህ ስርዓት ነፃነት ማለት ምን ማለት ነው?

የሕግ የበላይነት ባሌለበት የፍትህ ስርዓቱ ማለትም ፍርድ ቤት፤ አቃቤ ህግና ፖሊስ ከማንኛውም የውጭ ተጽእኖ ነፃ ሆነው ስራቸውን ያከናውናሉ። ፍርድቤቶች ከተፅእኖ ነጻ ሆነው በሕግ ላይ ብቻ ተመስርተው ውሳኔ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል።

3 የግለሰብን ነፃነት ያሳድጋል

በሕግ የበላይነት እና በግለሰብ ነፃነት መካከል ያለው ትስስር ምንድንነው?

የህግ የበላይነት ባለበት ህብረተሰብ ውስጥ አማራጭ አመለካከቶችን መግለፅ ይቻላል። የህግ የበላይነት ባለበት መገናኛ ብዙሀን እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጦች እና ማህበራዊ ሚዲያን ጨምሮ የሚዲያ ነፃነት ይከበራል። የሕግ የበላይነት በሌለበት ግን ማንም ሰው የመናገር መብትም ሆነ የተለያዩ አመለካከቶችን የማራመድና የመፃፍ መብት አይኖረውም።

4. የዘፈቀደ እና አምባገነንነት ን ያስቀራል

ዜጎች መብታቸውን እና ነጻነታቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁት የህግ የበላይነት በአግባቡ ሲተገበር ነው። ይህም መብታቸው እየተጣሰ መሆኑን እና አለመሆኑን ለማረጋገጥ ያስችላቸዋል። እንዲሁም የመንግስት ተሿሚዎችን የዘፈቀደነት እና አምባገነንነት ይቆጣጠራል። የህግ የበላይነት በሌለባቸው ሀገራት አምባገነን መንግስታት የህዝብን ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ ሃይል መጠቀምን ይመርጣሉ። የሚመሩትን ሀገርና ህዝብ ማስፈራራትና ማሸማቀቅ ይፈልጋሉ። ከዚህ የተነሳ አምባገነን መንግስት ስር ያሉ ዜጎች ለተቃውሞ አደባባይ መውጣታቸው የማይቀር ይሆናል።



ምስል 4.8 ሰላማዊ ተቃውሞ እና የአምባገነኖች ምላሽ

4.4. የህግ የበላይነት መገለጫዎች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡-

- የህግ የበላይነት መገለጫዎችን ትገልፃለህ/ጫለሽ፤
- ፍርድ ቤት ጥፋተኛ መሆናቸውን እስከሚወስንባቸው ድረስ ሰዎች ነፃ መሆናቸውን ትናገራለህ/ሪያለሽ፤
- የስልጣን ክፍፍል አስፈላጊነትን ትናገራለህ/ሪያለሽ።

- ህግ እያከበርክ መሆንህን ወይም አለመሆንህን እንዴት ታውቃለህ/ቂያለሽ?

1 የፍትህ ስርዓቱ ነፃ መሆን

የፍትህ ስርዓት ነፃ መሆን ማለት ውሳኔ በሚሰጥበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች እና ሌሎች የፍትህ አካላት ከተለያዩ ተጽእኖ ነፃ መሆን ማለት ነው። ዳኞች ሕግን

መሰረት ባደረገ መልኩ ውሳኔ ሲወስኑ ከፖለቲካ ተፅእኖ ፣ ከግል ፍላጎት እና ከሌሎች ተጽእኖዎች ነጻ መሆን አለባቸው። የፍትህ ስርዓት ነፃ መሆን የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል። ስለሆነም የፍትህ ስርዓቱ ነፃ መሆን የህግ የበላይነት መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ነው።

2 ሕግ በሁሉም ሰው ላይ እኩል ተግባራዊ መሆን

ከህግ የበላይነት መገለጫዎች ውስጥ ሌላኛው ተመሳሳይ ድርጊት የፈፀሙ ሰዎች ጉዳያቸው በህግ ፊት እኩል መታየት እና ተመጣጣኝ የህግ ውሳኔ ማግኘት ነው። የህግ የበላይነት የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ ከአድሎ የፀዳ አካሄድ ያስፈልጋል። ይህም ተመሳሳይ ድርጊት የፈፀሙ ሰዎች በህግ ፊት እኩል መታየት ማለት ነው። በሌላ በኩል የህግ የበላይነት ባለበት ሀገር ዜጎች የሚከተሉትን መብቶች ይኖራቸዋል።

- አንድ በወንጀል የተጠረጠረ ሰው በፍርድ ቤት ጥፋተኝነቱ እስካልተረጋገጠ ድረስ ተጠርጣሪ ተብሎ ይቆጠራል።
- ማንም ሰው በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር አይውልም/ አይታሰርም
- ማንም ሰው ሃብትና ንብረቱን ሊነጠቅ አይችልም፣
- ማንም ሰው ላይ ፍርድ የሚተላለፈው በፍርድቤት ውሳኔ ብቻ ሆኖ የሚሰጠው ውሳኔ ከሰራው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፤
- የህግ የበላይነት በሁሉም ሰው ዘንድ መከበር አለበት።

የፕሮጀክት ስራ

በአከባቢያችሁ የሚገኙትን የፍትህ አካላት በመጠየቅ ጉዳያቸው በፍርድቤት እየታየ ያለ እና ጥፋተኛ መሆናቸው ውሳኔ ያልተሰጠበት ሰዎች ምን እንደሚባሉ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

የህግ የበላይነት መከበር የሚገለፀው ህግን በሁሉም ስፍራ በተመሳሳይ መልኩ በመተግበር ነው። በህግ የበላይነት መርሆ መሰረት ማንም ሰው ስልጣን ቢኖረውም ባይኖረውም፤ ሀብታም ሆነ ደሀ፣ በብሔር፣በሀይማኖት በፖለቲካ ብዙ ሆነ አናሳ፣ ሁሉም ህግን ማክበር አለባቸው።

3 ሰላምና መረጋጋትን ማረጋገጥ

የህግ የበላይነት ሰላምና መረጋጋት እንዲረጋገጥ ያደርጋል። ሰዎች ለግል ደህንነታቸው ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣሉ። የህግ የበላይነት ኖሮ ሰላምና መረጋጋት ሲፈጠር ዜጎች በመንግስት ላይ እምነት ይኖራቸዋል። ሰላምና መረጋጋት

ሲጠፋ ደግሞ ዜጎች በመንግስት ላይ እምነት ያጣሉ። ይህ ደግሞ ህገወጥነት እንዲስፋፋ መንገድ ሊከፍት ይችላል። ይህን ለማስወገድ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

4. የሥልጣን ክፍፍል መኖር

የሕግ የበላይነት ባለባቸው ሀገሮች የስልጣን ክፍፍል በመንግስት አካላት መካከል ይኖራል። የስልጣን ክፍፍል የመንግስት አካላት አንዱ ሌላኛውን እንዲቆጣጠር እና የሀይል ሚዛን እንዲፈጠር በማድረግ የአስተዳደር አካላት ከቁጥጥር ውጪ እንዳይወጡ ያደርጋል። በመሆኑም የስልጣን ክፍፍል መኖር ከህግ የበላይነት መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ነው።

የቡድን ስራ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኃላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

1. የመንግስት የስልጣን ክፍፍል አስፈላጊነት ምንድነው?

2. የመንግስት አካላት ስልጣን የሀይልሚዛኑን ባይጠብቅና አንዱ ሌለኛውን ባይቆጣጠር ምን ሊፈጠር ይችላል?

የፕሮጀክት ስራ

በምትኖሩበት ወረዳ ውስጥ ሦስቱን የመንግስት አካላት በማየት የስራ ድርሻቸው ላይ በቡድን መረጃ በመሰብሰብ ለክፍል አቅርቡ።

4.5. የሕግ የበላይነት እና የግለሰብ የበላይነት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡-

- **የህግ የበላይነት እና የግለሰብ የበላይነትን ትገልፃለህ/ጫለሽ፣**
- **የህግ የበላይነት እና የግለሰብ የበላይነትን ትገመግማለህ/ሚያለሽ፣**
- **የግለሰብ የበላይነትን ትተቻለህ/ሽ።**

በህግ የበላይነት እና በግለሰብ የበላይነት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

የግለሰብ የበላይነት ማለት የመሪዎች ፍላጎትና ድርጊት ከህግና ከህዝብ ፍላጎት ያፈነገጠ ሲሆን ማለት ነው። በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ግለሰቦች ከህግ በላይ ሆነው የታዩበት ጊዜ ነበር። በእንዲህ አይነት ስርአት ውስጥ ግለሰቦች ስልጣንን መከታ በማድረግ ፍላጎታቸውን ለሚሟላት ሰዎችን ሲያስሩ፣ሲያሳድዱ እና ሲያሰቃዩ ፣ንብረታቸውን ሲዘርፉ ቆይተዋል። በመሆኑም ለፖለቲካ ስልጣን

ሲባል ህግን እንደመሳሪያ በመጠቀም ከህግ በላይ እንደሆኑ አሳይተዋል። ለምሳሌ- በንጉሣዊ አስተዳደር ውስጥ ንጉሱ/ንግስትቷ በህግ ያልተገደበ ስልጣን ስላለው/ላት በየትኛውም ህግ አይጠየቅም/አትጠየቅም።

የሕግ የበላይነት ሁሉም ሰው ለህግ ተገዢ መሆኑን እና ከህግ በላይ እንዳልሆነ የሚያመላክት ነው። የህግ የበላይነት የግለሰብ የበላይነት ተቃራኒ ነው። የሕግ የበላይነት በተረጋገጠበት ስርአት ውስጥ የመሪዎች ስልጣን በህግ የተገደበ ነው፡ ፡ ይሄውም የህግ የበላይነት መሰረታዊ መርሆችን ስራ ላይ በማዋል ይገለፃል። የህግ የበላይነት መርሆች ውስጥ ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. ህግ በመሪዎች እና በህዝቡ ላይ እኩል ተፈጻሚ ይሆናል።
2. መሪዎች እና ህዝቡ በህግ ፊት እኩል ናቸው.
3. ማንኛውም ሰው ተገቢውን የህግ ሂደት ተከትሎ በመደበኛ ፍርድ ቤት ፍርድ እስካልተቀበለ ድረስ በግፍ አይቀጣም።
4. አንድ ተከሳሽ በፍርድ ቤት ጥፋተኛ እስካልተባለ ድረስ ነፃና ተጠርጣሪ ተብሎ ይታሰባል።
5. ማንም ሰው ትክክል አይደለም ብሎ ያመነበትን ውሳኔ ይግባኝ ማለት ይችላል።
6. መንግሥት በሕገ መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት መምራት አለበት።
7. የግለሰብ እምነት ወይም ተግባር በሕገመንግሥቱ የተረጋገጡትን መሠረታዊ መብቶች መጣስ የለባቸውም። የሕጉ አተገባበር ሕገመንግስታዊ መሠረት ሊኖረው ይገባል።

የቡድን ስራ

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኃላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡ ፡

1. የህግ የበላይነት እጦት ምን አይነት ችግሮችን ሊያመጣ ይችላል?

2. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ የህግ የበላይነት እጦት መገለጫ ሊሆኑ የሚችሉ ካሉ ግለፁ?

4.6 የህግ የበላይነት እንቅፋቶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡-


- የህግ የበላይነት መርሆ እና አተገባበሩን ትገመግማለህ/ሚያለሽ፤
- የህግ የበላይነት ላይ እንቅፋት የሚሆኑትን ትለያለህ/ሽ።

የህግ የበላይነት እንቅፋቶች ምንድናቸው?

ዴሞክራሲያዊ የሆነ ማኅበረሰብ መገለጫዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የሕግ የበላይነት ነው። የሕግ የበላይነት ህግ የበላይ መሆኑን እና ማንም በህግ ላይ ስልጣን እንደሌለው የሚያሳይ ነው። የህግ የበላይነት በማንነት፣በአከባቢ እና ሌሎች መገለጫዎች ላይ ተመስርቶ አድሎ ሳያደርግ ሁሉንም ዜጋ የሚመለከት ይሆናል። የመንግስት መሪዎችን እና ህዝቡን እኩል ያገለግላል። በህግ የበላይነት ላይ እንቅፋት ከሚሆኑት ውስጥ ጥቅቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

1 ሙስና

ሙስና ማለት የመንግስት እና የህዝብ ሃላፊነትን ለግል ጥቅም ማዋል ማለት ነው። ሙስና የህግ የበላይነት በአግባቡ እንዳይተገበር ትልቅ እንቅፋት ነው። በሥልጣን ላይ ያሉት ሙስናን ለመዋጋት ፍላጎት ከሌላቸው የሕግ የበላይነትን ማስፈን አስቸጋሪ ይሆናል። ሙስናና የሌብነት አመለካከቶችን ለማስወገድ ሥነ ምግባር የጎደላቸው ተግባራትን የሚፀየፍ ማህበረሰብ መፍጠር አስፈላጊ ነው።



ምስል 4.9. የሙስና ድርጊት

2 የግንዛቤ ማነስ

ብዙ ሰዎች መሪዎች ህግ ሲጥሱ የመተችትም ሆነ በሕግ የመጠየቅ ህጋዊ መብት እንዳላቸው አያውቁም። ዜጎች ግንዛቤ ከሌላቸው የመንግስት መሪዎች ህግ ሲጥሱ ዝም ብሎ ለማየት ይገደዳሉ። ስለሆነም የሕግ የበላይነትን በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል አይቻልም። በመሆኑም የግንዛቤ ማነስ በሕግ የበላይነት ላይ እንቅፋት ከሚሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው።

3 ደካማ አመራር

ብቃት የሌላቸው መሪዎች ስልጣናቸውን ለግል ጥቅም ለመጠቀም ያላቸውን አቅም ስለሚገድብባቸው የህግ የበላይነትን ይጠሉታል። እንዲህ አይነት መሪዎች ህዝብን በመበደል ለግል ጥቅማቸው እና ፊላጎታቸው ብቻ ይጨነቃሉ፡ ፡ ስለሆነም የብቃት እጦት በህግ የበላይነት ላይ እንቅፋት ከሚሆኑት መካከል አንዱ ነው።

4 የሀገር ፍቅር ማጣት

የህግ የበላይነት ላይ እንቅፋት ከሚሆኑት ምክንያቶች ሌላኛው የሀገር ፍቅር ማጣት ነው። ሀገሩን የማይወድ ዜጋ ለግል ጥቅሙ ብሎ ህግ መጣሱ አይቀርም። በተጨማሪም በሙስና ከመንግስት መጠቀም ይፈልጋል። ስለዚህ ከድህነት እና ከሙስና የጸዳች ሀገር ለመገንባት ሀገሩን የሚወድ ዜጋ ሙስናና ህገወጥነትን የሚፀየፍ ትውልድ ማፍራት ያስፈልጋል።

የምዕራፉ ማጠቃለያ

የህግ የበላይነት ከዴሞክራሲ መሰረታዊ መርሆዎች ውስጥ አንዱ ነው። ዜጎች በህግ ፊት እኩል ናቸው የሚለው እውን የሚሆነው የህግ የበላይነት ሲኖር ነው። በዚህ አስተሳሰብ ዜጎች ሁሉ በህግ ፊት እኩል ናቸው ማለት ነው። ዋና ዋናዎቹ የሕግ ምንጮች በአራት ሊከፈሉ ይችላሉ። እነሱም ሕገ መንግሥት፣ እሴት፣ ሃይማኖትና ሞራል እና የሕግ አውጭው አካል ናቸው።

የህግ የበላይነት በአግባቡ ሲተገበር ዜጎች መብታቸውንና ነጻነታቸውን ጠንቅቀው ይረዳሉ። በዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ የህግ የበላይነት ከግለሰብ የበላይነት ይለያል። በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሕግ በመሪዎች ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የቆየበት ጊዜ ነበር። በሂደት ወደ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት የመንግስት አስተዳደር እየተቀየረ መጣ።

የህግ የበላይነት በመንግስት መሪዎችና ተቋማት ላይ ተፅእኖ አለው። የህግ የበላይነትን በአግባቡ እንዳይተገበር ከሚያደናቅፉ ምክንያቶች መካከል ጥቂቶቹ ሙስና፣ የግንዛቤ ማነስ፣ ደካማ አመራርና የሀገር ፍቅር ማጣት ናቸው። የሕግ የበላይነት በተገቢ ሁኔታ ስራ ላይ እንዲውል ገለልተኛ ፍርድ ቤት፣ ኃላፊነት የሚሰማው አመራር፣ የአገር ፍቅር ስሜት እና የእውቀት መስፋፋት አስፈላጊ ናቸው።

የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

- ሙስና፡ የህዝብና የመንግስትን ስልጣን ለግል ጥቅም ማዋል ማለት ነው።
- ፍትህ፡ አድሎ የሌለበትና በህግም ሆነ በሞራል ትክክል የሆነ አካሄድ ማለት ነው።
- የህግ አውጭው አካል፡ ከመንግስት አካላት ውስጥ ህግ የማውጣት ስልጣን ያለው ማለት ነው።
- ህግ ተርጓሚ አካል፡ ከመንግስት አካላት ውስጥ ህግ የመተርጎም ስልጣን ያለው ማለት ነው።
- የህግ የበላይነት፡- ማንም ሰው በህግ መገዛትና ከህግ በላይ አለመሆንን የሚያሳይ ነው።
- የግለሰብ የበላይነት፡ ለፖለቲካ ስልጣን ሲባል ህግን እንደመሳሪያ መጠቀምና በህግ አለመገዛት።

የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

ክፍል 1፡ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት"ትክክል ካልሆኑ "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ።

1) የህግ የበላይነት በሰፈነበት ሁሉንም ዜጎች ማሳተፍ የግድ አይደለም።
2) የህግ የበላይነት ባለበት ሀገር ውስጥ ማንም ሰው ለፈፀመው ጥፋት ተጠያቂ ይሆናል።
3) በዴሞክራሲያዊ ሀገር ውስጥ ህገ መንግስት የህጎች ሁሉ የበላይ ነው።
4) እሴት ከህግ ምንጮች ውስጥ አንዱ ነው።
5) ስልጣንን ያለመገደብ መጠቀም የህግ የበላይነት መከበር መገለጫ ነው።

ክፍል II፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጥ/ጪ።

1) የህግ የበላይነትን በተመለከተ ከሚከተሉት አንዱ እውነት አይደለም።
   ሀ) አድሎአዊ አሰራርን ያስቀራል
   ለ) የፍትህ አካላት ከሌሎች ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ውጭ እንዲሰሩ ያግዛል
   ሐ) የሀገሪቱ ዜጎች የመናገር እና የመፃፍ መብት እንዳይኖራቸው ያደርጋል
   መ) የሀገሪቱ ዜጎች ተከባብረው በእኩልነት እንዲኖሩ ያደርጋል
2) የህግ የበላይነት በምን ይረጋገጣል?
   ሀ) ሰላምና መረጋጋት በመኖሩ
   ለ) ሕግን በእኩልነት ተግባራዊ በማድረግ
   ሐ) ገለልተኛ ፍርድ ቤት መኖሩ
   መ) ሁሉም መልስ ነው
3) ከሚከተሉት ውስጥ በሕግ የበላይነት ላይ እንቅፋት የማይሆነው የቱ ነው?
   ሀ) ሙስና
   ለ) የግንዛቤ እጦት
   ሐ) ደካማ አመራር
   መ) ጠንካራ የሀገር ፍቅር

ክፍል III ፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጥ/ጪ።

1) ኢትዮጵያ የህግ ሀገር ናት እንጂ የግለሰቦች ሀገር አይደለችም ማለት ምን ማለት ነው?
2) የህግ የበላይነት እና የዴሞክራሲ ግንኙነት ምንድነው?

ምዕራፍ 5

ሰብዓዊ መብቶች

መግቢያ

በምዕራፍ አራት ስለ የህግ የበላይነት መሰረታዊ ፅንሰ-ሀሳብ እና ተዛማጅ ጉዳዮችን ተምረሀል/ሻል። በዚህ የትምህርት ክፍል ውስጥ ደግሞ ስለሰብዓዊ መብት መሰረታዊ ፅንሰ-ሀሳብ እና ተያያዥ ይዘቶችን ትማራለህ/ሪያለሽ። በመሆኑም ይህ ምዕራፍ የሰብዓዊ መብቶች ገፅታዎች፤ የሰብዓዊ መብት መከበር አስፈላጊነት፤ ሀገራት ሰብዓዊ መብቶችን የማስጠበቅ ቀዳሚ ኃላፊነት እንዳለባቸው፤ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችና ሰነዶችን እንዲሁም መንግስታት ሰብዓዊ መብቶችን በመተግበር ረገድ ስላላቸው ሚና በአጭሩ ያብራራል።

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

- የሰብአዊ መብት ጽንሰ-ሀሳብን መግለፅ፤
- የሰብአዊ መብቶች መገለጫ ባህሪያት ማብራራት፤
- የሰብአዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነትን መግለፅ፤
- ሀገራት ሰብዓዊ መብቶችን የማስጠበቅ ቀዳሚ ኃላፊነት ማወቅ፤
- የሰብአዊ መብት ስምምነቶችን መዘርዘር፤
- መንግስታት ሰብአዊ መብቶችን በመተግበር ረገድ ስላላቸው ሚና ማብራራት።

5.1. የሰብአዊ መብት ጽንሰ-ሀሳብ

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች፡

- የሰብዓዊ መብት ጽንሰ-ሀሳብን ትገልጻለህ/ሚለሽ፤
- የሰብዓዊ መብቶች ምሳሌዎችን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፡፡

ሰብዓዊ መብት ማለት ምን ማለት ነው? ምንጫቸውስ?



ቻርት 5.1 ሰብዓዊ መብቶች (ይሻሻል)

ሰብዓዊ መብት አንድ ሰው በተፈጥሮ ሰው በመሆን ብቻ የሚያገኛቸው መሰረታዊ መብቶች ናቸው፡፡ ሰብዓዊ መብቶች ማንኛውም ሰው ያለ አድልዎ የማግኘት መብት እንዳለው የሚያሳይ ነው፡፡ በዓለም ላይ ያሉ ሁሉም ሰዎች ከልደት እስከ ሞት ድረስ ያላቸው መሠረታዊ መብቶች እና ነጻነቶች መሆናቸውን ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ሰብአዊ መብቶች የሚገለጹት ለሰብአዊ ሕይወት እና ክብር መከበርን የሚያንፀባርቁ እሴቶች ናቸው፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ዋና ዋና ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- በህይወት የመኖር መብት፤
- የነፃነት መብት፤
- የእኩልነት መብት፤
- ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት፤
- የግላዊነት መብት፤
- የሃይማኖት ነፃነት፤
- የሃሳብ ነፃነት



የቤት ስራ

1. የሰብዓዊ መብት ፅንሰ-ሀሳብን አብራራ
2. ዋና ዋና የሰብዓዊ መብቶች ምሳሌዎችን በመውሰድ ለክፍል ተማሪዎች ገለፃ አድርግ

5.2. የሰብዓዊ መብቶች መገለጫ ባህሪያት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች

- የሰብአዊ መብቶች መገለጫ ባህሪያትን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤
- የሰብአዊ መብቶች ተፈጥሮአዊ ገፅታዎች ታብራራለህ/ሪለያሽ።



የሰብዓዊ መብቶች ምን ምን መገለጫ ባህሪያት አላቸው?

የሰው ልጅ የመወለድ መብቶች የሆኑት የሰብዓዊ መብቶች በሚከተሉት መለያ ባህሪያት ይገለጣሉ።

1. ሰብዓዊ መብቶች ሁለንተናዊ ናቸው

ሰብዓዊ መብቶች ሰው በመሆናችን ብቻ የምናገኛቸው መብቶች ናቸው።እነዚህ ሁለንተናዊ መብቶች ዘር፣ቀለም፣ጾታ፣ወይም ማህበራዊ ምንጭ፣ሃይማኖት፣ቋንቋ፣ብሔር፣ዕድሜ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣አካል ጉዳተኝነት ወይም ሌላ ማንኛውም ልዩነት ሳይገደብ ለሁላችንም ተላልፈው የተሰጡ ናቸው። የሰብዓዊ መብት ሁለንተናዊነት በሁሉም ቦታ እና በማንኛውም ጊዜ መከበር እና ጥበቃ መደረግ አለበት።



ስእል:5.2 የሰብዓዊ መብቶች ሁለንተናዊነት

የግንዛቤ ጥያቄ

ሰብዓዊ መብቶች ሁለንተናዊ ናቸው ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አብራሩ።።

2. ሰብዓዊ መብቶች ተፈጥሯዊ ናቸው።።

ሰብዓዊ መብቶች በተፈጥሮ የሚገኙ መብቶች ናቸው።። ይህ ማለት ማንም መብት ሊሰጥ ወይም ሊወስድ አይችልም ማለት ነው።። .ሰብዓዊ መብቶች የሚገዙ፣የሚሰጡ የሚወረሱ ሳይሆን ሰው በመሆናችን ብቻ የምናገኛቸው መብቶች ናቸው።። የሰው ልጅ ክብር ምልክቶች ናቸው።። ለምሳሌ በህይወት የመኖር መብት ልንገዛ ወይንም መንግሥት የሚሰጠን አይደለም፣ምክንያቱም የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ መብት ስለሆነ።።

3. ሰብዓዊ መብቶች የማይገፈፉ ናቸው።

ሰብዓዊ መብቶች ፍፁም እና መገፈፍ የሌለባቸው ናቸው። ማንም ማንንም እነዚህን መብቶች ሊነፍግ አይችልም፣ እንዲሁም ማንም ሰው እነዚህን መብቶች በራሱ/ራሷ አሳልፎ መስጠት አይችልም። የተለዩ ሁኔታዎች እስካልተፈጠረ እና ህጋዊ ሂደቶች ካልተከተሉ በስተቀር ሊወሰዱ አይገባም። ለምሳሌ አንድ ሰው በፍርድ ቤት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ የነፃነት መብቱ ሊገደብ ይችላል።

4. ሰብዓዊ መብቶች የማይነጣጠሉ እና እርስ በርስ የሚደጋገፉ ናቸው

ሰብዓዊ መብቶች የማይነጣጠሉ እና እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው። ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰብዓዊ መብት በሌሎች ሰብዓዊ መብቶች አጠቃቀም ላይ የተመሰረተ ነው። ከእነዚህ መብቶች ውስጥ አንዱን መጣስ በሌሎች ሰብዓዊ መብቶች አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል። ለምሳሌ የመኖር መብት የምግብ መብትን እና ጥሩ ኑሮ የመኖር መብት ጋር ይያያዛል።

አንድ ሰው መሠረታዊ የትምህርት መብት ከተነፈገው ፍትህ የማግኘት እና በማህበረሰብ ጉዳዮች ውስጥ የመሳተፍ መብቱ ሊደናቀፍ ይችላል። ለዚህ ነው ሰባዓዊ መብቶች የማይነጣጠሉ እና እርስ በርስ የሚደጋገፉ ናቸው የሚባለው፡ ፡ ባጠቃላይ የሰብዓዊ መብቶች ባህሪያት ሁለንተናዊ፣ ተፈጥሮአዊ፣ የማይገፈፉ እና እርስ በርስ የሚደጋገፍ መሆናቸው ነው።



የቡድን ስራ

የሰብዓዊ መብቶች ዋና ዋና የሆኑ ባህሪያት ላይ በቡድን በመወያየት ለክፍል ገለፃ አድርጉ

5.3. ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር አስፈላጊነት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተው የመማር ብቃቶች

- የሰብዓዊ መብቶች አስፈላጊነት ትዘረዝራለህ/ሽ፣
- የሰዓዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት ታብራራለህ/ሽ።



የሰብዓዊ መብቶች መከበር ለምን ያስፈልጋል?

የሰብዓዊ መብት መከበር የዜጎችን በራስ መተማመን በማጎልበት በማህበረሰቡ እና መንግስት መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉትን ፍራቻ እና ጥርጣሬ ለማስቀረት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ይህም በማህበረሰቡ እና መንግስት መካከል መተማመን በመፍጠር ዜጎች ለጋራ ጥቅም እንዲቆሙ ቅድመ ሁኔታን ያመቻቻል፡፡ በመሆኑም የሰብዓዊ መብት መከበር በማንኛውም ሁኔታ፤ቦታ እና ደረጃ የማህበረሰቡን ግንኙነት በማጠናከር ሂደት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡ ስለዚህ የሰብዓዊ መብቶች መከበር በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም፡-

- የሀገሪቱን ፍትህእና ልማት ለማረጋገጥ ፤
- አሳማኝ ልማትና ደህንነትን ለማረጋገጥ፤
- የዴሞክራሲ ስርአትግንባታን ለጎልበት፤
- የህዝብን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት፤
- የሴቶች፣ ህጻናትእና የአካል ጉዳተኞችን መብት ለማስጠበቅ፤
- ዜጎች እኩል የስራ እድል የማግኘት መብት ለማስከበር፤
- የዜጎችን እኩል የትምህርት እድር መብት ለማረጋገጥ

በአንድ ሀገር ውስጥ የዜጎች መብትና ጥቅም በእኩልነት ካልተከበሩና አድሎዓዊ ድርጊቶች ካሉ ዘላቂ ሰላምና ልማት ማስመዝገብ የማይታሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ዴሞክራሲ፣ ፍትህ እና እድገትን ለማረጋገጥ ሰብዓዊ መብቶች መከበር አለባቸው፡ :



የቡድን ስራ

1. ለዜጎች እኩል ጥበቃ ካልተደረገ ምን ሊፈጠር ይችላል? –
2. የዜጎች መብት መከበር አስፈላጊነት ምንድነው

5.4. የሰብዓዊ መብቶችን የማስጠበቅ ሀላፊነቶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተው የመማር ብቃቶች

- የሰብአዊ መብቶችን መጠበቅ የማን ሀላፊነት እንደሆነ ትለያለህ/ሽ፤
- የሰብአዊ መብቶችን በማስጠበቅ ረገድ የዜጎችን ድርሻ ትገልፃለህ/ጫለሽ፡፡



ሰብዓዊ መብቶችን የማስጠበቅ ቀዳሚ ኃላፊነት ያለው ማነው?

ለረጅም ጊዜ ሰብዓዊ መብቶች የአንድ ሀገር የውስጥ ጉዳይ ተደርገው ይቆጠሩ ነበር። ይህም ማለት ሌሎች መንግስታት እና አለም አቀፍ ማህበረሰብ ጣልቃ እንዳይገቡ ተከልክሏል። እንደ ዘር ማጥፋት በመሳሰሉ የሰብዓዊ መብት ረገጣዎችም ቢከሰቱ እንኳን ጣልቃ መግባት አይችሉም። በጊዜ ሂደት ይህ አካሄድ ተቀይሮ የሰብዓዊ መብትን ለመጠበቅ የወጡ መርሆዎች የሰብዓዊ መብቶችን መጠበቅ ሃላፊነት ሰጠ:: የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባላት (የሀገር መሪዎች እና መንግስታት) የሰብዓዊ መብቶችን የመጠበቅ ሃላፊነትን መሰረት ያደረጉ መርሆችን መስከረም 16 ቀን 2005እ.ኤ.አ በሙሉ ድምጽ አጽድቀዋል።

ይህ መርህ ዜጎቹን ከዘር ማጥፋት፣ ከጦርነት ወንጀሎች፣ ብሔር ተኮር ወንጀሎችና በሰው ልጆች ላይ ከሚፈጸሙ ወንጀሎች የመጠበቅ ኃላፊነት የእያንዳንዱ መንግሥት መሆኑን ይገልፃል። በዚህ መርህ መሰረት ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል እንደመሆኗ መጠን ህዝቦቿን ከዘር ማጥፋት፣ የጦር ወንጀል፣ የዘር ማጽዳት ወንጀሎች ወዘተ የመጠበቅ ሃላፊነት አለባት::

የሰብዓዊ መብት ጥበቃን በተመለከተ ሁሉም የአለም መንግስታት እኩል ሃላፊነት እንደሚወስዱ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን፣ አንድ መንግስት ህዝቡን ከከባድ አደጋዎች መጠበቅ ካልቻለ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የመግባት እና ሁኔታውን ያገናዘበ እርምጃ መውሰድ የሞራል ግዴታ አለበት።



የቤት ስራ

1. ሰብዓዊ መብቶችን የሚጥሱ ድርጊቶች ሲከሰቱ የመቆጣጠር እና እርምጃ መውሰድ የማን ሀላፊነት ነው?

5.5. የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች

- ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነትን ትጠቅሳለህ/ሻለሽ

- የአፍሪካ አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነድ ታውቃለህ/ቂያሽ
- የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ

የሰብዓዊ መብት ስምምነቶች የምታቀውን ጥቀስ?

ስምምነቶች፣መግለጫዎች፣ፕሮቶኮሎች እና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ህጎች እና በአጠቃላይ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ የህግ ምንጭ ሆነው የሚያገለግሉ ድንጋጌዎች የሰው ልጅ የሰብዓዊ መብቶች መሳሪያዎች ተብለው ይጠራሉ።

የሰብዓዊ መብት ሰነዶች ከአለም አቀፍ እስከ ሀገር አቀፍ ደረጃ ባሉ የተለያዩ አካላት ሊወሰዱ ይችላሉ። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል ዓለም አቀፋዊ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች፣ አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች እና ሀገራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች አሉ።



ስዕል: 5.4 አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች የፊርማ ሂደት

ብዙ ሀገራት አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ፈርመዋል። በሌላ አነጋገር፣ እንዲህ ዓይነት ስምምነቶች ሲታወጅ፣ ብዙ ሀገራት ይሳተፋሉ እና ይስማማሉ። ለምሳሌ፣ እ.ኤ አ. የ1948ቱ ሁለንተናዊ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) የሰብዓዊ መብት ታሪክ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች ውስጥ አንዱ ነው። ለሁሉም ሀገራት እና ህዝቦች የጋራ ስኬት መለኪያ ሆኖ ያገለግላል። አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነድ (UDHR) 30 አንቀጾችን ይዟል።



ስዕል 5.5 በአፍሪካ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች የፊርማ ሂደት

በአፍሪካ ደረጃ የሰብዓዊ መብቶችን በማስተዋወቅ እና በመጠበቅ ረገድ አፍሪካዊ የሰብአዊ መብት ሰነዶች ጠቃሚ እየሆኑ መጥተዋል። የአፍሪካ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች (ለምሳሌ ስምምነቶች፣መግለጫዎች) የአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መመዘኛዎችን አካባቢያዊ ለማድረግ የሚረዱ እና የአፍሪካን ልዩ ሰብዓዊ መብቶች ትብብር የሚያንፀባርቁ ናቸው። እ.ኤ.አ. በ1981 የፀደቀው የአፍሪካ የሰብዓዊ መብቶች ቻርተር የአፍሪካ ቀዳሚ አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች መሳሪያ ነው። የአፍሪካ ቻርተር ሁለንተናዊ የሰብዓዊ መብቶች መስፈርቶችን እና መርሆዎችን እንዲሁም የአፍሪካን ወጎች፤ በጎነት እና እሴቶችን ያጠቃልላል። ይህ ቻርተር 68 አንቀፆች አለው።

የሰብአዊ መብቶች እና ነጻነቶች በ1995 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ውስጥ አንድ ሶስተኛው ስለ ሰብዓዊ መብቶች ተደንግጓል። በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ውስጥ የተገለጹት መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው የአለም አቀፍ ሰብዓዊ መብት ህጎች፣ ሰነዶች፣ ስምምነቶችና መርሆዎች መሰረት የተተረጎመ ነው። የብሄራዊ ሰብዓዊ መብት ሰነዶችን ተግባራዊ ለማድረግ ሚና የሚጫወቱ የተለያዩ ተቋማት በኢትዮጵያ አሉ። እንደ ምሳሌ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና እንባ ጠባቂ ተቋም መውሰድ ይቻላል።



ስዕል: 5.6 የኢትዮ፝ያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን እና እንባ ጠባቂ ተቋም

የቡድን የፕሮጀክት ስራ

በአለም አቀፍ፤በአፍሪካ አህጉር እና በኢትዮ፝ያ ደረጃ የተፈረሙ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች ላይ በቡድን መረጃ በማሰባሰብ ለክፍል ተማሪዎች ሪፖርት አቅርቡ

5.6. የሰብዓዊ መብቶችን በማረጋገጥ ረገድ የመንግስት ሚና

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተው የመማር ብቃቶች

- የሰብዓዊ መብቶች መረጋገጥ ምንነት ትገልፃለህ/ጫለሽ፤
- የሰብዓዊ መብቶች ለማረጋገጥ የመንግስት ሚናን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፡፡

የሰብዓዊ መብቶች በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ የምታውቀውን የመንግስት ሚና ጥቀስ

የየሀገራት መንግስታት ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር፤መጠበቅ እና ማስከበር ቀዳሚ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ አብዛኞቹ አገሮች ከቅርብ አሥርተ ዓመታት ወዲህ ዋና ዋና የሰብዓዊ መብት ስምምነቶችን ፈርመዋል፡፡ አንድ መንግሥት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነትን ሲፈርም በስምምነቱ ውስጥ የተካተቱትን መብቶች የማክበር፣ የመጠበቅ እና የማስከበር ኃላፊነትን ይቀበላል፡፡ ይህም መንግስት ምንም አይነት እርምጃ መውሰድ ወይም በስምምነቱ የተረጋገጡትን መብቶች የሚጥስ እርምጃ ሊወስድ እንደማይችል ያመለክታል፡፡

የግለሰቦች ሰብዓዊ መብቶች እንዳይጣሱ መንግስት አስቀድሞ እርምጃ መውሰድ አለበት። ለምሳሌ አንድ ሰው በወንጀል ሊታሰር ይችላል፤ ነገር ግን ይህ እስረኛ በማንም ሰው አካላዊ ድብደባ ወይም እንግልት ሊደርስበት አይገባም።

መንግስት የዜጎችን ደህንነት ከማንኛውም አይነት የሽብር ጥቃት መጠበቅ አለበት። ይህም ህጎችን ከማውጣት ጀምሮ ሰብአዊ መብቶችን በብሄራዊ የትምህርት እና የመረጃ ዘመቻዎች እስከ ማስተዋወቅ ያለውን ማንኛውንም ነገር ሊያካትት ይችላል። ለምሳሌ የትምህርት መብት



የቤት ስራ

1. ሰብዓዊ መብትን ለማስከበር የፖሊስ፤የፍርድ ቤት እና የፍትህ አካላት ሚና ዙሪያ ቤተሰብህን በመጠየቅ ለክፍል አቅርብ

ማጠቃለያ

ሰብዓዊ መብት ማለት ሀይማኖት፣ ቋንቋ፣ ጾታ፣ ዘር፣ ጎሳ ወይም ሌሎች ልዩነቶች ሳይለዩ ለሁሉም ሰው የተረጋገጡ ናቸው። ይህም ሰው መሆን ብቸኛው የሰብዓዊ መብት መስፈርት ነው። የምንፈልገውን አይነት ማህበረሰብ ለመፍጠር ኢትዮጵያን ጨምሮ ሁሉም የአለም ሃገራት የሰብዓዊ መብት አስተሳሰቦችን ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ነው። ሰብዓዊ መብቶችን መተግበር እና ማክበር ኢትዮጵያውያን ዜጎችን ስልጣን የሚያጎናፅፍ ሲሆን አገራችን በተለያዩ ጊዜያት በሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት ለገጠሟት ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል። የሰብዓዊ መብት መከበር የረዥም ጊዜ ሰላምና ልማት ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ማስታወስም አስፈላጊ ነው።

ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሰብዓዊ መብቶችን የማስከበር የሞራል ግዴታ ቢኖርበትም መንግስታት ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር፣መጠበቅ እና ማስከበር ያለባቸው ቀዳሚ ተዋናዮች ናቸው።ይህም ዘላቂ ሰላም እና ልማት ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፆኦ አለው።ሁለንተናዊነት፣ ተፈጥሮአዊነት፤ የማይገፈፉ እና እርስ በርስ መደጋገፋቸው ዋና ዋና የሰብዓዊ መብቶች ባህሪያት ናቸው።

የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

ክፍል አንድ፡ የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት ብለህ/ሽ ፃፍ/ፊ።

1. ሰብዓዊ መብቶች ለሁሉም ሰው ተፈጥሯዊ የሆኑ መብቶች ናቸው።
2. ለዜጎች ሰብዓዊ መብት የሚሰጠው መንግስት ነው።
3. ሁለንተናዊ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) የታወጀው እ. ኤ. አ በ1948 ነበር።
4. እ. ኤ. አ በ1995 የወጣው የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንድ ሶስተኛው ስለሰብዓዊ መብቶች ያተኮረ ነው።
5. እ. ኤ. አ የ1948ቱ ሁለንተናዊ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) 30 አንቀጾችን ይዟል።

ክፍል II፡ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ

1. ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው ሰብዓዊ መብት ያልሆነው?
   ሀ. የፖለቲካ መብቶች ለ. የዜጎች መብቶች ሐ.የኢኮኖሚ መብቶች መ. መልስ አልተሰጠም
2. ከሚከተሉት ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች መገለጫ የትኛው ነው?
   ሀ. ሁለንተናዊነት ለ. የማይገፋፉ ሐ. እኩልነት
   መ. ሁሉም መልስነው
3. የሰብዓዊ መብት ተፈጻሚነት በሁሉም ቦታ ላይ እና በማንኛውም ጊዜ የሚያመለክተው
   ሀ. እኩልነት ለ. ሁለንተናዊነት ሐ. የማይደፈር
   መ. መደጋገፍ
4. ሰብዓዊ መብቶችን የማስጠበቅ ቀዳሚ ኃላፊነት ያለበትን አካል የቱ ነው።
   ሀ. መንግስት ለ.ህዝብ ሐ. የሰብዓዊ መብት ተቋማት
   መ. ሁሉም
5. ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነድ ነው?
   ሀ. ሁለንተናዊ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ
   ለ. የአፍሪካ የሰብዓዊ እና ህዝቦች መብቶች ቻርተር
   ሐ. የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ስለ ሰብዓዊ መብቶች
   መ. ሁሉም

ምዕራፍ 6

የማህበረሰብ ተሳትፎ

መግቢያ

በምዕራፍ አምስት ስለ ሰብአዊ መብቶች መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳቦች ተምረሃል/ሻል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ስለ መሰረታዊ የማህበረሰብ ተሳትፎ ትማራለህ/ሽ። በዚህ መሰረት የማህበረሰብ ተሳትፎ ፅንሰ- ሀሳብ፣የማህበረሰብ ተሳትፎ ጥቅሞች፣የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጥቅሞች እንዲሁም የማህበረሰብ ተሳትፎ ገፅታዎችን በቅደም ተከተል ትማራለህ/ሪያሽ፡

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

- የማህበረሰብ ተሳትፎ ትርጉም/ፅንሰ- ሀሳብ መግለፅ፣
- የማህበረሰብ ተሳትፎ ጥቅሞችን ማብራራት፣
- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጥቅሞችን መዘርዘር፣
- የማህበረሰብ ተሳትፎ ገፅታዎችን መለየት።

6.1 የማህበረሰብ ተሳትፎ ፅንሰ- ሀሳብ

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃት፤

- የማህበረሰብ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትገልፃለህ/ጫለሽ፤
- የማህበረሰብ ተሳትፎን ጽንሰ ሃሳብ ታብራራለህ/ሪያለሽ፤
- የማህበረሰብ ተሳትፎን ታደንቃለህ/ቂያለሽ።

የማህበረሰብ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት ነው?

የማህበረሰብ ተሳትፎ 'ማህበረሰብ' እና 'ተሳትፎ' የሚሉትን ቃላት የምያጣምር ሆኖ፣አጽንኦቱን ከግለሰብ ወደ የጋራ የሚያደርግ ነው። ብዙ ትርጓሜዎች ቢኖሩም፣የማኅበረሰብ ተሳትፎ በዴሞክራሲያዊ መርህ ላይ የተመሰረተ ሆኖ በማኅበረሰብ አቀፍ ጉዳይ የምጎዳ ማንኛውም ሰው በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የራሱን አስተያየት መስጠት አለበት የሚል ነው። የማህበረሰብ ተሳትፎ መንግስታት እና ድርጅቶች የረዥም ጊዜ ግንኙነቶችን እና ውስብስብ ጉዳዮችን ለመፍታት ማህበረሰብን ማዳመጥ እና አብሮ መስራትን ያካትታል።

የማህበረሰብ ተሳትፎ የማህበረሰቡን ደህንነቶች የሚነኩ ጉዳዮችን ለመፍታት ከማህበረሰቡ አባላት ጋር አብሮ የመስራት ሂደት ተብሎ ሊገለፅ ይችላል። እንደ እውነቱ ከሆነ፣የማህበረሰብ ተሳትፎ ባለሙያዎችን፣የመንግስት ባለስልጣናትን፣አገልግሎት ሰጪዎችን እና የማህበረሰቡ አባላት አጋርነት እንዲመሰርቱ የሚጠይቅ የረዥም ጊዜ ሂደት ነው። ስለዚህ የማህበረሰብ ተሳትፎ ከመረጃ አቅርቦት አንፃር በሁለት መንገድ የሚካሄድ ሂደት ነው። ይህም ማለት ከመንግስት አካል ወደ ማህበረሰቡ የሚደርስ የአንድ መንገድ የመረጃ ፍሰት አይደለም። በዚህ መሠረት ዜጎች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ንቁ ተሳትፎ ሲያደርጉ "ተሳተፉ" ይባላል።



ምስል 6.1 በጋራ ጉዳዮች ላይ የማህበረሰብ ውይይት

የቡድን ሥራ

 የማህበረሰብ ተሳትፎ ፅንሰ ሀሳብ ላይ በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።።

6.2 የማህበረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊነት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃት፤

- የማህበረሰብ ተሳትፎን አስፈላጊነት ታብራራለህ/ሽ፤
- የማህበረሰብ ተሳትፎ ዋና ምክንያቶችን ትዘረዝራለህ/ሽ፤

 የማህበረሰብ ተሳትፎ ለምን ያስፈልጋል?

ያለ ማህበረሰብ ተሳትፎ የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ልማት ጥረቶች ሊሳኩ አይችሉም። ለዚህም ነው ዜጎች ችግሮችን በመለየት እና መፍትሄዎችን በማቅረብ በንቃት መሳተፍ ያለባቸው። የማህበረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊ የሆነባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፣ በዚህ የክፍል ደረጃ ግን፣ የሚከተሉትን ብቻ እንመለከታለን።

1. ሀገር በቀል እውቀቶችን ለመጠቀም

 ሀገር በቀል እውቀት ማለት ምን ማለት ነው?

ሀገር በቀል እውቀት ማለት በማህበረሰቡ ነባር እውቀት፤ልምድ እና እሴት ላይ የተመሠረተ ሆኖ የህብረተሰቡ የጋራ ሀብት ነው ማለት ይቻላል፡ ፡ ማህበረሰቡን በአግባቡ በማሳተፍ እና በመጠየቅ አዳዲስ ሀገር በቀል ሃሳቦችን እና ልምዶችን ማዳበር ይቻላል። ይህ ከተደረገ ሰዎች የሂደቱ ዋና አካል እንደሆኑ ሊሰማቸው ይችላል። በተጨማሪም ከተለያየ ህዝብ እና ሀገር በቀል እውቀት ላይ የተመሰረቱ መፍትሄዎች ተግባራዊ እና ውጤታማ ናቸው። እንዲሁም የፕሮጀክቶችን ወይም እቅዶች በሰፊው ተቀባይነት የማግኘት እድልን ይጨምራል። አገራችን በዚህ ሁኔታ በሀገር በቀል ዕውቀትና ክህሎት የበለፀገች ናት።።

በዚህ መሠረት እንደ የእርከን ሥራ፣ የብረታብረት ስራ፤ የሸክላ ስራ፤ከቀንድ የቅርፃቅርፅ ሥራ፣ ከድንጋይ፣ ከጭቃ ቤት መስራት፤የቤት ዕቃዎችን በማምረትና መሸጥን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል። ስለዚህ የእንደዚህ

አይነት የአካባቢ ዕውቀት እና ክህሎቶችን ለመጠቀም የማህበረሰብ ተሳትፎ በጣም አስፈላጊ ነው።

የፕሮጄክት ሥራ



በአካባቢያችሁ ያለውን ሀገር በቀል እውቀቶችን አስመልክቶ መረጃ በመሰብሰብ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

2. የመተማመን ስሜት ለመገንባት



የማህበረተሰብ ተሳትፎ መተማመንን በምን መልኩ መገንባት ይችላል?

የማህበረሰብ ተሳትፎ በህዝብ እና በመንግስት መዋቅር መካከል መግባባት እንዲኖር ያደርጋል።እንዲሁም በአቅራቢያ ያለው የመንግስት መዋቅር እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ምን እየሰሩ እና ሊሰሩ እንዳቀዱ ለተሳታፊዎች ለማሳውቅ ይረዳል። ይህ መስተጋብር በአካባቢው ማህበረሰብ፤በመንግስት እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች መካከል መተማመንን ይጨምራል።


አሁን ባለንበት ዘመን መረጃ በተለያዩ መንገዶች ሊገኝ እንደሚችል የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ የመረጃው ምንጭ በሚገባ ካልተረጋገጠ በተለያዩ ወገኖች መካከል ያለው መተማመን ሊጠፋ ይችላል። መተማመን እንዲገነባ ግልፀኝነትና ሀቀኝነት ትልቅ ሚና አላቸው። ስለዚህ፤መንግስት እና የማህበረሰብ ተቋማት በሚሰሩት ሥራ ላይ ግልፅ የሆነ መረጃ ለማህበረሰቡ በመስጠት በመካከላቸው ያለውን መተማመን ማሳደግ ወሳኝ ነው።

3. ዜጎችን ለማብቃት

የማህበረሰብ ተሳትፎ ዜጎች በራሳቸው ማህበረሰብ ውስጥ ሊከሰቱ ለሚችሉ ነገሮች ሃላፊነት እንዲወስዱ እድል ይሰጣቸዋል። እንዲሁም ዜጎች በአካባቢያቸው ወይም በማህበረሰባቸው ውስጥ የሚከሰቱ የተለያዩ ጉዳዮችን እንዲፈቱ ያበረታታል። በተለያየ ምክንያት ከተሳትፎ የተገለሉ ቡድኖችም በማህበረሰባቸው ጉዳይ ውስጥ የመሳተፍ እድል እንድያገኙ ያስችላቸዋል። በአጠቃላይ፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች ውስጥ አንዱ ከሁሉም የህይወት ዘርፍ የተውጣጡ ሰዎችን ለጋራ አላማዎች እንዲሰሩ የጋራ መድረክ ማዘጋጀት ነው።

4. ችግሮችን ለመፍታት

በማህበረሰብ ተሳትፎ ምክንያት የዜጎች እውቀት እና ችግሮችን የመፍታት ክህሎቶች ይሻሻላሉ። በዚህ መልኩ፤ተሳታፊዎች ስለ ማህበረሰባቸው ጉዳይ ሁሉን አቀፍ ግንዛቤ በማግኘት የግንኙነት እና የውሳኔ አሰጣጥ ክህሎቶችን ለመለማመድ እድል ያገኛሉ። በመሆኑም የማህበረሰብ ተሳትፎ ተሳታፊዎች የችግር አፈታት ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ እና አንድን ጉዳይ ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመርመር ትክክለኛ ውሳኔ በመስጠት ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ያስችላቸዋል።



ምስል 6.2 ችግሮችን ለመፍታት በዜጎች ንቁ ተሳትፎ

የቤት ሥራ

1. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ዘርዝር/ሪ።
2. እነኚህን ችግሮች መፍታት የማን ድርሻ ነው ብለህ ታስባለህ/ቢያለሽ?

6.3 የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጥቅሞች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃት፤

- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምንነት ትገልፃለህ/ጫለሽ፤
- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጥቅሞችን ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤
- በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ውስጥ ትሳተፋለህ/ፊያለሽ::—

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምንድነው? ጥቅሞቹስ?

በጎ ፈቃደኝነት የማህበረሰብ አገልግሎት ሆኖ በግል ወይም በጋራ ጊዜን፣ገንዘብን፤ጉልበትን፤ጥረትን፤ እውቀትን እና ችሎታን ለህብረተሰቡ ፍላጎት ወይም ግብ ያለክፍያ የሚደረግ አስተዋፅኦ ነው። እንዲሁም አንድ ሰው ገቢ ለማግኘት በቋሚነት ከሚሰራው ሥራ የተለየ ነው። በአጠቃላይ፤በጎ ፈቃደኝነት ከአንድ ማህበረሰብ የተውጣጡ ግለሰቦች ወይም ቡድን በማህበራዊ በጎ አድራጎት እና በአካባቢያዊ ተግባራት የሚያደርጉት የበጎ ፈቃድ ተሳትፎ ነው።

በጎ ፈቃደኛ ማለት ደግሞ ለሌሎች ጥቅም ሲል አስተዋፅኦ የሚያደርግ እና በምላሹ ምንም የማይጠብቅ ሰው ነው። በጎ ፈቃደኞች የተለያዩ የክህሎት፣የእውቀት እና የልምድ ስብስቦችን በመጠቀም ለማህበረሰባቸው ልዩ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።

የበጎ ፈቃደኝነት መነሻ እና ግብ ለበለጠ ጥቅም የግል አስተዋፅኦ በማድረግ የህብረተሰቡን ችግር መፍታት ነው። በአጠቃላይ በጎ ፈቃደኝነት የሰው ልጅ ሌሎችን ለማገልገል እና ለማህበራዊ ጉዳዮች መሟገት ካለው ፍላጎት ጋር የተቆራኘ ነው። ስለዚህ፤ድጋፍ ለሚፈልጉ ግለሰቦችን እና ማህበረሰቦችን ለመርዳት ወሳኝ ስልት ነው። አረጋውያንን መርዳትና የአከባቢ እንክብካቤ ማድረግን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል።



ምስል 6.3 ተማሪዎች ችግኝ ሲተክሉ

የተቸገሩ ሰዎችን በበጎ ፈቃደኝነት ማገልገል ፈርጀ ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡ ከዚህ በመቀጠል የበጎ ፈቃደኝነት ዋና ዋናጥቅሞችን በጥልቀት እንመለከታለን፡፡

ሀ. ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ እድል ይፈጥራል

ከዚህ በፊት የማታውቀውን ሰው በመተዋወቅ የምታገኛቸው ጥቅሞች ምንድናቸው?

በጎ ፈቃደኝነት በሁሉም እድሜ፣ ብሄረሰቦች እና ማህበራዊ ቡድኖች ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር ለመገናኘት የሚያስችል አንዱ እና አስፈላጊ መንገድ ነው፡፡ የበጎ ፈቃደኝነት ስራ ለማንም ክፍት ስለሆነ ከተለያዩ የህይወት ዘርፎች የተውጣጡ ሰዎችን እንድታገኝ ያስችላል፣ ይህም የአስተሳሰብ አድማስህን ሊያሰፋ ይችላል፡፡ ከአዳዲስ ሰዎች ጋር በበጎ ፈቃደኝነት ስራ መሳተፍ እና ግንኙነቶችን ማጠናከር አዳዲስ ጓደኞችን ለመተዋወቅ እና ከነባሮቹም ጋር ለመቀጠል በጣም ጥሩ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህ፣በጎ ፈቃደኝነት የአንተን ፍላጎቶች እና ሀሳብ ከሚጋሩ እና የዕድሜ ልክ ጓደኞች ሊሆኑ ከሚችሉ ሌሎች ሰዎች ጋር ያስተዋውቅሀል፡፡



ምስል 6.4 ተማሪዎች በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ ሲሳተፉ

ለ. በራስ መተማመንን ይገነባል

በተለያዩ የበጎ ፈቃደኝነት ተግባራት ላይ መሳተፍ በምን መልኩ በራስ መተማመንን ያሳድጋል?

በበጎ ፈቃደኝነት መሳተፍ የስኬታማነት ስሜትን ይሰጥሃል እንዲሁም ለራስህ ያለህን ግምት በማጎልበት በራስ የመተማመን ስሜትህን ይገነባል። በጎ ፈቃደኝነት ስለራስህ ጥሩ ስሜት እንዲሰማህ ያደርግሃል፣ይህም በህይወትህ እና የወደፊት ግቦችህ ላይ የበለጠ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖርህ ይረዳሀል። በተለይም ዓይናፋር ለሆኑ ሰዎች በራስ የመተማመን ስሜትን ለማሳደግ በጎ ፈቃደኝነት ጠቃሚ እና ተመራጭ መንገድ ነው።

ሐ. አላማ እንዲኖርህ ያደርግሀል

በጎ ፈቃደኝነት አስፈላጊ የሆነውን ማህበራዊ ጉዳይ ለመፍታት እንዲሁም የአላማ ስሜት እንዲሰማህ እድል ይሰጥሀል። በጎ ፈቃደኝነት እድሜህ ወይም የህይወት ተሞክሮህ ምንም ይሁን ምን ለህይወትህ አዲስ ትርጉም እና አቅጣጫ ለመስጠት ተመራጭ መንገድ ሊሆን ይችላል። በጎ ፈቃደኝነት ወጣቶች ከማህበረሰባቸው ጋር የበለጠ ግንኙነት እንዲኖራቸው፣የትምህርት ብቃታቸውን እንዲያሻሽሉ እና በአደገኛ ሱስ እና ባህሪ ውስጥ እንዳይሳተፉ ይረዳቸዋል።

መ. ለወደፊት ስራህ ጠቃሚ ነው

በጎ ፈቃደኝነት እንደ ተግባቦት፣ ትብብር፣ ችግር መፍታት፣ እቅድ ማውጣት እና አደረጃጀት ያሉ አስፈላጊ የስራ ቦታ ክህሎቶችን እንድታዳብር ያስችልሃል። ከጊዜ ወደ ጊዜ ተወዳዳሪ በሆነ የሥራ ገበያ ውስጥ በጎ ፈቃደኝነት ተወዳዳሪ እንድትሆን ያስችልሃል። ለወደፊት ቀጣሪዎችህ በራስ ተነሳስተህ እና አለምን ለሌሎች የተሻለች ቦታ ለማድረግ ጊዜህን በፈቃደኝነት ለመስጠት ፈቃደኛ መሆንህን እንዲረዱ ያደርጋል።

የቤት ሥራ



ወላጆችህ በበጎ ፈቃደኝነት ተግባር ተሳትፈው ያውቃሉ? ከተሳተፉ ስለ ተሞክሯቸው በመጠየቅ ለክፍል ተማሪዎች አጋራ/ሪ።

ከታች ያለውን አጭር ታሪክ ካነበብክ በኋላ ከጎንህ ካለው ተማሪ ጋር ተወያይበት እና ለሚቀጥሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

የብዙሃን እናት

ወ/ሮ አበበች ጎባና በ1938 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ተወለዱ፡ ፡ ይሁን እንጂ ከግዜ በኋላ የትውልድ ቦታቸውን በመተው ወደ አዲስ አበባ ሄዱ። እኚህ ትጉ እናት በ1972 ዓ.ም. ወደ ወሎ ጠቅላይ ግዛት ሄደው ሲመለሱ እግረ መንገዳቸውን በድርቅ ሳቢያ በጣም የተጎዱና ሞት አፋፍ ላይ ያሉ ሁለት ልጆችን አይተው ወደ ቤታቸው ወሰዷቸው። በዚሁ አመት ውስጥ 21 ተጨማሪ ህጻናትን ወደ ቤታቸው በመውሰድ ማሳደግ ጀመሩ።

ወ/ሮ አበበች ጎበና የተቸገሩ ልጆችን ለማሳደግ ጉልበት፤ ሃብት፤ ግዜ፤ ገንዘብ እና ህይወታቸውን መስዋእት በማድረጋቸው ‹የብዙሃን እናት› የሚለውን ስም አግኝተዋል።

በኋላ ላይ እኝህ እናት በሺዎች የሚቆጠሩ ችግረኛ ልጆችን የሚረዳውን የሕፃናት እንክብካቤ እና ልማት ማህበር አቋቋሙ። እኚህ እናት ከተለያዩ ግለሰቦች እና ተቋማት ያገኟቸውን ጌጣጌጦችን እና ስጦታዎችን ለራሳቸው ሳይጠቀሙ ልጆቻቸውን ለማሳደግ ያውሉት ነበር።

በዚህ የበጎ አድራጎት ስራቸው የጅማ ዩንቨርስቲ በ2010 ዓ.ም የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷቸዋል። በመልካም ስራቸው እውቅና እና ክብር የተሰጣቸው እኚህ እናት ሰኔ 27 ቀን 2021 እ.ኤ.አ. ከዚህ አለም በሞት ተለይተዋል።



ምስል 6.5 ክቡር ዶክቱር አበበች ጎበና ከልጆቻቸው ጋር



የፕሮጀክት ስራ

1. ከዚህ አጭር ታሪክ ምን ትማራለህ/ሪያለሽ?
2. በአካባቢያችሁ ተመሳሳይ ታሪኮችን በመጠየቅ አቅርቡ።

6.4 የማህበረሰብ ተሳትፎ አይነቶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃት፤

- የማህበረሰብ ተሳትፎን ሶስት ገፅታዎች ትለያለህ/ሽ፤
- የማህበረሰብ ተሳትፎን ፖለቲካዊ ገፅታዎች ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ፤
- የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎን በማነፃፀር ታብራራለህ/ሪያለሽ፣

የማህበረሰብ ተሳትፎ በአጋጣሚ የሚሰራ ሳይሆን በእቅድና ስትራቴጂ/ስልት የሚመራ ተግባር ነው። ይህ ክፍል የማህበረሰቡን ተሳትፎ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ማብራራት ላይ ያተኩራል።

6.4.1 ማህበራዊ ተሳተፎ



ማህበራዊ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት ነው?

የማህበረሰብ ተሳትፎ ማህበራዊ ገፅታ ዜጎች በግል እና በጋራ—የማህበረሰቡን ማህበራዊ ፍላጎቶች እንዲሟላ የሚያደርጉት ተሳትፎ ነው። በሁሉም እድሜ ላሉ ሰዎች በተለይም ለአረጋውያን ማህበራዊ ተሳትፎ ማዳበር እና ማቆየት ወሳኝ ነው። ዋና ግቡ የህዝብ አገልግሎት ጥራትን ማሻሻል እና ከማህበረሰቦች ጋር ይበልጥ ተዛማጅነት እንዲኖረው ማድረግ ነው።

ይህም ለማህበረሰቡ አስፈላጊ የሆኑ እንደ ሰላም፡ ትምህርት፤ ጤና፤ መብራት፤ መንገድ እና የመሳሰሉት ተግባራት ውስጥ መሳተፍን ያካትታል፡ ፡ እዚህን የመሳሰሉትን ተግራት ለማሳካት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ማለትም ግለሰቦች፤ቡድኖች፤ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ተሳትፎን ያካትታል።



ምስል 6. 6 የማህበረሰብ ተሳትፎ

6.4.2 ፖለቲካዊ ተሳትፎ


የፖለቲካ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት ነው?

የፖለቲካ ተሳትፎ ማለት ዘጎች በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጉትን ተሳትፎ የሚመለከት ነው። የፖለቲካ ተሳትፎ የአንድ ማህበረሰብ አባላት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚሳተፉበት ሆኖ መሪዎቻቸውን በመምረጥ እና በሕዝብ ፖሊሲ ቀረጻ ላይ የሚሳተፉበት ተግባር ተደርጎ ይወሰዳል። ድምጽ መስጠት፣ መረጃ መፈለግ፣ ስብሰባ ማካሄድ፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ መዋጮ ማድረግ፣ የስራ ማቆም አድማ እና ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ እና ከህግ አውጭዎች እና ሌሎች ተፅዕኖ ፈጣሪ አካላት ጋር መነጋገር የፖለቲካ ተሳትፎ ምሳሌዎች ናቸው።

ንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ ማለት በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ አባል መሆን ሲሆን ይህም የምርጫ ቅስቀሳ፤ የመራጮች ምዝገባ እና ንግግሮችን ማድረግ ያካትታል፡ ፡ በተጨማሪም ለህዝብ እና ለፓርቲ እንደራሴነት መወዳደርን ያጠቃልላል።

ስለሆነም የሀገራችንን ዴሞክራሲ ጤናማ ለማድረግ ሁላችንም ስለ ወቅታዊ ሁኔታዎች እና የፖለቲካ ውሳኔዎች የረጅም ጊዜ ውጤቶችን ማወቅ አለብን። በፖለቲካው መድረክ በምናየው ነገር ካልረካን መናገር አለብን። በዚህ ረገድ በሁሉም የፖለቲካ ሂደቶች ውስጥ ወንዶች እና ሴቶች ሙሉ በሙሉ የመሳተፍ

እኩል መብት አላቸው። በመሆኑም ስለ ፖለቲካ ሂደት በመረዳት እና በመሳተፍ ህብረተሰባችን እና ሀገራቱን በአጠቃላይ መጥቀም ያስፈልጋል።



ምስል 6.7 የዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ

6.4.3 ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ

ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ማለት ምን ማለት ነው?

የማህበረሰብ ተሳትፎ እንደ ጽንሰ-ሀሳብ፣ በሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር እና ነባራዊ ሁኔታን የመቀየር ችሎታ ስላለው ለእድገት ማዕከላዊ ነው። የማህበረሰብ ተሳትፎ ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ደግሞ የተለያዩ የማህበረሰቡ አባላትን በተከታታይ የማህበረሰብ ልማት ሂደት ውስጥ ማካተትን ያመለክታል። እንዲሁም የፕሮጀክት ጥቅማ ጥቅሞች ተቀባይ ከመሆን ይልቅ በልማት አቅጣጫ እና አፈፃፀም ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩበት ተነሳሽነት እና ሂደት ተደርጎ ይወሰዳል። ስለሆነም የተለያዩ ተቋማት መንግስትን ጨምሮ፣አንዱና ዋነኛው ኃላፊነት ህብረተሰቡን በምጣኔ ሃብት ሂደት ውስጥ ማሳተፍ ነው።



ምስል 6.8 በአካባቢ በልማት የማህበረሰብ ተሳትፎ

የተደራጀ የማህበረሰብ የምጣኔ ሃብት ተሳትፎ የሚከተሉትን ጥቅሞች ሊያስገኝ ይችላል፤

- የፕሮጀክት ወጪን መቀነስ፣
- የአገልግሎት ሽፋንን ማስፋፋት፣
- ቴክኒካል እና አስተዳደራዊ ተለዋዋጭነትን ማበረታታት፣
- አሰራር እና ጥገናን ማሻሻል፣
- የፕሮጀክት ተቀባይነትን ይጨምራል፣
- የበለጠ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እና ስርጭት እንዲኖር ያደርጋል፣
- የአካባቢ ሃብት ማሰባሰብን ያበረታታል፣
- የፕሮጀክት ዘላቂነትን ያረጋግጣል።

ማጠቃለያ

“የማህበረሰብ ተሳትፎ” የሚለው ቃል “ማህበረሰብ” እና “ተሳትፎ” የሚሉትን ቃላት የሚያጣምር ሆኖ፤ለጋራ ጉዳዮች አጽንኦት ያደርጋል። የማህበረሰብ ተሳትፎ፤ በማህበረሰብ አቀፍ ጉዳይ የሚነካ ማንኛውም ሰው በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ አስተያየት መስጠት አለበት የሚለውን የዴሞክራሲ መርህ መሰረት ያደረገ ነው። ዜጎች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ንቁ ተሳትፎ ሲያደርጉ “ተሳተፉ” ይባላል። ማለትም ሃሳባቸውን በመግለጽ፣መፍትሄዎችን በመለየት እና የድርጊት እና የሀብት ቅደም ተከተል በማስቀመጥ ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ። የማህበረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ሰዎች የአካባቢ ዕውቀትን እንዲጠቀሙ፣ መተማመንን እንዲገነቡ፣ የተገለሉ ቡድኖችን ለማበረታታት እና የአካባቢ ችግሮችን ለመፍታት ያስችላል።

በጎ ፈቃደኝነት በበኩሉ የማህበረሰብ ተሳትፎ አንዱ ገጽታ ነው። በጎ ፈቃደኝነት አንድ ሰው ጊዜ፣ ጥረት እና ችሎታውን ለሆነ ዓላማ ያለ ክፍያ ማዋል ማለት ነው። በጎ ፈቃደኝነት አንድ ሰው ለበለጠ ጥቅም የግል አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ያስችለዋል። የተቸገሩ ግለሰቦችን እና ማህበረሰቦችን ለመርዳት ወሳኝ ስልት ነው። በጎ ፈቃደኝነት ለበጎ ፈቃደኞችም ሆነ ለማህበረሰቡ፣ ለግለሰብ ወይም አስተዋፅኦ ለሚያበረክቱት ድርጅቶች ብዙ ጥቅሞች አሉት።

የማህበሰብ ተሳትፎ የተለያዩ ገፅታዎች አሉት። እነዚህም ማህበራዊ ገፅታ፤ፖለቲካዊ ገፅታ እና ምጣኔ ሃብታዊ ገፅታ በመባል ይከፈላል።

ቁልፍ ቃላት

የህብረተሰብ ተሳትፎ- ዜጎች በሀገራቸው ጉዳይ ላይ የሚያደርጉት ተሳትፎ ነው፡
:

በጎ ፈቃደኝነት- ዜጎች በፍላጎታቸው ጊዜ፤ ሀብት እና ጉልበታቸውን ያለ ክፊያ ለሌሎች መስጠት ማለት ነው።

ሀገር በቀል እውቀት- ከጥንት ጀምሮ ከህዝቡ ጋር የነበረ ነባር እውቀት እና ልምድ ነው።

በራስ መተማመን- አንድ ሰው ለራሱ ያለው ትክክለኛ አቅም እና ቁርጠኝነት።

ዜጎችን ማብቃት፡ በሰዎች እና በማህበረሰቦች ውስጥ ራስን በራስ የማስተዳደር እና የመወሰን ደረጃ ነው።

ክለሳ ጥያቄ

ክፍል I፡ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ካልሆኑ ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ።

1. የማህበረሰብ ተሳትፎ የአንድ አቅጣጫ ሂደት ነው።
2. ተግባቦት እና ግንኙነት ለማህበረሰቡ እድገት አስፈላጊ ናቸው።
3. የማህበረሰብ ተሳትፎ ስኬታማ እንዲሆን የተወሰኑ ሰዎች ብቻ መሳተፍ አለባቸው።

ክፍል II፡ ለምከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ ምርጫን ምረጥ/ጭ።

1. ከሚከተሉት ውስጥ የበጎ ፍቃደኝነት ጥቅም ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመተዋወቅ እድል አይፈጥርም

   ለ. በራስ መተማመንን ይገነባል

   ሐ. አላማ እንድኖርህ ያደርግሀል

   መ. ለወደፊት ስራህ ጠቃሚ ነው

2. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የማህበረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊነት አይደለም።

   ሀ) ህዝቡ የሂደቱ ዋና አካል እንደሆነ ሊሰማው ይችላል

   ለ) ሰዎች በስልጣን ላይ ያለውን የባለስልጣኑን ውሳኔ በዝምታ መቀበል

   ሐ) ማንኛውንም ነገር ለመፍታት ህዝቡ አስተዋፅዖ ያደርጋል

   መ) አንድ ማህበረሰብ አላማውን በማሳካት ረገድ ስኬታማ የመሆን እድሉ ከፍተኛ ነው

3. በጎ ፈቃደኝነትን አስመልክቶ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው እውነት ነው?

ሀ) በክፊያ ግዴታን መወጣት

ለ) የታዘዘ ወይም የውል ስምምነት ነው

ሐ) ከክፊያ ነፃ የሆነ ድርጊት ነው

መ) ከላይ ያሉት ሁሉም

ክፍል III: አጭር መልስ፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ጻፍ/ፊ።

1) ለበጎ ፈቃደኞችም ሆነ በጎ ፈቃድ ለተደረገለት ሰው የበጎ ፈቃደኝነት ጥቅሞች ምንድን ናቸው?
2) ሶስቱን የማህበረሰብ ተሳትፎ ገፅታዎች በማነጻጸር ግለፅ/ጪ

ምዕራፍ 7 በጥልቀት ማሰብ

መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የመጨረሻ እና ሰባተኛው የትምህርት ክፍል ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ በጥልቀት ማሰብ ፅንሰ- ሀሳብ፤ በጥልቀት ማሰብ አስፈላጊነት እና መሰረታዊ በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶችን ትማራለህ/ሪያለሽ።

የምዕራፉ የመማር ውጤቶች

- ስለ በጥልቀት ማሰብ ፅንሰ- ሀሳብ ማብራራት፤
- በጥልቀት ማሰብ አስፈላጊነትን መግለፅ፤
- መሰረታዊ በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶች መጎናፀፍ።

7.1 በጥልቀት ማሰብ ፅንሰ- ሀሳብ

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች

- በጥልቀት ማሰብ ምንነት ትገልፃለህ/ጫለሽ፤
- የትንተና ዓላማ ታብራራለህ/ሪያለሽ፤
- የመረጃ ምንጮች ትለያለህ/ሽ።



በጥልቀት ማሰብ ማለት ምን ማለት ነው?

በጥልቀት ማሰብ መረጃን በትክክል የመተንተን እና ምክንያታዊ ውሳኔ የማድረግ

ችሎታ ማሳያ ነው። ይህ ማለት ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን ፍትሀዊ በመሆን መተንተን ማለት ነው። በዘመናችን ብዙ የመረጃ ምንጮች አሉ።

ለምሳሌ ጓደኞች፣ አስተማሪዎች፣ ጎረቤቶች፣ ቴሌቪዥን፣ ራዲዮ፣ ጋዜጦች፣ መጽሃፎች፣ ፊልሞች፣ እንደ ፌስቡክ ያሉ የማህበራዊ ሚዲያ ገፆች እና የመሳሰሉት ሁሉ የመረጃ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ። ጠቃሚ የሆኑ የመረጃ ምንጮች እንዳሉ ሁሉ የውሸት እና ጎጂ የሆኑ የመረጃ ምንጮች አሉ። ስለዚህ ተጨባጭ እና ጥሩ ውሳኔ ለማድረግ፣ መረጃዎችን ከተለያየ ማዕዘን መመርመር ወይም ከበርካታ ምንጮች መፈተሽ አለበት። ስለሆነም ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን በአግባቡ መተንተን ያሰፈልጋል።

የጉዳይ ጥናት

ለምሳሌ፣ በአንድ ወቅት፣ የዜግነት ትምህርት መምህሩ ቅኝ አገዛዝ ሰብአዊ መብቶችን ያበረታታል ወይም ይጥሳል የሚል ጥያቄ ለክፍሉ ጠየቀ። በቡድን ስም "ነብር" ተብለው የሚጠሩ ተማሪዎች ቅኝ አገዛዝን በመቃወም ሰብዓዊ መብቶችን ይጥሳል ብለው ተከራከሩ። በሌላ በኩል "አንበሳ" የሚል የቡድን ስም ያላቸው ተማሪዎች ቅኝ አገዛዝ መብቶችን እንደሚያሳለብት፤ እኩልነትን እና ነፃነትን እንደሚያረጋግጥ በማመን ቅኝ አገዛዝን በመደገፍ ይከራከራሉ።"የነብር ቡድን" አባላት በታሪክ ቅኝ ገዢዎች ዜጎችን ይጨቁኑ ነበር፣ እና በጭቆና ወቅት ሰብዓዊ መብቶችን ማስከበር እንደማይቻል ይከራከራሉ። "የአንበሳ ቡድን" አባላት ቅኝ ገዢዎች በቅኝ ግዛት ስር በነበሩ ሀገራት ውስጥ ብዙ መንገዶችን እና ድልድዮችን ሰርተዋል ይላሉ። እንደ "የአንበሳ ቡድን" ሀሳብ ድሀ አገሮች በቅኝ አገዛዝ መገዛት አለባቸው የሚል ፅኑ አቋም አላቸው። "የነብር ቡድን" ድሀ አገሮች በፍጹም ቅኝ መገዛት እንደሌለባቸው ያምናሉ ምክንያቱም አሉታዊ ተፅዕኖ ከአዎንታዊ ተጽእኖ ይበልጣል። "የነብር ቡድን" ቅኝ ገዢዎች መንገዶችን እና ድልድዮችን የሚገነቡት በቅኝ ግዛት ስር ያሉትን ሀገራት የተፈጥሮ ሃብት ለመበዝበዝ ብቻ እንደሆነ ይከራከራሉ።

የቡድን ስራ

ከላይ በተጠቀሰው የጉዳይ ጥናት አሳማኝ ሀሳብ የትኛው ቡድን ነው ያቀረበው? አንተ/ቺ የየትኛው ቡድን ደጋፊ ነህ/ሽ? ለምን?

ከዚህ የጉዳይ ጥናት ዋና አላማ ተማሪዎች ምክኒያታዊ በሆነ መልኩ በመረጃ የተደገፈ ሀሳብ የማቅረብ ችሎታ እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው። በጥልቀት ማሰብ

ክህሎት ያላቸው ሰዎች የመረጃን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ችግር ፈቺ ውሳኔዎችን ማስተላለፍ የሚችሉ ናቸው። አንድ ሰው በጥልቀት ማሰብ ክህሎት አለው የሚባለው ትክክለኛና የተሳሳቱ መረጃዎችን በትክክል በመገምገም መለየት ሲችል ብቻ ነው። ይህ ማለት በጥልቀት ማሰብ መረጃ መሰብሰብ ብቻ ማለት ሳይሆን መረጃን በአግባቡ መተንተን፤ መጠቀም እና ውጤቱን የመተንበይ ክህሎትን ያካትታል።

የጉዳይ ጥናት

ሂንሰርሙ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ነው።ሂንሰርሙ ፌስቡክ በተለያዩ የአለም ክፍሎች ከሚኖሩ ወዳጅ ዘመዶቻቸው ጋር ለመገናኘት ጠቃሚ መድረክ እንደሆነ ፅኑ እምነት አለው። እንዲሁም አዳዲስ ጓደኞችን ከማፍራት በተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በፌስቡክ ላይ ብቻ መጠቀም በቂ እንደሆነ ይተማመናል። እንደ ሂንሰርሙ አስተሳሰብ በፌስቡክ የሚተላለፉ መረጃዎች ሁሉ ጠቃሚ እና ትክክለኛ እንደሆኑ አድርጎ ይቆጥራል።

የቡድን ስራ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት ሀሳባችሁን ለክፍል ተማሪዎች ግለፁ

1. **እንደ ፌስቡክ ካሉ ማህበራዊ ሚዲያዎች የሚገኙ ሁሉም መረጃዎች ትክክል እና ጠቃሚ ናቸው?**
2. **እንደ ፌስቡክ ባሉ የማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ያሉ ሁሉም መረጃዎች እና ዜናዎች ሁል ጊዜ ሀሰት ናቸው ብላችሁ ታምናላችሁ?**

እንደ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሂንሰርሙ የመረጃን እውነተኛነት ለማረጋገጥ የተለያዩ ምንጮች ማገናዘብ እና ማመሳከር አስፈላጊ ነው። ፌስቡክ አንዱ የመረጃ ምንጭ ስለሆነ ብቻ የውሸት ዜና የለም ማለት እንዳልሆነ ማስታወስ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ሰዎች የሀሰት ዜና እና መረጃ ሊያሰራጩ ይችላሉ። ስለዚህ እንደ ፌስቡክ አይነት የመረጃ ምንጮችን በአግባቡ አለመተንተን እና ትክክለኛነቱን ከሌላ ምንጭ አለማረጋገጥ ሰውን ለከፋ ችግር ይዳርጋል።

በድርጊት ጥናቱ ላይ እንደተመለከተው ሂንሰርሙ በጥልቀት አሳቢ አይደለም። ምክንያቱም በፌስቡክ ላይ ያለውን መረጃ ሳይመረምር ስለሚወስድ ነው።

የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ከላይ ካለው የድርጊት ጥናት ምን ተረዳህ/ሽ?
2. በጥልቀት ማሰብ ማጣት ምን አይነት ጉዳት ያመጣል?

7.2 በጥልቀት የማሰብ አስፈላጊነት

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች

- በጥልቀት ማሰብ አስፈላጊነትን ትተነትናለህ/ኛለሽ፤
- በጥልቀት ማሰብ ማነስ የሚያስከትለውን ጉዳት ታብራራለህ/ሪያለሽ፤
- ትክክለኛ እና የተሳሳቱ መረጃዎችን ትለያለህ/ሽ።

በጥልቀት ማሰብ አስፈላጊነት ሲባል ምን ማለት ነው?



ቻርት: 7.1 በጥልቀት የማሰብ አስፈላጊነት

በጥልቀት ማሰብ በተለያዩ ምክንያቶች አስፈላጊ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም። በአጠቃላይ በጥልቀት ማሰብ ብዙ ጥቅሞች አሉት።

በዚህ የትምህርት ክፍል ውስጥ በጥልቀት የማሰብ ዋና ዋና ጥቅሞችን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1. እውነተኛ መረጃ ለማግኘት

እውነተኛ መረጃ ማግኘት በጥልቀት ማሰብ አስፈላጊነት ውስጥ አንዱ ነው። ይህም የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመፈተሽ የመረጃን እውነተኛነት ማረጋገጥን ያካትታል። ለምሳሌ አንድ ሰው በውሸት መረጃ ላይ ተመርኩዞ ውሳኔዎችን ቢያደርግ ውሳኔዎቹ መጥፎ እና በህይወቱ ላይ አሉታዊ ውጤቶችን ያመጣሉ፡ ፡ በመሆኑም የመረጃን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በጥልቀት ማሰብ በጣም አስፈላጊ ነው።

የጉዳይ ጥናት

በፈተና ወቅት መኮረጅ ትክክል ነው የሚል መረጃ ከጓደኛህ አገኘህ እንበል። በሌላ መልኩ ደግሞ በፈተና ወቅት መኮረጅ ትክክል አይደለም የሚል መረጃ ከዜግነት አስተማሪህ አግኝተሃል። በመሆኑም በፈተና ወቅት መኮረጅ ትክክል ነው ወይስ ፀያፍ ነው ለሚለው መረጃ ከሁለት ምንጮች አግኝተሃል። በመሆኑም ውሳኔ ከመወሰንህ በፊት የትኛው መረጃ ትክክለኛ እንደሆነ መለየት አለብህ። ይህን ለማድረግ ሌላ ተጨማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ ካሉ ሁለት መምህር እና ሁለት ተማሪ በመጠየቅ መረጃህን አጠናቅር። በመጨረሻም ያሰባሰብካቸውን መረጃዎች በማገናዘብ ትክክለኛ ውሳኔ ስጥ።



የቡድን ስራ

ከላይ በቀረበው የጉዳይ ጥናት መሰረት ከቡድን ጓደኞችህ ጋር በመወያየት ውጤቱን ለክፍል ተማሪዎች ግለፅ

1. ከሁለቱ የመረጃ ምንጮችህ የትኛው ትክክለኛ ነው?
2. በፈተና ወቅት መኮረጅ ወንጀል ነው ወይስ ወንጀል አይደለም? ለምን?

በጥልቀት የማሰብ ክህሎት የሌላቸው ተማሪዎች በተሳሳተ መረጃ ውሳኔ ሲወስኑ ይታያል። ከላይ በተጠቀሰው የጉዳይ ጥናት እንደተመለከተው ጓደኛህ በፈተና ወቅት መኮረጅ ወንጀል እንዳልሆነ ቢመክርህም ሌብነት ወንጀል እንደሆነ እና ከባድ ጥፋት እንደሚያስከትል ከተለያየ ምንጭ ማረጋገጫ መውሰድ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ትክክለኛ ውሳኔ ለመወሰን እውነተኛ መረጃ ማግኘት ጠቃሚ ነው።

2. መሰረታዊ ጥያቄዎችን እና ችግሮችን እንድናነሳ ይረዳናል።

በጥልቀት ማሰብ በህብረተሰቡ ውስጥ የተንሰራፋውን የተለያዩ ችግሮችን ለማስተካከል ይረዳናል።ለተለዋጭ ሀሳቦች እና አስተያየቶች ክፍት መሆን የምንችልበትን መንገድ ያስተምረናል፣ እንዲሁም የራሳችንን ግምቶች፣ እንድምታዎች እና ተግባራዊ መዘዞች እንዴት እንደምንገመግም እና ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታት እንዴት እንደምንችል ያስተምረናል። ለምሳሌ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚስተዋሉ ችግሮች ውስጥ የጤና አገልግሎት እጦት፤የውሃ ችግር፤ የመንገድና ትራንስፖርት ችግር፤የፆታ እኩልነት ችግር፤ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። በመሆኑም አንተም እንደ ተማሪ በጥልቀት ማሰብ ክህሎትን በማጎልበት በማህበሩ ውስጥ የሚገኙ ችግሮችን በመለየት እና የተለያዩ የመፍትሄ ሀሳቦችን በማቅረብ አስተዋፅኦ ማድረግ አለብህ።

3. ለዴሞክራሲ ግንባታ ወሳኝ ሚና ይጫወታል

ዜጎች በተቻለ መጠን ከአድሎ ነፃ በሆነ መልኩ በመረጃ ላይ የተመሰረተ እና ምክንያታዊ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ማድረግ ለዴሞክራሲ ግንባታ አስፈላጊ ነው። የዴሞክራሲ ዋና መገለጫ ህዝቡ የስልጣን ምንጭ መሆኑ ነው። በመሆኑም በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለሚመርጣቸው በየደረጃው ያሉ ባለስልጣናትን እቅድና የአፈፃፀም ስልት በመገምገም መሆን አለበት። ይህም ለዴሞክራሲ ግንባታ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በተጨማሪም ዛሬ ካሉት በጣም አሳሳቢ የማህበረሰብ ችግሮች፣ እንደ ድህነት፣ የአካባቢ ውድመት፣ ግጭቶች፣ የህብረተሰቡ የሞራል ዝቅጠት፣ ከፍተኛ ሙስና፣ እና የመሳሰሉትን ችግሮች ለመጥቀስ ማህበረሰቡን በጥልቀት የማሰብ ክህሎት ማዳበር ወሳኝ ነው።

7.3 በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶች

ከተማሪ የሚጠበቅ ዝቅተኛው የመማር ብቃቶች


- በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶችን ትገልፃለህ/ጫለሽ፤
- የትንተናን ምንነት ታብራራለህ/ሪያለሽ፤
- የቡድን ስራን ጥቅም ትዘረዝራለህ/ሪያለሽ



የቡድን ስራ

1. በጥልቀት ማሰብ ምን አይነት ክህሎቶች ያስፈልጉታል?

2. እንደ አንድ ተማሪ በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶች ይኖርሃል/ሻል?



ቻርት: 7.2 በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶች

በጥልቀት ማሰብ አራት ዋና ዋና ክህሎቶችን ያካትታል። እነሱም ትንተና፤በቡድን መስራት፤ፈጠራ እና ችግር መፍታት ናቸው።

1. ትንተና

ትንተና የመጀመሪያ እና በጣም አስፈላጊ በጥልቀት የማሰብ ክህሎት ነው። አንድን ነገር በተጨባጭ መረጃ ላይ በመመርኮዝ የመመርመር እና መገምገም ትንተና ይባላል። ቀደም ሲል እንደተገለጸው አሁን ከተለያዩ ምንጮች መረጃ ማግኘት ችለናል። ለምሳሌ ከጓደኞችህ አንዱ ሀይማኖት፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ ፆታ እና የቆዳ ቀለም ምንም ይሁን ምን ሁሉንም ሰው እንድታከብር ሊመክርህ ይችላል። በሌላ በኩል ሌላው ጓደኛህ ደግሞ የቤተሰብህን አባላት ብቻ እንድታከብር ሊመክርህ ይችላል። ከላይ ካሉት ምሳሌዎች ማየት እንደምትችለው ሁለት ምርጫዎች አሉህ፤ ሁሉንም ሰው ማክበር ወይም ቤተሰብህን ብቻ ማክበር። አሁን እነዚህ ሁለቱ ምክሮች እኩል አስፈላጊ ናቸው? ወይስ አይደሉም? የሚለውን መተንተን አለብህ። እያንዳንዱ ሰው መከበር አለበት የሚለው የመጀመሪያው ምክር ጥሩ ነው፤የቤተሰብህን አባላት ብቻ ማክበር እንዳለብህ የሚገልፀው ሁለተኛው ምክር ሌሎች ሰዎችን ስለሚያገለል ጥሩ ሀሳብ አይደለም። ምክንያቱም ቤተሰብን ማክበር ጥሩ ቢሆንም ቤተሰብን ብቻ ማለቱ ግን ስህተት ነው፤ ይህም ሌላ ሰውን ማክበር እንደማያስፈልግ ስለሚያሳይ ስህተት ነው። እንዲህ አይነት የተለያዩ አማራጮች ሲቀርቡልህ የቀረቡትን ሁለት አማራጮች ከተለያዩ አቅጣጫዎች በጥልቀት መተንተን ለአንተም ሆነ ለሀገርህ ጠቃሚ ይሆናል።




ስዕል: 7.3 ማሰብና መወሰን

የጉዳይ ጥናት

በክፍልህ ውስጥ እርስ በርስ የሚጣሉ ሁለት ተማሪዎች አሉ። እነዚህ ተማሪዎች እየተጣሉ ሳለ አንዳንድ ተማሪዎች ጣልቃ ሳይገቡ ዝምብለው ይመለከቷቸዋል። እነዚህ ተማሪዎች ግጭቱ በኃይል መፈታት እንዳለበት የሚያምኑ ናቸው። ሌሎች ተማሪዎች ግን እነዚህ እርስ በርስ የሚጋጩ ተማሪዎች ጥላቸውን አቁመው በሰላማዊ መንገድ ጉዳያቸውን በውይይት እንዲፈቱ ይፈልጋሉ። እነዚህ ተማሪዎች ግጭቱ በሰላማዊ መንገድ በውይይት ሊፈታ እንደሚገባ ያምናሉ።ነገር ግን ሁለቱ ተቃራኒ ተማሪዎች አለመግባባታቸውን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አይፈልጉም። ይልቁንም አለመግባባታቸውን በኃይል መፍታት ይፈልጋሉ።

የቡድን ስራ

የተማሪዎቹ ግጭት እንዴት መፍታት አለበት? ለምን? በቡድን በመሆን ስለ ጉዳዩ በመወያየት አብራሩ።

በተለያዩ ምክንያቶች በሁለት ተማሪዎች መካከል ግጭት ሊፈጠር ስለሚችል፣ አለመግባባቱ በኃይል ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ መፈታት አለበት። እንደተማሪ ሁለት አማራጮች አሉህ፡ ይህም ወይ ጥላቸውን እንዲያቆሙ መርዳት ወይም ሲጣሉ ዝም ብለህ መመልከት። የትኛው አማራጭ ከሌሎቹ የበለጠ አስፈላጊ እንደሆነ መወሰን አለብህ፤ ዝም ብለህ መመልከትን ከመረጥህ ውሳኔህ የተሳሳተ

ነው። ምክንያቱም በተማሪዎች መካከል የሚደረግ ጠብ ብዙ አሉታዊ ውጤቶች አሉት፣ አካላዊ ጉዳት እና የመማር ማስተማሩ ሂደት መቋረጥን ጨምሮ።

ተማሪዎቹ ጥላቸውን እንዲያቆሙ ለመርዳት ከወሰንክ ያደረከው ውሳኔ ትክክለኛ ነው። ምክንያቱም ግጭቶችን በኃይል ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ መፈታት እንዳለበት ያሳያል። በመሆኑም ጥሩ ትንተና ክህሎት በመባል የሚታወቀው በጥልቀት የማሰብ ክህሎት እንዳለህ ያመለክታል። የትንታኔ ክህሎት ያላቸው ተማሪዎች የአንድን ድርጊት ጥሩ እና መጥፎ ጎኑን በመገምገም ውሳኔ ይወስናሉ፡ ፡ ግጭትን በሃይል ለመፍታት መሞከር ስህተት መሆኑን በመረዳት ለተቀሩት ለክፍል ጓደኞቻቸው ምክንያቱን በትክክል ማስረዳት ይችላሉ። የትንታኔ ክህሎት ያላቸው ተማሪዎች የግጭትን ጉዳት አስቀድመው ስለሚረዱ ተማሪዎችን በማስረዳት በተለያየ ምክንያት የሚነሱ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ይረዳሉ።

2. የቡድን ስራ



የቡድን ስራ ምን አይነት ጥቅም አለው?





ስዕል : 7.4 ተማሪዎች በቡድን ሲያጠኑና የቡድን ስራ ሲሰሩ

ከእያንዳንዱ ተማሪ የሚጠበቀው ሌላው አስፈላጊ በጥልቀት የማሰብ ክህሎት ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመተባበር/በቡድን የመስራት ክህሎት ነው። በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን የቡድን ስራ ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ፣ መምህሩ የቡድን ፕሮጀክት ከመደብክ፣ የቡድን አባል እንደመሆንህ፣ የተለያዩ ችግሮችን ለመፍታት ከሌሎች ጋር መተባበር እና በብቃት መወጣት ያስፈልግሀል። ተማሪዎች አንድን ተግባር ለማጠናቀቅ ሲተባበሩ ለሁሉም ተጠቃሚ ይሆናሉ።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ፣ ለምሳሌ፣ የቡድን አባላት አስቀድመው ያቅዱ እና ስራዎችን ለመመደብ፣ ለውጥን ለመገምገም እና የቡድን ስራውን በሰዓቱ ለማቅረብ መተባበር አለባቸው። የቡድን መሪው ብዙ ጊዜ የቡድን ስራ አስተባባሪ ነው። በዚህ ሁኔታ እያንዳንዱ ተማሪ በቡድን ስራ ውስጥ እንዲሳተፍና ድርሻውን እንዲወጣ ማበረታታት ይጠበቅበታል። በተጨማሪም የቡድን አስተባባሪው ሁሉንም አባላት አሳታፊ የሆነ ውሳኔ በመወሰን የአባላትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይጠበቅበታል።ይህም በአባላት መካከል መተማመንን በማጎልበት ረገድ ወሳኝ ሚና አለው። ምንም እንኳን በቡድን የሀሳብ ልዩነት የሚጠበቅ ቢሆንም ምክንያታዊ በመሆንና የመቻቻል ባህልን በማዳበር ለጋራ ጥቅም ሲባል በቡድን መስራት አስፈላጊ ነው።

በአጠቃላይ በቡድን መስራት የሚከተሉትን ባህሪያት ያጎናፅፋል

- ☞ በትብብር መስራት፣
- ☞ የኃላፊነት ስሜት፣
- ☞ አስተዋጽዖ ማድረግ፣
- ☞ ሀሳብ፣አስተያየት መስጠት እና መቀበል፣
- ☞ ለተለያዩ አስተያየቶች፣ ልማዶች እና የግል ምርጫዎች ጤናማ አክብሮት፣
- ☞ በቡድን ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ የመሳተፍ ችሎታ።



የቤት ስራ

1. የቡድን ሥራ በጣም አስደሳች ገጽታ ምንድነው?
2. የቡድን ሥራ በጣም አስቸጋሪው ገጽታ ምንድን ነው?

የጉዳይ ጥናት


ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ የቡድን ስራ በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን ወሳኝ ነው። የትምህርት ቤታችሁ የእግር ኳስ ቡድን ከሌላ የእግር ኳስ ቡድን ጋር ሲጫወት አይተህ ታውቃለህ? በቡድን ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ተማሪ፣ ልክ እንደ አንድ የእግር ኳስ ቡድን ግብ ለማስቆጠር አብረው እንደሚሰሩ፣ ለቡድኑ የተሰጠውን ተግባር በማጠናቀቅ ረገድ የሚጫወተው የተለየ ሚና አለው። ምንም እንኳን አንድ ተጫዋች በዋነኝነት አጥቂው ጎል ያስቆጠረ ቢመስልም ኳሱን ወደዚያ ተጫዋች ለመድረስ ብዙ ሰዎች ባደረጉት እቅድ፣

ቅንጅት እና ትብብር ተችሏል። በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተማሪዎች እቅድ ከማውጣት ጀምሮ ተግባሮችን ለማጠናቀቅ ሲተባበር፣ እያንዳንዱ ተማሪ የበለጠ ውጤት ያስገኛል።

የግንዛቤ ጥያቄ

ከዚህ የጉዳይ ጥናት ምን ተማርክ?

3. ፈጠራ



ስዕል:7.5 የፈጠራን ክህሎትን ማጎልበት

ፈጠራ እንደ አንተ ካሉ ተማሪዎች ሁሉም የሚጠበቅ ወሳኝ በጥልቀት የማሰብ ክህሎት ነው። ከዚህ በፊት ማንም ያላሰበውን ሃሳብ ወይም መፍትሄ ማምጣት ፈጠራ ይባላል። ለምሳሌ አንድ ሰው ከወዳደቁ ብረታብረት አውሮፕላን፤መኪና፤ድሮን እና የመሳሰሉትን ቢሰራ ፈጠራ ሊባል ይችላል። ስለዚህ እንደ ተማሪ አንድ ተግባር ከተሰጠህ፣ ከሌሎቹ ተማሪዎች የተለየ አዲስ ሀሳብ ማምጣት ይጠበቅብሃል።.

የጉዳይ ጥናት

በክፍልህ ውስጥ 35 ተማሪዎች እንዳሉህ አስብ።ከክፍል ጓደኞችህ አንዱ ዝቅተኛ ገቢ ካለው ቤተሰብ የመጣ በመሆኑ የመርጃ መጽሐፍ ለመግዛት አቅም የለውም። ይህንን የመርጃ መጽሐፍ መኖሩ ለሁላችሁም ወሳኝ መሆኑን አስታውሱ። ብዙዎቻችሁ ይህ የመርጃ መጽሃፍ አላችሁ ምክንያቱም

ቤተሰቦቻችሁ ስለገዙላችሁ ነው። ይህን መፅሃፍ በማንበባችሁ ብዙዎቻችሁ ጥሩ የአፈፃፀም ደረጃ ላይ ናችሁ። ምክንያቱም በጣም እየረዳችሁ ያለው መርጃ መጽሐፍ ስላላችሁ ነው። በሌላ በኩል ከዝቅተኛ ገቢ ካለው ቤተሰብ የመጣው ተማሪ የመርጃ መጽሐፍን ስላላነበበ ዝቅተኛ ውጤት አስመዘገበ፡ ፡ በመሆኑም የክፍል ጓደኞቹ ካለበት ችግር አንፃር፣ ሁላችሁም ለጓደኛችሁ ገንዘብ እንድታዋጡ እና የመርጃ መጽሃፍ እንድትገዙ ሁላችሁም ወስናችሁ ነበር።ከዚያም ከየቤተሰቦቻችሁ አንድ አንድ ብር በመጠየቅ 35 ብር አዋጥታችሁ ለቸገረው ተማሪ መፅሃፉን በመግዛት የተማሪውን ችግር በመፍታታችሁ እሱም እናንተም ተደሰታችሁ።

የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ከዚህ የጉዳይ ጥናት ምን ተረዳህ/ሽ?
2. ተማሪዎች ለችግሩ ያቀረቡት መፍትሄ እንዴት ይታያል?

4. ችግር ፈቺ



ቻርት:7.6 የችግር አፈታት ሂደቶች

ችግር መፍታት ሌላ ወሳኝ በጥልቀት የማሰብ ክህሎት ሲሆን ከእያንዳንዱ ተማሪ የሚጠበቅ ነው። በስኬት መንገዳችን ላይ የሚቆሙትን መሰናክሎች መሻገር ወይም ማሸነፍ ችግርን መፍታት ማለት ነው። በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ

ያሉትን ጨምሮ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ ብዙ ጉዳዮች አሉ። የትም ብንሰራም ሆነ ብንማር በየቀኑ መፍትሄ የሚሹ ችግሮች እንደሚያጋጥሙን መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ይህም እያንዳንዳችን በእለት ተእለት ግንኙነታችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን ችግሮች መፍታት እንድንችል የረዳናል።



የቡድን ሥራ

ችግር ለመፍታት መከተል ያለብንን ሂደቶች በቡድን በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አብራሩ

አንተ/አንቺ እና ሁለት ጓደኞችህ እርስ በርስ እየተረዳዳችሁ ስለምትማሩ በምትማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ ታዋቂዎች ናችሁ። ሁለቱ የቅርብ ጓደኞችህ በአጋጣሚ ይጣላሉ። በጓደኞችህ መካከል ያለው አለመግባባት ጓደኝነታችሁን ጎድቶታል። ከሁሉም በላይ ደግሞ የትምህርት አፈጻጸምህ ላይ ከፍተኛ ተዕዕኖ ፈጥሮብሃል። የሁለቱም ተማሪዎች የጋራ ጓደኛ ስለሆንክ የጓደኞችህን ችግር መፍታት የአንተ ሃላፊነት ነው። ሆኖም ችግራቸውን ለመፍታት ከመሞከርህ በፊት በመጀመሪያ ችግራቸውን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም በመጀመሪያ እነሱ የሚሉትን ማዳመጥ አለብህ። ጓደኞችህ ሀሳባቸውን እንዲገልጹ እድል ልትሰጣቸው ይገባል። ሃሳባቸውን ካዳመጥክ በኋላ ሁለቱንም ሊያረካ የሚችል የመፍትሄ ሃሳብ ማቅረብ አስፈላጊ ነው።ተጨባጭ መሆንህም በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የጓደኞችህን ችግር በዚህ መንገድ ለመፍታት ያስችልሃል።



የግንዛቤ ጥያቄ

በሁለቱ ጓደኞችህ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት እንዴት ልትፈታ ትችላለህ?

ማጠቃለያ

መረጃን በተጨባጭ የመተንተን እና ምክንያታዊ ውሳኔ የመስጠት ክህሎት በጥልቀት የማሰብ ዋና መገለጫ ነው። ይህም የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመገምገም ተጨባጭ ውሳኔ ማስተላለፍን ያካትታል ። በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶችን ማዳበር እውነተኛ መረጃ ለማግኘት፤የማህበረሰባችን መሰረታዊ ጥያቄዎች እና ችግሮችን ለመረዳት እና ለዴሞክራሲ ግንባታ ወሳኝ ጠቀሜታ አለው።

በዘመናችን ብዙ የመረጃ ምንጮች አሉ። መረጃ ከጓደኞች ፣ ከመምህራን ፣ ከጎረቤቶች ፣ ከቴሌቪዥን ፣ ከራዲዮ ፣ ከጋዜጦች ፣ ከመጻሕፍት ፣ ከፊልሞች እና ከማህበራዊ ሚዲያ መድረኮች ማግኘት ይቻላል። በተጨማሪም ትንተና፣ የቡድን ስራ፣ ፈጠራ እና የችግር አፈታት የመሳሰሉ መሰረታዊ በጥልቀት የማሰብ ክሎቶችን ማዳበር አስፈላጊ ነው። በአጠቃላይ በማህበረሰባችን ውስጥ የተንሰራፋውን እንደ የሰብዓዊ መብት ረገጣ፣ ድህነት፤ የአካባቢ ውድመት፤ ግጭት እና የመሳሰሉትን ችግሮች ለመፍታት በጥልቀት የማሰብ ክህሎትን ማዳበር ወሳኝ ነው።

ቁልፍ ፍቺ

- ትንተና- አንድን ጉዳይ ከተለያዩ ምንጮች መረጃ በመሰብሰም መገምገም
- ፈጠራ- አዲስ ሃሳብ ማቅረበ ወይም የነበረውን ማሻሻል
- በጥልቀት ማሰብ- መረጃ ባግባቡ በመተንተን ተጨባጭ ውሳኔ መስጠት
- ችግር መፍታት- ሂደቶችን በመከተል ውሳኔ መስጠት.
- በቡድን መስራት- በመተባበር በጋራ መስራት.
- የጋር ጥቅም- አባላትን ሁሉ የሚያሳትፍ

የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

ክፍል 1፡ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እውነት የተሳሳተ ከሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ/ሽ፡፡

1. ሁሉም የመረጃ ምንጮች ሁልጊዜ ታማኝ ናቸው::
2. በጥልቀት ማሰብ መረጃ ማሰባሰብ ብቻ ነው፡፡
3. ሳይተነተን የተለየ መረጃ እንደ እውነት መውሰድ በጣም ችግር ያለበት እና አደገኛ ነው፡፡
4. በጥልቀት ማሰብ ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡
5. የቡድን ስራ ለእያንዳንዱ ተማሪ ከፍተኛ አስተዋፆ አለው፡፡

ክፍል II፡ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ

6. ስለ በጥልቀት ማሰብ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው እውነት ነው?
   ሀ. በጥልቀት ማሰብ መረጃን የመተንተን ችሎታ ነው፡፡
   ለ. በጥልቀት ማሰብ ክፍት አእምሮ እንዲኖረን ይረዳናል፡፡
   ሐ. በጥልቀት ማሰብ ዴሞክራሲያዊ ሂደትን ያበረታታል፡፡
   መ. ሁሉም
7. አንድን ነገር የመመርመር ችሎታን የሚያመለክት በጥልቀት የማሰብ ክህሎት የቱ ነው፡፡
   ሀ. ፈጠራ ለ. ትንተና ሐ. የቡድን ሥራ መ. ችግር መፍታት
8. ከሌሎች ጋር አብሮ መስራትን የሚያመለክት በጥልቀት የማሰብ ክህሎት
   ሀ. ችግር መፍታት ለ. ትንተና ሐ. ፈጠራ መ. የቡድን ስራ
9. ከሌሎቹ የተለየ አዲስ ሃሳብ ማምጣትን የሚያመለክት በጥልቀት የማሰብ ክህሎት ነው፡፡
   ሀ. የቡድን ስራ ለ. ፈጠራ ሐ. ትንተና መ. ችግር መፍታት
10. ለስኬታችን እንቅፋት የሆኑትን መሰናክሎች ማለፍን የሚያመለክት በጥልቀት የማሰብ ክህሎት ነው፡፡
    ሀ. ችግር መፍታት ለ. ፈጠራ ሐ. ትንተና መ. የቡድን ስራ